# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ረቡዕ | 81ኛ ዓመት ቁጥር 313 ሐምሌ 13 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10.00 | ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







# ‹‹የኢትዮጵያን ብልጽግና ለማረጋገጥ ኢኮኖሚያዊ አቅማችንን ማጠናከር ይኖርብናል››

**- ወይዘሮ ሙፈሪሃት ካሚል**
**የሥራና ክህሎት ሚኒስትር**



ፎቶ - ዳኜ አበራ

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያን ሁለንተናዊ ብልጽግና ለማረጋገጥ ኢኮኖሚያዊ አቅማችንን በዘላቂነት ማጠናከር እንደሚገባ የሥራና ክህሎት ሚኒስትር ወይዘሮ ሙፈሪሃት ካሚል ገለጹ፡፡

ወይዘሮ ሙፈሪሃት ካሚል የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በጅማ ከተማ ባዘጋጀው ‹‹ስለኢትዮጵያ›› የውይይት መድረክ ላይ እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ ለዘመናት ነፃነቷ አስከብራ ኖራለች፡፡ ነፃነቷ የተሟላ እንዲሆን ደግሞ ኢኮኖሚያችንን በዘላቂነት አሳድገን መጓዝ ይኖርብናል።

ኢትዮጵያ ጠንካራ ኢኮኖሚዊ አቅም እንዲኖራት ስለሥራ፣ ብሩህ ሀሳብና ክሂሎት እንዲሁም ስለምርታማነት ይበልጥ ማሰብ ይገባናል ያሉት ሚኒስትሯ፤ የኢኮኖሚ ነፃነቱ ስር እንዲሰድ በልቶ ከማደር የሚሻገር ጠንካራ ሥራ ይጠይቀናል ሲሉ ተናግረዋል።

ኢትዮጵያን ዓለም ላይ ካሉ 20 ባለጠንካራ ኢኮኖሚ አገራት ውስጥ እንድትገባ የማድረግ የረጅም ጊዜ ትልም እንዳለ አስታውሰው፤ ለዚህም የአገር በቀል ኢኮኖሚን በተከተለ መንገድ በግሉና በመንግሥት ተሳትፎ ኢንቨስትመንትን የማስፋፋትና የሥራ ዕድል ፈጠራን የማሳደግ ተግባራት እየተከናወኑ መሆኑን ጠቁመዋል።

ኢትዮጵያ በተለያዩ ፈተናዎች ውስጥ ብትሆንም ጥቅም ላይ ያልዋሉ ዕምቅ ሀብትና የኢኮኖሚ አማራጮች እንዳሏት የጠቆሙት ሚኒስትሯ፤ ዕምቅ ሀብታችንን ተገቢው ጥቅም ላይ በማዋል በዘላቂነት የኢኮኖሚ ገቢያችንን ማሳደግ ይገባል ብለዋል።

ኢኮኖሚው ትልቅ አገራዊ፣ ቀጣናዊና ዓለም አቀፋዊ ዕድሎች እንዳሉት አመልክተው፤ ዕድሎቹን አሟጦ በመጠቀም በኩል ግን ያሉትን ክፍተቶች ማስተካከል እንደሚገባ ተናግረዋል፡፡

ለአብነት የግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ 44 በመቶ የሥራ ዕድል እንዲፈጥር ቢጠበቅም የእስካሁን አፈጻጸሙ ግን ከ26 በመቶ ያልዘለለ ነው፡፡ ኢንዱስትሪውም ከ50 በመቶ በታች በሆነ አቅም እያመረተ ነው ብለዋል፡፡

በመሆኑም ዕድሎችን በአግባቡ ለመጠቀምና አገራዊ


«የኢትዮጵያን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል












# ኢትዮጵያዊነት፣ አሸናፊነት!!

**ቦጋለ አበበ**

ኢትዮጵያውያን በሩጫው ዓለም አሻራችን ታላቅ ነው። ያ ታታሪው ዘመን የማይሽረው ጀግና አትሌት አበበ ቢቂላ በከፈተው በር የማይታጠፉ ዘመን ተሻጋሪ የድል ታሪኮችን በዓለም አደባባይ ስንጽፍም ኖረናል። እልፍ የአልሸነፍ ባይነት ተምሳሌት የሆኑ ጀግኖችን አፍርተን ለዓለም የጽናትን ሀሁ አስተምረናል።

ኢትዮጵያ የቱንም ያህል እንደ አለት የጠነከረ ፈተና ቢገጥማት በአንድነት፣ በፍቅርና በኅብረት ስናብር እንዴት እንደምንደምቅ ጀግኖች አትሌቶቻችን የኢትዮጵያዊነት ነጸብራቅ የሆነውን አልሸነፍ ባይነትን በኦሪገን ገልጠው አሳይተውናል።

በመካከለኛና ረጅም ርቀቶች ኢትዮጵያ በሩጫው ያላትን ታላቅ ተፈጥሮዓዊ አቅም በማውጣት ከአራቱም አቅጣጫ የዘር፣ ሃይማኖትና ፖለቲካን አጥር አፍርሰው ጀግኖቹ በኦሪገን የስኬት ማማ ላይ አረንጓዴ፣ ቢጫና ቀዩን ሰንደቅ ሰቅለዋል። በብዙ ችግሮችና ፈተናዎች ውስጥ አልፈው የተከፋበትን ነገር ሁሉ ወደ ጎን በመተው አገራቸውን ከፊት በማስቀደም ብሔራዊ መዝሙራቸውን ደጋግመው ዘምረዋል፣ አዘምረዋል።

ሻለቃ አትሌት ኃይሌ ገብረሥላሴ በዓለም ሻምፒዮናው ውድድር የታየው የቡድን ሥራና የአትሌቶች እርስ በርስ መተባበርና አንድነት ደግሞ ከምንም በላይ አስደሳች ነበር ብሏል።

ይህ ውድድር እኛ እርስ በርስ ከተከባበርንና


ኢትዮጵያዊነት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል







## እንቦጭን የሚያጠፋ የእንጉዳይ ዝርያ በምርምር መገኘቱ ተገለጸ

‹‹ወያኔ ዛፍ››ን በግብዓትነት የሚጠቀም ፋብሪካ ወደሥራ ገብቷል


ገጽ 4

# አረንጓዴ አሻራ መርሃግብርን ከኢንዱስትሪ ልማት ጋር አጣምሮ መሥራት እንደሚገባ ተገለፀ

**ውብሸት ሰንደቁ**

ድሬዳዋ፡- ለኢንዱስትሪዎች ቀጣይነት ያለው ውጤታማነት አረንጓዴ አሻራን ከኢንዱስትሪ ልማት ጋር አጣምሮ መሥራት እንደሚገባ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ገለፀ፡፡

የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈፃፀም እና የ2015 የዕቅድ መነሻ ውይይት በትናንትናው ዕለት ተጠናቋል፡፡

ሚኒስቴሩ ከክልል እና ከከተማ አስተዳደር ኢንዱስትሪ ቢሮዎች ጋር በመሆን በድሬዳዋ የሚገኙ ኢንዱስትሪዎችን በመጎብኘት በድሬዳዋ ኢንዱስትሪ ፓርክ የአራተኛው አረንጓዴ አሻራ የችግኝ ተከላ መርሃግብር አከናውኗል፡፡

የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ሽሰማ ገብረሥላሴ፤ አራተኛው የአረንጓዴ አሻራ ፕሮግራም በሁሉም አካባቢዎች ከሁሉም ሥራዎቻችን ጋር አስተሳሰረን የምንፈፀመው ተግባር ነው ብለዋል፡፡ በዘንድሮው ዓመት የአረንጓዴ አሻራ መርሃግብር በአገሪቱ በሚገኙ ኢንዱስትሪ ፓርኮች እና በሌሎችም አካባቢዎች 100 ሺህ ችግኞች ለመትከል አቅደው እየሠሩ መሆኑን ተናግረዋል፡፡


ፎቶ - በሃዲስ አብርሃ

በዚሁ ዓመት የአረንጓዴ አሻራ መርሃግብር በቂሊንጦ ኢንዱስትሪ ፓርክ፤ በደቡብ ክልል ሃድያ ዞን እንዲሁም በትናንትናው ዕለትም ሦስተኛውን ዙር በአዳማ ኢንዱስትሪያል ፓርክ ግቢ ውስጥ ማከናወናቸውን ገልፀው፤ ለኢንዱስትሪዎች ዘላቂነት ያለው ዕድገት ለማምጣት እና በዓየር ንብረት ለውጥ የማይናጋ ኢኮኖሚ ለመፍጠር የአረንጓዴ አሻራ መርሃግብርን መተግበር የውዴታ ግዴታ መሆኑን አብራርተዋል፡፡

አረንጓዴ ልማት ከኢንዱስትሪው ዘርፍ ተነጥሎ የሚታይ አይደለም ያሉት አቶ ሽሰማ፤ አብዛኞቹ ኢንዱስትሪዎች የግብርና ምርትን እንደ ግብዓት የሚጠቀሙ እንደመሆናቸው መጠን በአረንጓዴ አሻራ ላይ የሚሠራው ሥራ ኢንዱስትሪው በቂ ግብዓት እንዲያገኝ እንደሚረዳው ገልፀዋል፡፡

ሌላው የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ታረቀኝ ቡሉልታ በበኩላቸው፤ የ2014 በጀት ዓመት የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር አፈፃፀም የተሻለ እና ተስፋ ሰጪ ጅምሮች የታዩበት ነው፡፡ ይህ ጅምር ቀጣይ ሊሆን የሚችለው ከኢንዱስትሪዎች የሚወጡ በካይ እና ሙቀት አማቂ ጋዞችን መጥጠው የሚያስቀሩ እና የዓየር ንብረት እንዳይዛባ ማድረግ የሚችሉ ዛፎችን ማልማት ስንችል ነው ብለዋል፡፡

ከአረንጓዴ የኢንዱስትሪ ልማት አኳያ የችግኝ ተከላው ትልቅ ትርጉም የሚሰጠው ነው ያሉት አቶ ታረቀኝ፤ ከኢንዱስትሪዎች የሚወጣውን ካርበን መከላከል የሚቻለው ዛፎችን በመትከል ነው፤ በቀጣይም በሁሉም ኢንዱስትሪ ፓርኮች እና ሌሎች አካባቢዎች ጭምር የችግኝ ተከላ መርሃግብር በማካሄድ ዘላቂነት ያለው የኢንዱስትሪ ልማትን ለማረጋገጥ እንሠራለን ሲሉ ገልፀዋል፡፡

የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ ኃላፊ አቶ አሻግሬ ጀምበሬ፤ የኢንዱስትሪዎች ቀጣይነት ያለው ውጤታማነትን ለማረጋገጥ የአረንጓዴ አሻራ መርሃግብር ቁልፍ ሚና ይጫወታል ብለዋል፡፡

አረንጓዴ አሻራ ሥራ በአገራችን ፈርጀ ብዙ ጠቀሜታ ያለው ነው የሚሉት አቶ አሻግሬ፤ ኢንዱስትሪዎች በብቁ ሁኔታ አምርተው ውጤታማ የሚሆኑት የተስተካከለ የዓየር ንብረት ሲኖር ነው ሲሉ ገልፀዋል፡፡

እንደ አቶ አሻግሬ ገለፃ፤ ለዓየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖ የማይበገር ኢኮኖሚ ለመገንባትም የአረንጓዴ አሻራ መርሃግብር የማይተካ ሚና ስላለው የኢንዱስትሪ ልማትን ለማፋጠን በሚታሰብበት ጊዜ ሁሉ አረንጓዴ አሻራ ጋር አጣምሮ መሥራት ያስፈልጋል፡፡


ፎቶ - በገበቦ ገብሬ

# በኮቪድ የተቀዛቀዘው የሆቴል ዘርፍ በመንግሥት ጥረት መነቃቃት እየታየበት መሆኑ ተገለጸ

**ዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- በኮቪድ የተቀዛቀዘው የሆቴል ዘርፍ በመንግሥት ጥረት መነቃቃት እየታየበት መሆኑን የአዲስ አበባ ከተማ የባህልና ኪነጥበብ ቱሪዝም ቢሮ አስታወቀ። በግራንድ ኤልያና ሆቴል የተዘጋጀውና ለሁለት ቀናት የሚቆይ ባዛር በኤልያና ሆቴል ተከፍቷል።

የአዲስ አበባ ከተማ የባህልና ኪነጥበብ ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ሂሩት ካሳው የሆቴል ግብአት አቅራቢዎች ባዛር ትናንት ሲከፈት እንደገለፁት፤ በኮቪድ 19 ወረርሽኝ ምክንያት መቀዛቀዝ የታየበት የሆቴል ቱሪዝም ዘርፍ መንግሥት ባደረገው ያላሰለሰ ጥረት በዘርፉ ሕይወት መዝራት ተችሏል።

ባለፉት አስር ዓመታት የሆቴል ቱሪዝም ዘርፉ ከፍተኛ እድገት ማሳየቱን ያወሱት ኃላፊዋ፤ በተቃራኒው ባለፉት ሁለት ዓመታት ዘርፉ በኮቪድ 19 ወረርሽኝ ምክንያት መቀዛቀዝ ቢያሳይም መንግሥት የተለያዩ መውጫ መንገዶችን በመፈለግና በመተግበር የሆቴል ዘርፉ በአጭር ጊዜ መነቃቃት ማሳየት መቻሉን ገልጸዋል።

የሆቴል ግብአት አቅራቢዎች ባዛርና ኤክስፖዎች በሆቴልና ቱሪዝም ዘርፉ ላይ አዲስ አበባን የቱሪስት መዳረሻ በማድረግ ሂደት ላይ ሚናቸው የጎላ ነው ሲሉም ዶክተር ሂሩት ተናግረዋል።

የግራንድ ኤልያና ሆቴል የሰው ኃይል አስተዳደር የሆኑት ወይዘሮ ምሥራቅ ሞገስ በበኩላቸው እንደገለፁት፤ ባዛሩ በኮቪድ 19 ወረርሽኝ ምክንያት የተቀዛቀዘውን የሆቴል ቱሪዝም ዘርፍ ለማሳደግና ለማነቃቃት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው። ባዛሩ የኅብረተሰቡን አቅም ባገናዘበ ሁኔታ ምርት እና አገልግሎትን በአንድ ቦታ እንዲያገኙ በማድረግ አቅራቢውን እና ሸማቹን በቀላሉ የሚያገናኝ ነው።

በዓለማችን የሚገኙ ሆቴሎች ለተለያዩ ሥራዎች የሚሆኑ አልግሎቶችን እና ግብአቶችን ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪን በማውጣት አገርን በተለያየ አላስፈጊ ወጪ እንደሚዳረጉ የገለፁት ወይዘሮ ምሥራቅ፤ ባዛሩ አገር ውስጥ ያሉ የሆቴል አቅራቢዎችን ከሆቴሎች ጋር በማገናኘት እየባከነ ያለውን ምንዛሬ ከመተካት አንፃር ጉልህ ሚና የሚጫወት እንደሆነም ገልፀዋል።

ባዛሩ የሆቴል ግብአት አቅራቢዎች፣ የንግዱ ማኅበረሰብ፣ ባለድርሻ አካላትና ከፍተኛ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች በተገኙበት ተከፍቷል። ግራንድ ኤልያና ሆቴል በከተማችን ካሉ ባለ አራት ኮከብ ሆቴሎች አንዱ ሲሆን የቱሪዝም እድገትን እያሳደጉ ከሚገኙ ሆቴሎች መካከል ሰፊውን ድርሻ ይዞ በመሥራት ላይ እንደሚገኝ በመድረኩ ተመላክቷል።

# በተጠናቀቀው የበጀት ዓመት ከ336 ቢሊዮን ብር በላይ ገቢ ተሰበሰበ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የገቢዎች ሚኒስቴር በተጠናቀቀው የ2014 በጀት ዓመት ከ336 ቢሊዮን ብር በላይ ገቢ መሰብሰቡን የገቢዎች ሚኒስትር አቶ ላቀ አያሌው አስታወቁ።

ኢትዮጵያ በ2022 አገራዊ የታክስ አስተዳደር ተገንብቶ አገራዊ ወጪን በራሷ ገቢ ለመሸፈን የምታደርገውን ጥረት ለማሳካት ተልዕኮ የተሰጠው የገቢዎች ሚኒስቴር በስኬት ገቢን የመሰብሰብ አቅሙ ተጠናክሮ ቀጥሏል ብለዋል።

ለዚህም ማሳያ የሚሆነው ሚኒስቴሩ በዚህ በጀት ዓመት ሊሰበስብ ካቀደው 360 ቢሊዮን ብር ውስጥ 336 ቢሊዮን 710 ሚሊዮን 021 ሺ 930 ብር በመሰብሰብ የእቅዱን 93 ነጥበ 53 በመቶ ማሳካቱ ነው ተብሏል።

አፈፃፀሙ ከባለፈው በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻፀር የብር 57 ቢሊዮን 494 ሚሊዮን 923 ሺ 697 ወይም የ20 ነጥብ 59 በመቶ እድገት እንዳለው አቶ ላቀ አያሌው ተናግረዋል።

የተሰበሰበው ገቢ ምንጭ ከአገር ውስጥ ታክስ 196 ቢሊዮን 211 ሚሊዮን 638 ሺ 548 ብር የሚሸፍን ሲሆን ከውጭ ንግድ ቀረጥና ታክስ ደግሞ 140 ቢሊዮን 498 ሚሊዮን 338 ሺ 382 ብር መሆኑን ጨምረው ገልጸዋል።

ገቢው በአገራችን በተፈጠረው ጦርነት ብዙ ተቋሞቻችን ከሥራ ውጪ በሆኑበት፣ በጦርነቱ ምክንያት የንግዱ እንቅስቃሴ በተቀዛቀዘበት፣ በተለያዩ አካባቢዎች በሚፈጠሩ ግጭቶች ተቋሞቻችን በአግባቡ ሥራቸውን እንዳይሠሩ በተቸገሩበት እንዲሁም የንግዱ ማኅበረሰብ ሥራውን ተረጋግቶ ባልሠራበት ሁኔታ ውስጥ በመሰብሰቡ የተሻለ አፈጻጸም ሊያስብለው እንደሚችል ተጠቁሟል።

የሕገ-ወጥ ንግድና ኮንትሮባንድ እንዲሁም የሀሰተኛ ግብይት ለገቢ አሰባሰቡ ትልቅ ተግዳሮት ቢሆንም ይህንን ለመሻገር የገቢዎች ሚኒስቴር ከኅብረተሰቡ እና ከባለድርሻ አካላት ጋር የሚሠራቸው ቅንጅታዊ ሥራዎች




ተጠናክረው የቀጠሉ ቢሆንም ሕገ-ወጥ ድርጊቱ ሙሉ በሙሉ ባልተቀረፈበት ሁኔታ ገቢያችን በዚህ ደረጃ መሰብሰቡ የተቋሙን ስኬታማነት ማሳያ ነው ሲሉ ሚኒስትሩ ተናግረዋል።

# በጎ ተግባር የህሊና ደመወዝ አለው

ሳሙኤል ወንደሰን

ወጣት በብዛት ከሚገኝባቸው አገራት መካከል አንዷ ኢትዮጵያ ናት። በኢትዮጵያ ታዲያ ወጣቱ ክፍል ከመሥራትና አገርን ከማሳደግ ይልቅ ባልባሌ ትርክቶች ተጠምዶ እርስበርስ ሲጋጭ ማስተዋል ከተጀመረ ዋል አደር ብሏል።

በአገሪቱ የሚሠራ ሥራ ጠፍቶ ሳይሆን አለመስማማቶች በመበራከታቸው የሚሠሩ እጆች ለጥፋት እየዋሉ ይገኛሉ። ከጸጥታም አኳያ ጠንከር ያሉ ሥራዎች ባለመከናወናቸው ዝርፊያና ቅሚያ በከተሞች አካባቢ እየተስፋፋ ይገኛል።

ይሁን እንጂ እነዚህ ሁሉ ችግሮች የመኖራቸውን ያህል አገርን የሚያቆሙ መልካም ሥራዎችም በርከት ያሉ ናቸው፡፡ ከጊዜ በኋላ የመጣብን በሽታ ሆኖ ግን ከነዚህ ሥራዎች ይልቅ ክፉ ሥራዎች በማኅበራዊ፣ ሚዲያ አማካኝነት ቦታ ሲያገኙና በኅብረተሰቡ ውስጥም በስፋት ሲሰራጩ ይስተዋላል፡፡ ነገር ግን አገርን ለማስቀጠል ሁሉንም በሚዛን መመልከቱ እና መረዳቱ መልካም ነው፡፡

እኔም ዛሬ ይህን ጉዳይ ያለ ምክንያት አይደለም ያነሳሁት። ለጥፋት የሚውሉ እጆች እንዳሉ ሁሉ ለበጎ ተግባራት የሚሰነዘሩ እጆች እንዳሉ ለማሳየት ፈልጌ ነው።

«የበጎ ፍቃደኝነት አገልግሎት ጊዜና ሁኔታ አይገድበውም። የሰው ልጆች ሁሉ ደረጃቸው ይለያይ እንጂ ድጋፍና እርዳታ ያስፈልጋቸዋል» ይላል ወጣት ፍቅሩ ቀልቤሳ። ወጣት ፍቅሩ በኢንተርናሽናል ቢዝነስ ማኔጅመንት የትምህርት መስክ የሁለተኛ ዲግሪውን ከያዘ አንድ አመት ሆኖታል። በአዲስ አበባ ከተማ ቆይታው ሥራ እያፈላለገ ከመቆየት ጎን ለጎን ደግሞ በበጎ ፍቃድ ሥራ ተሰማርቷል።

በዓለም ላይ ሁሉም ሰው በአንዴ ሙሉ ጤነኛ፣ ሀብታም ወይም የሞላለት አይሆንም። መለያየቱ የተፈጥሮ ሕግጋቶች ናቸው ባይ ነው። በጎ ተግባር የህሊና ደመወዝ አለው ሲልም ይናገራል።

ሁል ጊዜ ክፍያ ላለው ነገር ብቻ የምንሮጠው የትም አያደርሰንም። አገር እንድትለማ፣ ኢኮኖሚያችን እንዲያድግ፣ ኅብረተሰቡ ጤናማ እንዲሆን መተባበር እንደሚገባም ይናገራል።

በዚኛው አመት የክረምት በጎ ፍቃድ አገልግሎት ላይ መሰማራቱ ቀጣዩ ትውልድ አገርን ታላቅና በርካታ የተማረ የሰው ኃይል እንዲኖራት ያስችላል ሲል ይገልፃል ወጣት ፍቅሩ።



ወጣት ፍቅሩ ቀልቤሳ



ወይዘሮ ቃልኪዳን ሽፈራው
የልደታ ክፍለ ከተማ ወጣቶች ማህበር ሰብሳቢ



አቶ በኃይሉ ጥላሁን
የሜጀር ጀነራል ሀየሎም አርአያ የመጀመሪያ ደረጃ
ትምህርት ቤት ዋና ርዕሰ መምህር

በክረምት የእረፍት ጊዜዬን የማሳልፈው በዘመድ ጥየቃና በመዝናናት ነበር የሚለው ወጣት ብሩክ ነጋሽ በበኩሉ ከዩኒቨርሲቲ የወጡ ወጣት ተማሪዎችን በበጎ ፈቃድ አገልግሎትና በሌሎች ተግባራት ማሳተፍ ለአገር እድገትና ብልጽግና ከፍተኛ አስተዋጽዖ አለው ይላል።

የክረምት በጎ ፍቃድ ከማኅበረሰባችን ምስጋና የምናገኝበት፣ ሰፊ ልምድ የምንቀስምበት፣ መንፈሳዊ በረከትና የህሊና እርካታ የምንጎናፀፍበት፣ ማኅበራዊ መስተጋብራችንን የምናጠናክርበት መልካም አጋጣሚን የሚፈጥር ነው።

አገልግሎቱ በእኛ አገር የተለመደው በከተማ ትምህርት ሲዘጋ ተማሪዎችና መምህራን የክረምት ወቅትን ተከትሎ የክረምት በጎ ፈቃድ አገልግሎት በስፋት እንዲሰጡ ይደረጋል። ነገር ግን ሁሉም ሰው በየትኛውም ወቅትና ቦታ የበጎ ፈቃድ አገልግሎቱን መስጠት ይችላል።

ሁሉም ሰው በሚችለው ልክ በጋራ በመተጋገዝ የብዙኃን ችግርን ለመቅረፍ የሚያስችል ተግባር ማከናወን ይኖርበታል። ስለዚህ በከተማ የሚገኙ ወጣቶች፣ ኅብረተሰብና ተቋማት በበጎ ፈቃድ በሚከናወኑ ተግባራት ላይ በንቃት እንዲሳተፉና ለሌሎችም አርአያ እንዲሆኑ መልዕክት አስተላልፋለሁ ብሏል።

የክረምት በጎ ፍቃድ አገልግሎት ከዛሬ አስራዘጠኝ አመት በፊት በአዲስ አበባ ወጣቶች ፊት አውራሪነት የተጀመረ መሆኑን የልደታ ክፍለ ከተማ ወጣቶች ማኅበር ሰብሳቢ ወይዘሮ ቃልኪዳን ሽፈራው ይናገራሉ።

ከለውጡ በፊት የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ውስን ከመሆኑ የተነሳ ከከተማ አስተዳደሩ የሚፈለጉ ነገሮችን በፍጥነት ያለማግኘት ሁኔታዎች ነበሩ። በባለሀብቱ በኩል ደግሞ በመንግሥት በኩል ካልሆነ ድጋፎችን አናደርግም የማለት ሁኔታዎች ይፈጠሩ ነበር።

በበጎ ፈቃደኝነት የተደራጁ ማኅበራትን ማገዝ የማይፈልጉበት ሁኔታም ነበር። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን በከተማዋ መነቃቃትና ለውጥ መኖሩን ሰብሳቢዋ ይናገራሉ።

የክረምት በጎ ፍቃድ በተለይ ከዩኒቨርሲቲ የሚመጡ ወጣቶች የትርፍ ጊዜያቸውን በተለያዩ የበጎ ፈቃድ አገልግሎቶች ማኅበረሰቡን እያገለገሉ የሚሄዱበትና በአጭር ጊዜ ውስጥ ሰፊ ትርፍ የሚገኝበት በመሆኑ ለአገር እድገት ጉልህ ሚና አለው።

አሁን ላይ ማኅበረሰቡ ስለበጎ ፍቃድ አገልግሎት ያለው ግንዛቤ ሰፊ ነው። ካስተዋላችሁት ወጣቶች በየአካባቢያቸው እየተደራጁ የአረጋውያንን ቤት ያድሳሉ፤ አካባቢያቸውንም ያፀዳሉ እና ኅብረተሰቡ ላይ ያለው ግንዛቤ ከዚህ በፊት ከነበረው የተሻለ ነው ሲሉ ይገልፃሉ።

የክረምት የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ዕድሜ አይመርጥም፡፡ በተለይ ወጣቶች ላይ ይሠራል እንጂ ሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል የሚሠራው ሥራ ነውና ማኅበረሰቡ የክረምት በጎ ፍቃድ አገልግሎትን እንደሃሳብ ተቀብሎ አካባቢያቸውን የሚያጸዱበት፣ ችግኞችን የሚተክሉበትና ልጆቻቸውን ለማጠናከሪያ ትምህርት ወደ ትምህርት ቤት እንዲልኩ ጥሪ አስተላልፋለሁ ብለዋል።

በልደታ ክፍለ ከተማ የሜጀር ጀነራል ሀየሎም አርአያ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ርዕሰ መምህር የሆኑት አቶ በኃይሉ ጥላሁን በበኩላቸው፣ ከዚህ በፊት የክረምት በጎ ፍቃድ ሰጪ መምህራን የሚመለመሉት በክፍለ ከተማና በወረዳ ደረጃ ነበር።

ዘንድሮ ግን ሥራዎችን የጋራ የማድረግ ሁኔታዎች ይታያል። በዚህም ትምህርት ቤቱ ለትምህርት አገልግሎት የሚረዱ ቁሳቁሶችን ከማሟላት ባለፈ ለክረምቱ የሚያስተምሩ መምህራንና የሚማሩ ተማሪዎችን የመቀስቀስ ሥራዎችን እየሠራ ይገኛል።

የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች የሚሰጡት ማጠናከሪያ ትምህርት በርካታ አስተዋፅኦ አለው። በተለይ ሰባተኛ ክፍል የእንግሊዝኛ ትምህርቶች የሚጀምሩበት በመሆኑ በክረምቱ ከትምህርቶች ጋር ተዋውቀው ስለሚመጡ በጋው ላይ ለትምህርቱ አዲስ አይሆኑም። ይህም ውጤታቸው እንዲሻሻል ማድረጉ የማይካድ ነው።

ወጣቱ ይህን የበጎ ፍቃድ አገልግሎት አጠናክሮ እንዲቀጥልበትና መንግሥት ለዚህ መልካም ተግባር ድጋፎችን እንዲያደርግ እጠይቃለሁ ብለዋል።

# የገቢ ግብርን በቴሌብር መክፈል የሚያስችል ሥርዓት ተግባራዊ ተደረገ

ፋንታነሽ ክንዴ

አዲስ አበባ፡- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮና ኢትዮ ቴሌኮም ገቢ ግብርን በቴሌብር መክፈል የሚያስችል ሥርዓት ተግባራዊ አድርገዋል። የኢትዮ ቴሌኮም ዋና ሥራ አስፈጻሚ ወይዘሪት ፍሬሕይወት ታምሩና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ ኃላፊ አቶ ሙሉጌታ ተፈራ ገቢ ግብርን በቴሌብር መክፈል የሚያስችል ስምምነት በትናንትናው ዕለት ተፈራርመዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ ኃላፊ አቶ ሙሉጌታ ተፈራ ስምምነት በተፈረመበት ወቅት እንደገለጹት፤ ስምምነቱ የግብር ከፋዮችን እንግልት በመቀነስ በቢሮውና በግብር ከፋዮች መካከል ያለውን መተማመን ያሳድጋል።

የግብር አሰባሰብ ሥርዓቱን በማዘመን ከዚህ በፊት በተበጣጠሰ መንገድ ሲሰበሰቡ የነበሩ ገቢዎችን በተደራጀ መንገድ እንዲሰበሰብ በማድረግ ውጤታማነቱን ከፍ ያደርገዋል ያሉት አቶ ሙሉጌታ፤ የተዘረጋው ሥርዓት ሌብነትና ብልሹ አሠራርን በማስቀረት በኩልም ትልቅ ድርሻ እንደሚኖረው ጠቁመዋል።

በከተማ አስተዳደሩ ወደ 340 ሺህ የሚጠጉ የደረጃ “ሐ” ግብር ከፋዮች መኖራቸውን ጠቁመው፤ በዚህ ማዕቀፍ ውስጥ የሚካተቱት በቀጥታ በቁርጥ ግብር የሚወሰንባቸው ከ285 ሺህ በላይ የሚሆኑ ግብር ከፋዮች መሆናቸውን አመልክተዋል።

ብዙዎቹ የመንግሥት የክፍያ ሥርዓቶች በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በኩል በመሆናቸው ግብር ከፋዮች በንግድ ባንክ ብቻ እንዲከፍሉ ይገደዱ ነበር ያሉት ቢሮ ኃላፊው፤ አሁን ላይ ግን የባንክ ሂሳብ ቁጥር(አካውንት) ካላቸው ከየትኛውም ባንክ በቴሌብር በኩል ግብራቸውን መክፈል ይችላሉ ብለዋል።

ፎቶ - በኤዮብ ተፈራ




ቢሮው በ2015 በጀት ዓመት 70 ቢሊዮን ብር የሚደርስ ገቢ ለመሰብሰብ ማቀዱን ጠቁመው፤ የተዘረጋው ሥርዓት ይህን እቅድ ለማሳካት ትልቅ አቅም ይፈጥራል። በቀጣይነትም አገልግሎቱን ወደ ደረጃ “ሀ” እና “ለ” ግብር ከፋዮችም በማሳደግ አብዛኞቹ ቢሮው አገልግሎቶች ዲጂታላይዝድ ለማድረግ እንሠራለን ብለዋል፡፡

የኢትዮ ቴሌኮም ዋና ሥራ አስፈጻሚ ወይዘሪት ፍሬሕይወት ታምሩ በበኩላቸው፤ ግብር ከፋዮች ግብር ለመክፈል ተጨማሪ ወጪ ማውጣትና መንገላታት አይገባቸውም። በመሆኑም ቢሮው ከኩባንያችን ጋር ባደረገው ስምምነት መሠረት ግብር ከፋዮች ጊዜያቸውን፣ ገንዘባቸውንና ጉልበታቸውን ቆጥበው ግብራቸውን በቀላሉ በቴሌብር መክፈል ይችላሉ ብለዋል።

ዜጎች አገልግሎት ለማግኘትና ክፍያ ለመፈጸም ከቦታ ቦታ በመዘዋወር የሚያጠፉትን ጊዜ በሥራ ላይ እንዲያውሉ በማድረግ ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ ያስችላል ያሉት ዋና ሥራ አስፈጻሚዋ፤ በቀጣይነትም የደረጃ “ሀ” እና “ለ” ግብር ከፋዮችም አገልግሎቱን እንዲያገኙ ይሠራል። አገልግሎቱ ከአዲስ አበባ ከተማ በተጨማሪ ለፌዴራል ግብር ከፋዮች ተደራሽ የሚደረግ መሆኑንም አስታውቀዋል።

ባለንበት ጊዜ አንዱና ዋናው አስፈላጊ ነገር ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ መሆኑን ጠቅሰው፤ ኢትዮጵያን ዲጂታላይዝ ለማድረግ የምንሠራው ሥራ የዜጎችን ጊዜና ጉልበት በመቆጠብ ምርታማነታቸውን እንዲያሳድጉ ያግዛል። ከግብር በተጨማሪ ሌሎች የከተማዋ አገልግሎቶችን ዲጂታላይዝ ለማድረግ ሥራዎች እየተሠሩ መሆናቸውንም ጠቁመዋል።

ግብር ከፋዮች በሞባይል ስልካቸው ከአዲስ አበባ ገቢዎች ቢሮ በ7075 በአጭር የጽሑፍ መልዕክት በሚደርሳቸው የክፍያ ማዘዣ ቁጥርን በመጠቀም ግብራቸውን መክፈል የሚችሉ መሆኑ የተጠቀሰ ሲሆን፤ ከዚህ በፊት ያስመዘገቡትን ስልክ ቁጥር ከቀየሩ መልዕክት ስለማይደርሳቸው አቅራቢያቸው ወደሚገኙ ቅርንጫፍ ጣቢያዎች ሄደው ማስተካከል እንዳለባቸው ተጠቁሟል።

ግብርን በቴሌብር መክፈል የሚያስችለው ሥርዓት ከሐምሌ 1 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ መደረጉ የተገለጸ ሲሆን፤ እስካሁን ድረስ 679 በሚሆኑ ግብር ከፋዮች በቴሌ ብር አማካኝነት አራት ሚሊዮን ብር የሚጠጋ ገንዘብ ግብር መክፈላቸውን ታውቋል።

ዜና

# «ባለፉት 10 ሳምንታት ከ130 ሺህ ቶን በላይ ምግብና ምግብ ነክ ድጋፍ ወደ ትግራይ ተልኳል»

### - የዓለም የምግብ ፕሮግራም




አዲስ አበባ፡- ባለፉት 10 ሳምንታት ብቻ ከ130 ሺህ ቶን በላይ ምግብና ሌሎች ሰብዓዊ ድጋፎች ወደ ትግራይ መላካቸውን በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የዓለም የምግብ ፕሮግራም ገለፀ።

በዓለም የምግብ ፕሮግራም የኢትዮጵያ ተወካይ ክላውድ ጂቢዳር እንደገለፁት፤ መንግሥት ሰብዓዊ ድጋፍ ወደ ትግራይ ክልል እንዲገባ መፍቀዱን ተከትሎ የዓለም የምግብ ፕሮግራም የሚያቀርበውን ሰብዓዊ እርዳታ በከፍተኛ ሁኔታ አሳድጓል።

በሌላ በኩልም የተባበሩት አረብ ኤምሬቶች በሰሜን ኢትዮጵያ በአማራ፣ በትግራይና በአፋር ክልሎች ለሚገኙና በጦርነት ጉዳት ለደረሰባቸው ወገኖች ሰብዓዊ እርዳታ የሚውል 60 ሚሊዮን ዶላር ድጋፍ ማድረጉንም ተወካዩ ተናግረዋል።

ድጋፉ በጦርነት ምክንያት ከቀዬአቸው ለተፈናቀሉ፣ ለምግብ እጥረት ለተጋለጡ ሕፃናት፣ እናቶች እና አቅመ-ደካሞች ለአደጋ ጊዜ የምግብ አቅርቦት እንደሚውልም ድርጅቱ አስታውቋል።

የተባበሩት አረብ ኤሜሬቶች ያደረገችው ድጋፍ በትክክለኛው ሰዓት የተደረገ መሆኑን ገልፀው፤ ድጋፉ በተቻለ ፍጥነት እንዲደርስ የሚደረግ መሆኑን ጠቁመዋል ሲል ኢዜአ ዘግቧል።



# እንቦጭን የሚያጠፉ የእንጉዳይ ዝርያ በምርምር መገኘቱ ተገለጸ

### ‹‹ወያኔ ዛፍ››ን በግብዓትነት የሚጠቀም ፋብሪካ ወደሥራ ገብቷል

**ክፍለዮሐንስ አንበርብር**

አዲስ አበባ፡- እንቦጭን በመመገብ ማጥፋት የሚችል የእንጉዳይ ዝርያ በምርምር መገኘቱን የኢትዮጵያ ደን ልማት አስታወቀ፡፡

በተለምዶ የወያኔ ዛፍ የሚሰኘውንና በሳይንሳዊ አጠራሩ «ፕሮሶፒስ» የተባለውን የዕፅዋት ዝርያ ለጣውላ፣ ለፐርኬ፣ ለቤት ግንባታና ለተለያዩ አገልግሎቶች እንዲውል የሚያግዝ ፋብሪካ ሥራ መጀመሩን ተቋሙ አስታውቋል።

በኢትዮጵያ ደን ልማት የደን ውጤቶችና ኢኖቬሽን ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ዳንኤል ገበየሁ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፤ እንቦጭ አረምን ለማጥፋት ብዙ ጥረትና ምርምር ሲደረግ ቆይቷል። በአሁኑ ወቅት እንቦጭን በመመገብ የሚያጠፉ እንጉዳይ ዝርያ በምርምር ተገኝቷል፡፡ የምርምር ውጤቱ የእንቦጭ አረምን ለማጥፋት ይረዳሉ ተብለው ለመፍትሔነት ከቀረቡ አማራጮች መካከል አንዱ ነው።

በምርምሩ መሠረት እንቦጭ ያለበት ቦታ ላይ እንጉዳዩ እንዲዘራ ይደረጋል ያሉት ዳይሬክተሩ፤ እንጉዳዩ ሲበቅል እንቦጭን እንደ ምግብ በመጠቀም የሚያድግ ይሆናል፤ በዚህ ሂደት እንጉዳዩ ለሰው ልጆች ምግብነት የሚውል ሲሆን፤ እንቦጩ ደግሞ እየጠፋ ይሄዳል ብለዋል፡፡

ተቋሙ የእንጉዳይ ምርት ላይ የተለያዩ ምርምሮችን እያደረገ መሆኑን አቶ ዳንኤል ገልጸው፤ በቀጣይ ጊዜያትም የሚገኙ የምርምር ውጤቶችን በሰፊው ጥቅም ላይ ለማዋል ጥረት እንደሚያደርግ ጠቁመዋል።

ከዚህ ባለፈ ተቋሙ መጤ አረሞችን ወደ ጥቅም ሰጪ ነገር ለመቀየር የተለያዩ ምርምሮችንና የቴክኖሎጂ አማራጮችን ጥቅም ላይ ለማዋል እየሠራ እንደሚገኝ ተናግረዋል፡፡

አቶ ዳንኤል እንዳስታወቁት፤ የወያኔ ተክል በአፋርና ሱማሌ ክልሎች አንድ ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ሄክታር መሬት ላይ ተንሰራፍቷል። ስርጭቱን ሙሉ ለሙሉ መግታት ወይንም ደግሞ ስርጭቱን በሂደት ማቆም ያስፈልጋል፡፡

ይህ የዛፍ ዝርያ በአርብቶ አደርነት የሚተዳደረውንና የአፋር እና ሱማሌ ክልል ማኅበረሰብ ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ እየፈጠረ ሲሆን፣ በወተትና ሥጋ ምርት ላይም አሉታዊ ጫና አሳድሯል፡፡ በእነዚህ አካባቢዎች የሳር ግጦሽ ወሳኝ ሲሆን፤ ይህ አረም ግን ሳር፣ ቅጠላ ቅጠልና ሌሎች የዕፅዋት ዝርያዎች እንዲጠፉ እያደረገ ነው ብለዋል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የከርሰ ምድር ውሃን በከፍተኛ ሁኔታ ስለሚመጥና ከፍተኛ ትነት በመኖሩ የሥነ-ምህዳር መዛባትን እያስከተለ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

የወያኔ ተክልን እየተጠቀሙ ማጥፋት የሚለው መርህ ትኩረት ተደርጓል ያሉት አቶ ዳንኤል፤ አረሙን ሙሉ ለሙሉ ለማጥፋት ባይቻልም እንኳን ባለበት ለመቆጣጠር ተክሉን ለጣውላ ምርትነትና ለከሰል ምርት ለማዋል የሚደረገውን ጥረት ተቋሙ እየደገፈ መሆኑን ገልጸዋል።

በተለያዩ አካባቢዎች እየተስፋፋ የመጣውን በተለምዶ “ወያኔ” ዛፍ የሚባለውን በሳይንሳዊ አጠራሩ «ፕሮሶፒስ» የተሰኘውን ተክል ለፋብሪካ ግብዓት እንዲውል ተደርጓል።

ወያኔ ዛፍን ለጣውላ፣ ለቤት ግንባታና ለተለያዩ አገልግሎቶች እንዲውል የሚያደርግ ፋብሪካ ሥራ ጀምሯል።

የወያኔን ዛፍ በዘመናዊ መንገድ ወደ ከሰልና አማራጭ ኢነርጂ በመቀየርም ጥቅም ላይ ማዋል ይቻላል ያሉት አቶ ዳንኤል፤ ለዚህም በአፋር ክልል አሚባራ ወረዳ ፋብሪካ ተቋቁሞ ወጣቶችም ተደራጅተውና ስልጠና ወስደው ወደ ሥራ መግባታቸውን አረጋግጠዋል፡፡

# ‹‹የኢትዮጵያን ብልጽግና...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ትልሞችን ለማሳካት ተጨማሪ ጥረት እንደሚያስፈልግ ጠቁመዋል።

በተጨማሪ ኢኮኖሚያዊ ነፃነታችንን ዘላቂነት እንዲኖረው በሕግ የታገዘና የሠራተኛን አቅም የሚያሳድግ አሠራር መፍጠር ይኖርብናል ሲሉ ገልጸዋል።

አሁን ላይ ግን ሕጎቻችን ጉልበታቸው የሚለካው በመቆለፍ አቅማቸው እንጂ ምቹ ሁኔታ በመፍጠር አይደለም ያሉት ወይዘሮ ሙፈሪሃት፤ ይህንን ለመፍታትና አዳዲስ ሥራ ፈጣሪዎችን ወደ ገበያው ለማስገባት የሚረዳ የሕግ ዝግጅት መደረጉን ጠቁመዋል።

ከዚህ ባለፈ ኢኮኖሚው በዘላቂነት እንዲያድግ የአምራች ኃይሉን አቅም ማጠናከር ይገባል፤ በዚህ ረገድ መንግሥት ትኩረት አድርጓል ሲሉ ተናግረዋል።

በተለያዩ ያደጉ አገራት የአብዛኛው ዜጎቻቸው ዕድሜ የገፋ መሆን ፈተና ሆኖባቸዋል ያሉት ሚኒስትሯ፤ ኢትዮጵያ 70 በመቶ የሚሆነው ዜጋዋ ወጣት ነው፡፡ ይህም ትልቅ የመወዳደሪያ አቅም ስለሆነ ብቃት ባለው ሥርዓተ ስልጠና በመደገፍ ወደ ውጤት ለመቀየር እየተሠራ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

እንደ ሚኒስትሯ ገለጻ፤ ሥራን በአግባቡ የሚመራ ኃይል ያስፈልገናል። በተለይ በአስተሳሰቡ፣ በስብዕናውና በአገር ወዳድነቱ ልቆ የድህነት ታሪካችንን ለመቀየር የሚታትር ወጣት ማፍራት የሁላችንም የቤት ሥራ ሊሆን ይገባል።

ባለፉት ጊዜያት የነበረን የታሪክ ውጣውረድ አወንታዊም አሉታዊም ጎኖች አሉት፡፡ ከትውልድ ትውልድ እየተወራረሱ መቀጠል የሌለባቸውን ልማዶች ማስቆም እንዲሁም ጠንካራ የሥራ ልምዶችን ደግሞ ማጎልበት ይጠበቅብናል ብለዋል።

እንደአጠቃላይ ለአገራዊ የኢኮኖሚ መጠናከር ከግለሰብ ጀምሮ በየደረጃው ያሉ ሁሉም ባለድርሻ አካላት ሚናቸውን ለመወጣት መዘጋጀት እንዳለባቸው ወይዘሮ ሙፈሪሃት አሳስበዋል።

# ኢትዮጵያዊነት፣...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ከተዋደድን ሌላው እንደሚያከብረን፣ እንደሚያቅፈን አመላካች መሆኑንም ጠቅሷል።

ኢትዮጵያውያኑ ድል ባደረጉት በሁለቱም ውድድር የቡድን ሥራ እንደነበረው አስታውሶ፤ ይህ በቀጣይም መቀጠል እንዳለበት ነው የገለጸው።

መላው የኢትዮጵያ ሕዝብም ከመከፋፈል ይልቅ በአንድነት ድህነትን ታግሎ መጣል ቀዳሚው ሥራ አድርጎ ከተነሳ ታላቋን ኢትዮጵያ መገንባት ይቻላል ብሏል።

በአጠቃላይ የዓለም ሻምፒዮናው የኢትዮጵያን ሕዝብ ያስደሰተና የአንድነት ስሜት የፈጠረ እንደሆነ ነው የተናገረው።

አትሌቶቻችን በልባዊ ፍቅር እንዲህ ከኢትዮጵያ ጎን ስንቆም አገራችንን ከፍ አድርገን በዓለም መድረክ ማስጠራት እንደምንችል አስተምረውናል። ለእኛ ብቻ ሳይሆን ፊቱን ኢትዮጵያ ላይ ላዞረ ሁሉ በተደጋጋሚ ድሎቻቸው ትልቅ መልዕክት አስተላልፈዋል። በድላቸው ጠላት አሳፍረዋል። በጦርነት፣ በመፈናቀል፣ በንጹሃን ግድያ ልትፈርስ አንድ ሐሙስ ቀራት ብለው የሚያስቧትን አገር በሜዳሊያ ሰንጠረዥ ኃያሏን አሜሪካ የምትገዳደር አድርገዋል።

ኢትዮጵያዊነት! አልሸነፍ ባይነት። ከዚህ በላይ ምን የሚያስደስት ነገር አለ?፣ ይሄ ከፍታችን በኅብረት የመሥራት ውጤታችን ነው። ኢትዮጵያዊነት ጠንካራ መሠረት ነው፣ አሸናፊነት ነው፣ ሁሉን የመውደድ ምስጢር ነው፣ ለሌላው የማዘን መንፈስ ነው፣ ስለ አገር ፍቅር ማንባት ነው፣ ይህም በጀግኖቹ ልጆቿ ኦሪገን ላይ ተገልጧል። ዛሬም ነገም ወደፊትም ይቀጥላል። ኢትዮጵያ በተለይም እንዲህ በውስብስብ ችግሮች ውጥረት ውስጥ በገባችበት በዚህ ወቅት ከሁሉም አቅጣጫ ተሰባስበው ለክብሯ የተዋደቁ ጀግኖቿ የተጎናጸፉት አንጸባራቂ ድል በስፖርታዊ ስኬት ብቻ የሚለካ አይሆንም። ከሌሎች ተለይቶ ታሪክ ሲያወሳው የሚኖር በወርቅ ቀለም የሚጻፍ ግዙፍ አሻራ ይሆናል።

የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት ኮማንደር ደራርቱ ቱሉ በበኩሏ በአሜሪካ ኦሪገን በሚካሄደው የዓለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና ኢትዮጵያውያን ያሳዩት ጥንካሬና ድል የሚደነቅ መሆኑን በስፍራው ለሚገኙ መገናኛ ብዙኃን ገልጻለች።

የኢትዮጵያን ሰንደቅ አላማ ከፍ አድርገው ያሳዩ ጀግና አትሌቶችም ክብር ይገባቸዋል፤ አጠቃላይ የቡድን ሥራውም ጠንካራ ነው ስትል ተናግራለች።

ይህን የዘላለም ሐውልት ከተከሉት ከእንቁዋ አትሌትና የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት ኮማንደር ደራርቱ ቱሉ አመራር አንስቶ አሰልጣኞችና የተለያዩ ባለሙያዎች በኢትዮጵያውያን ሲመሰገኑ ይኖራሉ። የኦሪገን የአትሌቲክስ ድግስ በመጪዎቹ ቀናት ሲቀጥል ኢትዮጵያ በተለያዩ ውድድሮች ተጨማሪ ድል ሊጠብቃት እንደሚችል ቢታመንም እስካሁን የተመዘገቡት ከበቂ በላይ ኢትዮጵያዊነት ተገልጦባቸዋል።

ለዚህም የማራቶን ባለድሎቹ ታምራት ቶላና ጎተይቶም ገብረሥላሴ፣ የአስር ሺ ሜትር የወርቅ ሜዳሊያ ባለቤቷ ለተሰንበት ግደይ፣ የማራቶን የብር ሜዳሊያ አሸናፊው ሞስነት ገረመው፣ የ3ሺ ሜትር መሰናክል የብር ሜዳሊያ ባለቤቱ ለሜቻ ግርማ፣የ1500 ሜትር ተመሳሳይ ሜዳሊያ ያጠለቀችው ጉዳፍ ፀጋይ እንዲሁም በተለያዩ ውድድሮች የሚችሉትን ሁሉ አድርገው ሜዳሊያ ማግኘት ያልሆነላቸው አትሌቶችም የዚሁ ዘመን የማይሸረው ታሪክ አካል ሆነው ይኖራሉ።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ስንተባበር ሁሌም እናሸንፋለን!

ኢትዮጵያውያን አንድነት መለያቸው፤ማሸነፍ ታሪካቸው ነው ። ኢትዮጵያውያን ሲተባበሩ የማይደረምሱት ተራራ፤ የማያሸንፉት ጠላት ፤የማይወጡት አቀበት አይኖርም ። ኢትዮጵያ ነጻነቷን አስከብራና የጥቁር ሕዝቦች መከታ ሆና የዘለቀችውም በዚሁ በሕዝቦቿ ትብብርና አንድነት ነው ።

ትላንት ኢትዮጵያውያን አድዋ ላይ ቅኝ ገዢዎችን አሳፍረው መልሰዋል ። በወቅቱ በመሪው አጼ ምኒሊክና በተለያዩ ሀገረ ገዢዎች መካከል አለመግባባትና ቅራኔ ቢኖርም ሁሉም ነገር ከሀገር በታች ነውና ልዩነቶቻቸውን ወደ ጎን ትተው ወራሪውን የጣሊያን ጦር በአንድነት ድል ነስተዋል ። በዚህም ኢትዮጵያን ከፍ አድርገዋል፤ ከዛም አልፎ የጥቁር ሕዝቦች ኩራት ሆነዋል ። አንድነት ኃይልም እንደሆነ ለቀሪው ዓለም የማይፋቅ ታሪክ ጽፈዋል ።

በኢትዮጵያ ያለውን ልዩነት ተጠቅሞ ኢትዮጵያን ለመውረር የተነሳው የፋሺስት ኃይል በኢትዮጵያን የተባበረ ክንድ ተደቁሶ ወደ መጣበት ከመመለሱም ባሻገር ኢትዮጵያውያን በውስጣቸው ልዩነት ቢኖርም ኢትዮጵያን ለማዋረድና ለመበታተን ለሚመጣ ኃይል ክፍተት እንደማይሰጡ ትምህርት ሆኗል ።

በተመሳሳይ መልኩም ተስፋፊው የሶማሌ ወራሪ ኃይልም በ1969 ዓ/ም አካባቢ ኢትዮጵያ ተዳክማለች በሚል ስሁት ዕሳቤ እስከ ድሬዳዋ ድረስ ዘልቆ በኢትዮጵያ ላይ ወረራ ፈጽሟል ። በወቅቱ ገና በሁለት እግሩ ያልቆመውን የደርግ መንግሥት በቀላሉ አሸንፈዋለሁ በሚል ቀቢጸ ተስፋና የኢትዮጵያውያንም አንድነት ላልቷል በሚል ምኞት በዚያድ ባሬ የሚመራው የሶማሌ መንግሥት ታላቋን ሶማሊያ እመሰርታለሁ በሚል ቅዠት ኢትዮጵያን ለመውረር ቢነሳም ሶስት ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ኢትዮጵያውያን ከጫፍ እስከ ጫፍ በመትመም ወራሪውን ኃይል አሳፍረው መልሰውታል ።

ኢትዮጵያውያን በተባበረ ክንድ በየጊዜው የሚነሱ ወራሪዎችን ድል ነስተው ከማባረራቸውም ባሻገር ሀገራቸውን በሚያሻግሩ ልማቶችም ላይ በጋራ የመረባረብ ድንቅ ታሪክ አላቸው ። የኢትዮጵያውያን የዘመናት ትልም የሆነው የህዳሴ ግድብ ለዚህ አንዱ ማሳያ ነው ። በአንዳንድ የውጭ ኃይሎች ሴራ ለዘመናት በከንቱ ሲፈስ የቆየውን የዓባይ ግድብ በመገደብ ኢትዮጵያውያን በጋራ ክንዳቸው ዛሬ ለብርሃን አብቅተውታል ። በተባበረ ክንድም ለዘመናት የተበተቡንን ገመዶች በመበጣጠስ ‹‹የአይቻልምን›› ዕሳቤን ወደ ‹‹ይቻላል›› መንፈስ ቀይረውታል ።

ኢትዮጵያ ከውጭ ወራሪዎች ባሻገር የውስጥ ባንዳዎችም በየጊዜው እየተነሱ ሀገሪቱን ለማዳከምና ለማፈራረስ ቢሞክሩም በኢትዮጵያውያን የተባበረ ክንድ እየተደቆሱ ምኞታቸው ጉም ሆኖ ቀርቷል ።ለሃያ ሰባት ዓመታት ኢትዮጵያን ሲያስተዳደር የቆየውና በሂደትም ሀገሪቱን ለማዳከምና ለማፈራረስ ሲሠራ የቆየው አሸባሪው የወያኔ ቡድን በኢትዮጵያውያን የተባበረ ክንድ ተመትቶ ከነሴራው ጥጉን ይዟል ። ከአራት ኪሎ ቤተ መንግሥት በተባበረ ክንድ ስልጣኑን ያጣው አሸባሪው ቡድን መራራ ሽንፈት ተጎንጭቶ ኢትዮጵያን የማፈራረስ ሕልሙ እንደጤዛ በንኗል ።

ይሄው ደማቅ ታሪክ የመጻፍ ሂደት ቀጥሎ ዛሬ ኢትዮጵያውያን አዲስ ታሪክ መጻፍ ጀምረዋል ። ለዘመናት የተዘራውን የጥላቻ አረም እየነቀሉ በምትኩ የአንድነትና የኅብረት ችግኝ በመትከል ላይ ይገኛሉ ። ጥላቻን የመንቀል፤ ፍቅርን የመትከል ተምሳሌት የሆነውን የአረንጓዴ አሻራ መርሐ ግብር ይፋ በማድረግም በአራት ዓመታት ውስጥ ከ20 ቢሊዮን በላይ ችግኞችን መትከል ችለዋል ። ኢትዮጵያውያን ሲተባበሩ ታሪክ ይሠራሉና በአንድ ቀን ከ350 ሚሊዮን በላይ ችግኞችን በመትከል በዓለም አቀፍ መድረክ ግንባር ቀደም መሆን መቻላቸውም የቅርብ ጊዜ ትውስታ ነው ።

ዛሬም ኢትዮጵያውያን ዓለምን ማስደመማቸውን ቀጥለዋል ። በኦሪጎን እየተካሄደ ባለው በ18ኛው የዓለም አቀፍ አትሌቲክስ ውድድር ላይ በመሳተፍ ከሁሉም ማዕዘናት የተውጣጡ ዜጎች ኢትዮጵያን አድምቀዋታል ። የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማም በዓለም መድረክ ከፍ ብሎ ተውለብልቧል ። በ10ሺ ሜትር የሴቶች ሩጫ ለተሰንበት ግደይና ጓደኞቿ ያደረጉት የቡድን ሥራ ኢትዮጵያን ለወርቅ አብቅቷታል ።በወንዶች ማራቶን ታምራት ቶላና ሞስነት ገረመው ሀገራቸውን ወርቅና ብር አልብሰዋታል ። በሴቶች ማራቶን ጎይተቶም ገብረስላሴና ጓደኞቿ ተቀናጅተው ኢትዮጵያ በዓለም መድረክ በወርቅ እንድትደምቅ አድርገዋታል ። በጉዳፍ ጸጋዬና ግርማ ለሜቻ የተገኙ የብር ሜዳሊያዎችም የኢትዮጵያ ድምቀትና ውበት ሆነዋል።

ይህ ድል ኅብረ ብሔራዊ ነው ። የውጭ ጠላቶች ተላላኪ የሆኑ ባንዳዎች ኢትዮጵያን በብሔርና በሃይማኖት ከፋፍለው ሊያዳክሟት ቢሞክሩም ኢትዮጵያዊነት ረቂቅ ነውና ይበልጡኑ እያበበና እየጎመራ መጥቷል ። በጠቢባን እንደበት ሲነገር የቆየው የኢትዮጵያዊነት ጥልቅ መንፈስም ዛሬ በ18ኛው የዓለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና ጉልህና ደማቅ ሆኖ ተንጸባርቋል!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - - 011-156-98-73

ፋክስ 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


**ነፃ ሃሳብ**

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

# ሕግ የማስከበሩ ሂደት በየዘርፉ ተጠናክሮ ቢቀጥል

ስምስም መንግሥቱ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጋራ መኖሪያ ቤት የዕጣ ዕድለኞችን ከሰው ንክኪ ነጻ በሆነ የዕጣ አወጣጥ ይፋ ካደረገ ማግሥት ጀምሮ በየማኅበራዊ ድረ ገጹ በዕጣ አወጣጡ ላይ የዕጣው ኢ-ፍትሐዊነት ሲገለጽና በከተማ አስተዳደሩ ላይ ስድብ አዘል ነቀፌታዎች ሲቀርቡ እንደነበር አስተውለናል ።

ቅሬታው መነሻ ሆኖ ይሁን የከተማ አስተዳደሩ በራሱ ጥረት ጉዳዩን ደርሶበት በአጭር ጊዜ ውስጥ ጠንከር ያለ እርምጃ ወስዶ ፍትሐዊነትን ለማስፈን ሞክሯል። ዕጣውንም መሰረዙን ይፋ አድርጓል ። ይቅርታም ጠይቋል። ኢፍትሐዊነት የጎደለው አሠራርንና በደል አድራሾችን ማጋለጥ፣በደል የደረሰባቸውም የፍትሕ ያለ እንዳሉ መቅረታቸው የተለመደ ተደርጎ በሚወሰድበት በዚህ ወቅት ፍትሕ ብትቀጥንም አትበጠስም የሚለውን ለማየት ተችሏል ።

አሁንም በጉዳዩ ላይ ብዙ ማጣራትና ሕዝብ ጆሮ መድረስ ያለባቸው ተግባራት ከከተማ አስተዳደሩ የሚጠበቅ ቢሆንም ከእለት ጉርሳቸው ቆጥበው ነገ የቤት ባለቤት ለመሆን በጉጉት ሲጠባበቁ ከነበሩ ዜጎች ላይ ነጥቀው ለመውሰድ አሰፍስፈው በነበሩት ላይ እርምጃ መወሰዱ በመልካም እየተወሰደ ቢሆንም እርምጃው በቀማኞቹ የሴፍትዌር ባለሙያዎችና የሥራ አመራሮች ብቻ ሳይሆኑ በማይገባ መንገድ የማይገባቸውን ቤት ለማግኘት የሞከሩትንም ተጠያቂ ማድረግ ያስፈልጋል ።

ባልተገባ መንገድ ለማይገባቸው ሰዎች ቤቱን ለማስተላለፍ በማጭበርበር ተግባር ላይ ተሳትፈዋል ተብለው ስማቸው ከነፎቶግራፋቸው ይፋ የተደረጉ ተጠርጣሪዎች ጉዳይ በብዙዎች በአዎንታዊ ጎኑ የታየ ነው ። እንዲህ ያለው እርምጃ በተመሳሳይ በማጭበርበር ወንጀል ውስጥ ለመሳተፍ የሚንቀሳቀሱትን ብቻ ሳይሆን፣ለሚያስቡትም ጭምር ትልቅ ማስተማሪያ ሊሆን ይችላል የሚል ሀሳብ አለኝ ።

እነዚህ በማጭበርበር ወንጀል ላይ የተሳተፉት ሙያተኞችና ኃላፊዎች መንግሥት አምኖባቸው የሰጣቸውን ሥራ አለመወጣት ብቻ ሳይሆን፣ እንዲያገለግላቸው ግብር ከፍሎ ባስተማራቸው ሕዝብ ላይም ነው ክህደት የፈጸሙት ።ያሳደጋቸውን ቤተሰብም አንገት የሚያስደፋ ድርጊት ነው ያከናወኑት ። ልጅ ወልደው ቤተሰብ ያፈሩ ከሆኑም በእነርሱ እንዲኮራ አላደረጉትም ። የሥራ ኃላፊነቱን ሲረከቡ ብቻ ሳይሆን ትምህርታቸውን ሲያጠናቅቁ በቅንነትና በታማኝነት ሕዝብ ለማገልገል ቃል ገብተዋል ። ግን ለቃላቸው ታማኝ ሆነው አልተገኙም ። ይህ ሁሉ ንዋየ አፍቅሮት ያመጣው መዘዝ ነው ።

ከሁሉም አሳሳቢው በማጭበርበር ሂደት ውስጥ ተመሳሳይ ፍላጎት ያላቸው ባለሙያዎችና የሥራ ኃላፊዎች በመንግሥት መዋቅር ውስጥ በዚህ ደረጃ መኖራቸው እጅግ አስደንጋጭ ነው ።ይሄ የሞራል ዝቅጠቱ የደረሰበት አንዱ ማሳያ ነው ።ችግሩ ወደቤተሰብ አስተዳደግና ትምህርት ቤቶችም መሔዱ አይቀርም ።የሕዝብ አገልጋይና ሰብዓዊነት የሚሰማቸው ዜጎች በማፍራት ረገድ ቤተሰብና ትምህርት ቤት ሚናቸው ከፍ ያለ ነው ።በተለይ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚቋቋሙ እንደስካውት ያሉ ሥነ ምግባርን በማነጽ ሚናቸው የጎላ እንደነበር ይታወሳል ።

በኋላም የሥነ ዜጋ የትምህርት ክፍለ ጊዜም ነበር ።ይህ ሁሉ ሀገርን የሚያገለግሉ ዜጎች ለማፍራት የሚያስችል አንዱ መንገድ እንደነበርም በትምህርት ቤት ያለፈ ሁሉ የሚያውቀው ነው ።‹‹አሳዳጊ የበደለው››የሚል ስድብ የቤተሰብ ስብዕናን የሚነካ በመሆኑ ስማቸውን በመልካም ለማስጠራት በልጆቻቸው ላይ ብዙ የሚደክሙ ወላጆች መኖራቸውም አይዘነጋም ።

ለክብሩና ለስሙ የሚጨነቅ፣ከራሱ ይልቅ ሌላውን የሚያስቀድም ጥሩ የሆነ የኢትዮጵያዊ መገለጫ ያለው ማኅበረሰብ የበዛበት እንደነበርም ከቃል ባለፈ በተግባር ይታወቃል ። አሁን ላይ የሚስተዋለውና የሚሰማው ‹‹ሲሾም ያልበላ ሲሻር ይቆጨዋል›› ከሚባለውም በላይ የሆነ ድፍረትና ጭካኔ እየታየ ነው ።የመጣው ይምጣ ብሎ ማስለቀስና ማሳዘን እየተለመደ ነው ።

መንግሥት ደሀውንና ዝቅተኛውን ማኅበረሰብ ተጠቃሚ ለማድረግ ብሎ የጀመረው የቤት ልማት ፕሮግራም በግንባታ ጥራት፣ በሚገነባው ቤት ብዛት፣ቤት ማስተላለፍ በውስብስብ ችግር ውስጥ አልፎ እዚህ የደረሰ ነው ። አሁን ላይ በተደራጀ አሠራር በዕጣ አወጣጥ ላይ የተፈጠረው ችግር ለየት ያለ ቢመስል አንድ ሀገራዊ የሥነ ምግባር ችግር መገለጫ ነው ።ችግሩ ተደርሶበት እርምጃ መወሰዱ አንድ ነገር ቢሆንም ቅድመ ጥንቃቄ ላይ ተገቢው ሥራ እንዳልተሠራ አመላካች ነገሮች አሉ ።

የቤት ጥያቄ ሰፊ በሆነበትና ሳይደክሙ ቤት በመሸጥና በመለወጥ ሀብት ያካበቱ የአየር ባየር ነጋዴዎች በበዙበት በዚህ ወቅት ማጭበርበር እንደሚኖር መታወቅ ነበረበት ።ዛሬ በየምንኖርበት አካባቢ ይህ ነው የሚባል የመንግሥትም ሆነ የግል የሆነ ሥራ የሌላቸው ቤትና መሬት በመሸጥና በመለወጥ በሀብት የማይወዳደራቸው የሆኑ ሰዎች እያየን ነው ።

በጣም የሚገርመው ደግሞ ማን እንደነበሩ የሚያውቃቸውን ሕዝብ እንኳን የሚያከብሩ አይደሉም ። ጥቅም አሳዳጆች ናቸው ። የሚሸጡት ቦታም የሚያውቁት አካባቢ በመሆኑ የወረዳውንና የክፍለ ከተማውን አስተዳደር በቀላሉ ነው የሚይዙት ። በገንዘብ ኃይል የነዋሪ መግቢያና መውጫ ሳይቀር በመሸጥ ዓይኔን ግንባር ያድርገው ብለው ሕዝብ የሚያሳዝኑ መኖራቸው በግልጽ ይታወቃል ።

በፍትሕ ቢጠየቁ እንኳን ገንዘብ ስላላቸው የሚያሸንፋቸው የለም ። የከተማ አስተዳደሩ የልብስ መሸጫ ሱቅ የቸገረው ይመስል ክፍት ቦታዎች ሁሉ ተሸንሽነው ሱቅ የተሠራባቸው ጥቂት የማይባሉ አካባቢዎች በመዲናዋ ውስጥ ይገኛሉ ።የከተማ አስተዳደሩ በ14ኛው ዙር የጋራ መኖሪያ ቤት እጣ አወጣጥ ላይ የወሰደውን ፈጣን እርምጃ በተመሳሳይ በየክፍለ ከተማውና ወረዳ ውስጥ ያለውን የመሬት ልማት አስተዳደር ይፈትሽና የሕግ ማስከበር ሥራውን ያጠናክር ።

መውጫ መግቢያቸው ተዘግቶባቸው፣የንግድ ቦታቸውና የመኖሪያ ቤታቸው ፈርሶባቸው ከንቲባዋን በየት በኩል አግኝተናቸው ድምጻችንን እናሰማ የሚሉ ዜጎች በየአካባቢው ስላሉ አጠቃላይ በከተማዋ ያሉ ሕገወጥ ተግባራትን ለማስቆም በቂ ትኩረት ሰጥቶ መንቀሳቀስ ተገቢ ነው ። ሕገ ወጦችን ወደ ሕግ የማቅረቡ ሂደት የአንድ ሰሞን ጩኸት እንዳይሆን አበክሮ መሥራት ያስፈልጋል ።

የከተማ አስተዳደሩ የዘጠኝ ወር የሥራ አፈጻጸሙን በገመገመበት ወቅት የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ተገኝተው ‹‹በሾፌር በር ተከፍቶለት በኮብራ መኪና የሚሄድ አመራር ሳይሆን በፒካፕ መኪና እየተዟዟረ ታች ወርዶ የሚሠራ ነው የሚያስፈልገው ።›› ማለታቸው ይታወሳል ። ከፍተኛው አመራር በየወረዳውና ክፍለ ከተማው ስርቆትን ማዕከል አድርጎ የሚሠራውንም ይዘው ለሕግ እንዲያቀርቡ ጭምር ነው በአፈጻጸም ግምገማው ላይ የተናገሩት ።

የከተማ አስተዳደሩ የጠቅላይ ሚኒስትሩን መልዕክት እየተገበረው ይሆን? የሚል ጥያቄ ቢኖርም፣በጋራ መኖሪያ ቤት የዕጣ አወጣጥ ላይ የተፈጠረውን ችግር ለማረም የወሰደውን እርምጃ አይነት በሌሎችም ይጠበቃል ። ቴክኖሎጂ ሰው ሰራሽ መሆኑ ተዘንግቶ ሙሉ ለሙሉ እምነት መጣሉ ሌላው ክፍተት ነው ።

ከሰው ንክኪ ነጻ የሆነው የዕጣ አወጣጡ እንኳ ቀድሞ የተሠራው ሥራ ላይ ክፍተት ስለመኖሩ አልታየም። ዛሬ ከባንክ ውስጥ ብር ለመዝረፍ የሚያግዝ ቴክኖሎጂ በተፈጠረበት ዘመን ቴክኖሎጂ በራሱ የሚሠራ አድርጎ መገመት የዋህነት ነው ።በዚህ ረገድም ትምህርት እንደሚወሰድበት ተስፋ አደርጋለሁ ።

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ተጠየቅ

## ‹‹ ከሕዝብ ጋር በተግባባንበት መንገድ ሕግ የማስከበር ሥራዎችና እንቅስቃሴዎች ተሠርተው በርካታ ውጤቶች ተመዝግበዋል ››

**- አቶ እንግዳው ጠገናው**
**የአማራ ክልል ሰላምና ፀጥታ ቢሮ ሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ**

**ክፍለዮሐንስ አንበርብር**



በዛሬው የ‹‹ተጠየቅ›› አምዳችን በአማራ ክልል ሕግ ለማስከበር የተሠራውን ሥራ፤ ስለ ክልሉ ሰላምና ደህንነት እንዲሁም አሁናዊ ሁኔታ በተጨማሪ ያሉ ቀጣይ ስጋቶችንና አማራጮች ፤ በተጨማሪም አማራ ክልል ከአጎራባች ክልሎችና ከፌደራል መንግሥት ጋር በጥምረት እየተገበሩት የሚገኘውን አጠቃላይ እንቅስቃሴ ክልላዊ፣ ሀገራዊ እና ቀጣናዊ ጉዳዮችን አንስተን የአማራ ክልል ሰላምና ፀጥታ ቢሮ የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ ከሆኑት አቶ እንግዳው ጠገናው ጋር ያደረግነውን ቃለመጠይቅ እንደሚከተለው ለንባብ አብቅተነዋል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- የክልሉን ሰላም አስተማማኝ ለማድረግ ምን እየተሠራ ነው?**

**አቶ እንግዳው፡-** በአሁኑ ወቅት በአማራ ክልል አንፃራዊ ሰላም አለ ብሎ መውሰድ ይቻላል ፡፡ ጠላት ካሰበው ፍላጎትና ዓላማ አንፃር በሕግ ማስከበር ሥራ ትልቅ ኪሣራ ደርሶበታል ፡፡ ኪሳራውም የውስጥና የውጭ ኃይሎች በተቀናጀ መንገድ የአማራ ክልልን ሕዝብና አመራር ለዳግም መከራ፣ ስቃይና ስደት ለመዳረግ ውስጥ ለውስጥ ከኢ-መደበኛ ኃይሎች፣ ከቅማንት ጽንፈኛ ኃይሎች፣ ከጉሙዝ አማፅያን እና ከአሸባሪው ሸኔ ጋር በተቀናጀ መንገድ ውጭ ካሉ ጠላቶቻችን ጋር ተሳስረው የክልሉ ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ወደ ኋላ ለመመለስ ከፍተኛ እንቅስቃሴ ሲያደርጉ ነበር ፡፡ ስለዚህ የሕዝባችን እና የክልሉ መንግሥት በተለይም ሕዝባችን ሕግ ይከበርልን ጥያቄ በሰፊው አንስተዋል ፡፡

በጦርነቱ ማግስት በጦርነት የተሳተፈውም ያልተሳተፈውም በተቀላቀለ መንገድ ዘምቻለሁ በሚል እራሱን እንደጀብደኛ በመቁጠር በአመራሩ እና በሕዝባችን ላይ ብዙ ሕገ-ወጥ ድርጊት ለመፈፀም ጥረት አድርጓል ፡፡ ስለዚህ ይህንን ለመመከት ከሕዝባችን ጋር ባደረግነው ውይይት የመንግሥት አንዱና ዋነኛ ማሳያው ሕግ ማስከበር በመሆኑ ከሕዝብ ጋር በተግባባንበት መንገድ ሕግ የማስከበር ሥራዎችና እንቅስቃሴዎች ተሠርተው በርካታ ውጤቶች ተመዝግበዋል ፡፡ የተፈናቀሉ ዜጎች ወደቀያቸው ተመልሰዋል ፡፡ የሕዝቡ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ከዚህ በፊት ከነበሩበት የፀጥታ ስጋት ወጥቶ ወደ የተረጋጋ ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ለመግባት ጥረት ተደርጓል ፡፡

የተጀመሩ የልማት እንቅስቃሴዎች ለማከናወን በሚደረገው ጥረት ሕገ ወጥ ኃይሉ የመንግሥትን ሚና በመቀማት ባለሃብቶችን የሚያስፈራራበት፤ የተጀመሩ የልማት ሥራዎች እንዲቆሙ መኪና የሚያስቆምበት፣ ኬላ አስቀምጦ ግብር የሚያስከፍልበት ሁኔታዎች ነበሩ፡፡ እነዚህን ሕገወጥ እንቅስቃሴዎች ማስቆም ተችሏል ፡፡ ሕገ ወጦችን ለመቆጣጠርና የሕግ የበላይነትን ለማስፈን አስችሏል ፡፡ ይህ አንዱ ትልቅ ስኬት ነው ፡፡ ስለዚህ ሕዝብና መንግሥትን ያገናኘ ትልቅ የሰላም ድልድይ ለመገንባት ጥረት ተደርጓል ማለት ነው ፡፡

ጠላት ከድንበር ላይ ሆኜ ከምዋጋ ውስጥ ሆኜ ማፍረስ እችላለሁ የሚለው ሃሳቡ ከሽፏል ፡፡ ከዚህ አኳያ የሕግ ማስከበር ዘመቻው እጅግ ስኬታማ ነበር ማለት እንችላለን ፡፡ በዚህም አልሳካ ሲለው ደግሞ ከሌሎች ኃይሎች ጋር ተደራጅቶ እና ተሳስሮ በወለጋ የተፈፀመውን የዜጎች ጭፍጨፋ መሠረት አድርጎ የኦሮሚያ እና አማራ ክልል ዜጎችን እርስ በእርስ ለማጋጨትና ግንኙነትን ለማላላት እንዲሁም ሀገር ለማፍረስ ከፍተኛ እንቅስቃሴ ባደረገበት ልክ፤ ዜጎች ተገደሉ ተብሎ መጮህ ነበር ፡፡ ይህን ሲያደርግ የነበረው እራሱ ጠላት ነው ፡፡ ይህም ‹‹ራሱ ገርፎ ራሱ ይጮኻል›› የሚሉት ቢጤ ነው ፡፡

ጭፍጨፋው የአማራንም ሆነ የኦሮሞ ሕዝብን በአጠቃላይ የሰው ልጅ የሆነውን ሁሉ ያሳዘነ ነው ፡፡ ነገር ግን ይህ ታስቦበት ሆን ተብሎ የተደረገ ነው ፡፡ ይህንን ሁላችንም እናውቃለን ፡፡ ነገር ግን ግድያው እናወግዛለን በሚል በዩኒቨርሲቲዎች፣ በመንግሥት ተቋማትና በኅብረተሰቡ ከፍተኛ የተቃውሞ እንቅስቃሴ አድርገው ነበር ፡፡ በሰላማዊ መንገድ ወጥቶ የተፈፀመውን ድርጊት ማውገዝ ትክክል ነው፡፡ ይህ አንዱ ሰብዓዊ መብት ማሳያ ነው ፡፡ ዜጎች ባልመሰላቸውና ቅር በተሰኙባቸው ጉዳዮች ላይ ቅሬታ ማሰማታቸው ችግር የለውም ፡፡ ነገር ግን ውስጡ የተቀመመው ቅመም ሕገ-ወጥ የሆነው ሰልፍ በሚካሄድበት ጊዜ የሽብር ጥቃቶችን ለመፈፀም፣ መንግሥትን ለመገልበጥም ጭምር ‹‹ሞብላይዝድ›› የተደረገ ነው ፡፡ ስለዚህ ይህ አንዱ ትልቅ ችግር እንደሆነ ተገምግሞ በሰላማዊ መንገድ ወጥተን ከምናሰማው ድምፅ በላይ ሌሎች ሊፈጽሙት የተዘጋጁት ችግር በሚዛን ደረጃ ሲታይ ሰልፉ እንደ አንድ መልካም አጋጣሚ መውሰድ ይቻላል ፡፡

ዜጎችን ሰልፍ መከልከል ሊያሳድረው የሚችለው ተፅዕኖ፤ ውስጥ ላይ ያደራጇቸውና የላኳቸው ኃይሎች እንቅስቃሴ ጭራሽ ሰላማዊ ሰልፍን ሳይሆን ሕዝብ ከሕዝብ እንዲጫረስ ለማነሳሳት የታሰበበት ነበር ፡፡ በመሆኑም በአንድ በኩል ጠላት ያሰበውን አጀንዳ እያከሸፍን በቀጣይ ደግሞ ከሕዝባችን ጋር እየተወያየን ለመግባባት ተሞክሯል ፡፡ በአጠቃላይ በክልሉ ሆነ ከክልሉ ውጭ የሚደረጉ የተለያዩ ትንኮሳዎችን ማክሸፍ ተችሏል የሚለው ጉልህ ነጥብ ተደርጎ መወሰድ አለበት፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ሰልፎቹ ሕጋዊ ፈቃድ አልነበራቸውም ?**

**አቶ እንግዳው፡-** አልነበራቸውም! ዜጎች ሕጋዊ ሆነውና መብታቸው ተጠቅመው መግለጽ እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ ነገሮች ባልተረጋጉበት ወቅት፤ ስጋት ባልቀነሰበት ነባራዊ ሁኔታ ውስጥ ሆነን ሰልፉን ሲዘውሩት የነበሩት ጠላቶች ነበሩ ፡፡ ስለዚህ ሰልፉ ሕጋዊ አልነበረም፤ የትም ቦታ ላይ አልተፈቀደም ፡፡ የተፈለገው ሰላማዊ ሰልፉ በሰላም ሳይሆን ሕገወጥ በሆነ መንገድ እንዲካሄድ ነበር ፡፡ ሰልፍ አደርጋለሁ እና ሰልፍ አታደርግም በሚለው ኃይል መካከል በተለይም በፀጥታ ኃይሉ እና በኅብረተሰቡ መካከል ግጭት በማስነሳትና ንብረትን በማውደም ተቋማትን ለመምታት የታሰበበት ነበር ፡፡ ስለዚህ የሚጠራው ሰልፍ ሕጋዊ አለመሆን አንዱ ስጋት ነበር ፡፡ ይሁንና አንዱ መሰናክል ሲገጥመን ሌላውን በጥበብ ለማለፍ ጥረት ተደርጓል ፡፡

**እኛ እየተወጋን ያለነው ከአሸባሪው ሸኔ፤ ከጉሙዝ አማፂ ቡድን፣ ከቅማንት ፅንፈኛ ቡድን እና ኢ-መደበኛ ኃይሎች ጋር ብቻ አይደለም፡፡ ጠላት በተዘዋዋሪ መንገድ የገዛቸው፤ ያደራጃቸው አፍራሽ ኃይሎችና ተላላኪዎችም ጋር ነው ፡፡ እነዚህ ኃይሎች ከፊት ለፊት ይኑሩ እንጂ ከኋላ የገንዘብ ድጋፍ የሚያደርጉ፣ በማኅበራዊ ሚዲያም የመንግሥትን ሥራ የሚያብጠለጥሉት የውጭ ኃይሎችና ሕወሓት መሆኑ መታወቅ አለበት**

ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ጋር በጋራ በተሠራ ሥራም እጅግ በርካታ ሕገ ወጥ ኃይሎችን በመቆጣጠር ሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነትን ለማጠናከር የተሠራው ሥራ አንዱ መልካም ነገር ነበር ፡፡ ስለዚህ ጠላት በከፈተው አጀንዳ ሳይሆን በልማትና በሕዝባዊ ትስስሮች የጠላትን አጀንዳ ማክሸፍ ላይ በመሠራቱ በርካታ የተፈናቀሉ ዜጎች ወደቀያቸው ተመልሰው ወደ እርሻቸው ገብተዋል ፡፡

የጉሙዝ የኅብረተሰብ ክፍሎችም ‹‹የአማራ ኢ-መደበኛ ኃይል ሊያጠቃህ›› ነው በሚል ወደጫካ የወሰዱትን የኅብረተሰብ ክፍል ሁሉ መመለስ ተችሏል፡፡ ሕዝብ በሰላማዊ መድረክና ውይይቶች ላይ እያለ ያለው ‹‹እኛ ተጣልተን አናውቅም፤ ይህን ያደረገን ጠላት ስለሆነ በጋራ ሆነን የምትገድሉንም ከሆነ ግደሉን ፡፡ ከዚህ ውጭ የአማራ ሕዝብ ወንድማችን ነው፤ የጉሙዝ ሕዝብ ወንድማችን ነው፤ የሺናሻ ሕዝብ ወንድማችን ነው›› ብሏል ፡፡ ከዚህ በኋላ የጠላት አጀንዳ ማራገፊያ ሳንሆን የልማትና ማኅበራዊ ትስስር መሠረት ነን በሚል በዚያ መንገድ እየተሠራ ነው ፡፡ በመሆኑም ብዙ መልካም ነገሮች እንዳሉ ማወቅ ይገባል ፡፡

ከአፋር ክልል ጋርም ያካሄድናቸው በርካታ መድረኮች አሉ ፡፡ የተደረሰበት ድምዳሜ መሰናክሎችን በጋራ እንዴት እንለፋቸው የሚል ሲሆን ውይይቱ መሬት እየነካ ነው ፡፡ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ የፀጥታ ስጋት በነበረባቸው አካባቢዎች ላይ የአመራር ለአመራር እና የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት ተጠናክሮ ቀጥሏል ፡፡ ስለዚህ ሕግ የማስከበር ሥራው በዘመቻ ሳይሆን ተቋማዊ ሆኖ በየአካባቢው የሚፈጠሩ የፀጥታ ስጋቶችን በአካባቢ ያለው የጸጥታ መዋቅር በራሱ አቅም ማስተካከል የሚችልበት ሁኔታ እየተፈጠረ ነው፡፡ ስለዚህ ተቋማዊ ግንባታችን ተጠናክሮ ይቀጥላል ፡፡ ሕግ የማስከበር እንቅስቃሴያችንም ዕውን ይሆናል ፡፡ ይህም ቀጣይነት ባለው መንገድ እየተሠራ ነው ፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ሕግ በማስከበር ዘመቻው ‹‹ኢ-መደበኛ ኃይሎች›› የተባሉት የቂም በቀል ሥራ ነው በማለት ሕዝብን ለማነሳሳት ይጠቀሙበታል ይባላል ፡፡ የክልሉ ግምገማ በዚህ ላይ ምን ይላል?**

**አቶ እንግዳው፡-** ከሕዝብ በላይ የሕግ ይከበርልን የሚለውን ጥያቄ ያቀረበ የለም ፡፡ በእያንዳንዱ መድረክ ተወያይተናል ፡፡ ከ6 ነጥብ 2 ሚሊዮን ሕዝብ በላይ አግኝተናል ፡፡ በሁሉም መድረኮች ላይ የሕግ የበላይነት እንዲከበር ሕዝብ ጠይቋል ፡፡ ምክንያቱም ወጥቶ መግባት አይቻልም፤ ከቦታ ቦታ መንቀሳቀስ አይቻልም፤ በራስ ንብረት ማዘዝ አይቻልም፤ ባለሀብት ዘንድ ተደውሎ በሚሊዮን ብር ይጠየቅ ነበር ፡፡

**አዲስ ዘመን፡-እውነት ብር የተጠየቁ ባለሃብቶች ‹ተጠይቀናል› ብለው ለእናንተ መረጃ ሰጥተዋል?**

**አቶ እንግዳው፡-** እንዴ! በሕዝብ መድረካችን ሕግን በትክክል ማስከበር ከቻላችሁ እኛ እስከ ሕይወት መስዋዕት እንከፍላለን ፡፡ ሌባውን እና አጭበርባሪውን በትክክል አውጥተን መስጠት እንችላለን የሚለው ሕዝብ ቀላል አልነበረም ፡፡ ስለዚህ በጥፋት ላይ የተሰለፉ በሕግ የሚፈለጉ፤ ከማረሚያ ቤት ያመለጡና ውሳኔ ያረፈባቸውን በርካታ ኃይሎችን በቁጥጥር ሥር ማዋል ተችሏል ፡፡ የተረጋጋ ሁኔታ ከተፈጠረ እና የሕግ የበላይነት ካለ በፈፀሙት ድርጊትና ወንጀል መጠየቅ የማይቀር ስለሆነ ይህ ኃይል ይረብሻል ፡፡ ስለዚህ ይህን ኃይል መቆጣጠር ተችሏል ፡፡ በመሆኑም ለቂም በቀል ነው የሚለው አግባብ አይደለም ፡፡ ከፌደራል

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ተጠየቅ

መንግሥትና ከሌሎች ፀጥታ መዋቅሮች ጋር ለማጋጨት የሚደረግ የጠላት ሴራና የግለሰቦች ፍላጎት ነው ።

ኢ-መደበኛ አደረጃጀት የምንለው የፋኖ ሥም ይዞ ነገር ግን የፋኖን ምግባር እና ተግባር ያልያዘና ያልተላበሰ ሌባ፣ ዘራፊ ነው ። በመሆኑም ሕዝቡ ሕግ ይከበርልን እያለ ቂም በቀል ነው ማለት የሚጣረስ ሃሳብ ነው ።

**አዲስ ዘመን፡- የክልሉን ሰላም ለማስከበር የፌደራል መንግሥት በእጅጉ ጣልቃ ገብቷል የሚል ወቀሳም ይሰማል ። እርስዎ ምን ይላሉ?**

**አቶ እንግዳው፡-** እኛ ሕግ እያስከበርን ያለነው በራሳችን ኃይል ነው ። ሕግ እያስከበርን ያለነው በራሳችን ልዩ ኃይል፣ በራሳችን ሚሊሻ፣ ፖሊስና እና በራሳችን ፀጥታ መዋቅር ነው ። ስለዚህ የፌደራል መንግሥት ጣልቃ እየገባ ነው የሚለው በአንድ የፌደራል ሥርዓት ውስጥ እስከተዳደርን ድረስ የፌደራል መንግሥት ከክልል መንግሥት ጋር ሆነው በቅርበት ይሠራሉ ። በዋናነት ግን የችግሩም ሆነ የፀጥታው ባለቤት የክልሉ ሕዝብ እና መንግሥት ነው ። ሆኖም ሕግን የማስከበር ሥራዎች በቅንጅት የሚሠሩ ናቸው ። ሌላው ቀርቶ ከጎረቤት ሀገራትም ጋር በጋራ የፀጥታ ሥራዎች ላይ በትብብር ይሠራል ።

ዓለም አንድ መንደር እየሆነች ባለችበት ወቅት በጋራ በሚሠራበት ሁኔታ ፌደራል መንግሥት በክልሉ ጉዳይ ጣልቃ ገብቷል የሚለው ወቀሳ ውሃ የሚያነሳ አይደለም። በአጠቃላይ እኛ ሕግ እያስከበርን ያለነው በራሳችን የፀጥታ መዋቅርና አደረጃጀት ነው ። ነገር ግን እንደ አመራር፤ የአመራር ድጋፍ እንደሚኖር መታሰብ አለበት። ምክንያቱም ዋነኛ አጀንዳ ተደርጎ የተወሰደው አማራ ክልልን ማፍረስ ከተቻለ፤ ኢትዮጵያን ማፍረስ ይቻላል የሚል ነው ። ይህ የጠላት ዓላማ ነው ። ምክንያቱም ለሕገ-ወጥ ኃይሉ እና ሕወሓት ላስታጠቃቸው የውስጥ ጠላቶች በዋናነት የአማራ ክልልን ማፍረስ ከተቻለ የፌደራል መንግሥትን መቆጣጠር ይቻላል የሚል ሕልምና ዓላማ ነው ያለው ። ይህንን በጋራ ተባብሮ መስመር ማስያዝ የፌደራል መንግሥትም ጉዳይ ነው ።

እኛ እየተወጋን ያለነው ከአሸባሪው ሸኔ፤ ከጉሙዝ አማፂ ቡድን፣ ከቅማንት ፅንፈኛ ቡድን እና ኢ-መደበኛ ኃይሎች ጋር ብቻ አይደለም ። ጠላት በተዘዋዋሪ መንገድ የገዛቸው፤ ያደራጃቸው አፍራሽ ኃይሎችና ተላላኪዎችም ጋር ነው ። እነዚህ ኃይሎች ከፊት ለፊት ይኑሩ እንጂ ከኋላ የገንዘብ ድጋፍ የሚያደርጉ፣ በማኅበራዊ ሚዲያም የመንግሥትን ሥራ የሚያብጠለጥሉት የውጭ ኃይሎችና ሕወሓት መሆኑ መታወቅ አለበት ። ሕወሓት የአማራ ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያም ጠላት ነው ። በመሆኑም በጋራ ጠላት ላይ የፌደራል መንግሥትም እንደሚመለከተው መግባባት ያስፈልጋል ።

**አዲስ ዘመን፡- የሱዳን በአማራ ክልል አዋሳኝ ላይ የሚያደርገው ትንኮሳ፣ በወለጋ የአማራ ተወላጆች ጭፍጭፋ፣ የሕወሓት ዳግም ትንኮሳ፣ የኢ-መደበኛ ኃይሎች መግነን ከታላቁ ህዳሴ ግድብ ሦስተኛ ዙር የውሃ ሙሌት ወቅት ጋር መያያዙ አንድምታው ምንድነው?**

**አቶ እንግዳው፡-** እነዚህ ኃይሎች ተጠናክረው እየሠሩ ያሉት ከምዕራባውያን እና ግብጽ ከምታስታጥቃቸው ኃይሎች ጋር በተቀናጀ መንገድ ነው። የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ሦስተኛ ዙር የውሃ ሙሌት ማለት ኢትዮጵያ ወደ ከፍታ የምትሻገርበት አንዱና ዋነኛ መሠረት ነው ። ስለዚህ ይህን ማደናቀፍ ማለት የፌደራሉንም ሆነ የክልሉን መንግሥት ውጥረት ውስጥ በማስገባት የተጀመረው ልማት እንዳይጠናቀቅ ማድረግ ነው ።

ክልሎችን እርስ በእርስ በማጋጨት ዓላማችን ማሳካት እንችላለን የሚል ነው ። የህዳሴ ግድብን ማስተጓጎል ማለት ወይንም አማራን ማፍረስ ኢትዮጵያን ከማፍረስ ጋር የተያያዘ ነው ። ሕወሓትም የሱዳንን ኮሪደር ለማስከፈት ከፍተኛ ጥረት እያደረገች ያለችበት ወቅት ነው ። ስለዚህ እነዚህ አንድ ላይ ተዳምረው ያለውን ፍላጎት ማወቅ ይገባል ።

የሚስተዋሉት ትንኮሳዎች ተራ የጥቅም ሽኩቻ አይደሉም ። የሚደረገው እንቅስቃሴ ጠላት ያሰለፋቸው በማኅበራዊ እንቅስቃሴ፤ በፖለቲካ ዘርፎች የተሰለፉ ኃይሎችን በመጠቀም ነው ። በመሆኑም የፌደራል እና የክልል መንግሥታት ከመቼውም በበለጠ ተጠናክረው ለመሥራት የሚገደዱበትና ጠላትን ለማሳፈር

**የተፈናቀሉ ዜጎች ወደቀያቸው ተመልሰዋል ። ሕዝቡ ከዚህ በፊት ከነበሩበት የፀጥታ ስጋት ወጥቶ ወደ ተረጋጋ ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ስመግባት ጥረት ተደርጓል ። የተጀመሩ የልማት እንቅስቃሴዎች ለማከናወን በሚደረገው ጥረት ሕገ ወጥ ኃይሉ የመንግሥትን ሚና በመቀማት ባለሃብቶችን የሚያስፈራራበት፤ የተጀመሩ የልማት ሥራዎች እንዲገቱ መኪና የሚያስቆምበት፣ ኬላ አስቀምጦ ግብር የሚያስከፍልበት ሁኔታዎች ነበሩ ። እነዚህን ሕገወጥ እንቅስቃሴዎች ማስቆም ተችሏል ። ሕገ ወጦችን ስመቆጣጠርና የሕግ የበላይነትን ለማስፈን አስችሏል ። ይህ አንዱ ትልቅ ስኬት ነው ።**

◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇

መስዋዕትነት የሚከፈል መሆኑን መገንዘብ ይገባል ።

ብዙ ትንኮሳዎች ቢኖሩም መንግሥት ለሰላም አማራጮች ቅድሚያ በመስጠት ብልህነት የተሞላው አካሄድ እየተከተለ መሆኑን ማወቅ አስፈላጊ ነው ። ከዚህም አለፍ ሲል ሕግን የማስከበር ጉዳይ የአንድ መንግሥት ቀዳሚ አጀንዳ ተደርጎ እየተሠራ ነው ። በየቦታው የሚታዩና ጥቃቅን የሚመስሉ፤ ነገር ግን ትስስር ያላቸው፤ የውስጥና የውጭ ኃይሎች በተናበበ ሁኔታ በገንዘባቸው በገዟቸው ኃይሎች አማካኝነት የበለጠ ውጥረት ለማንገስ፤ ‹‹ኮሪደር›› ለማስከፈት ያለመ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ የህዳሴውን ግድብ ሙሌት ለማስተጓጎል የሚደረግ ሲሆኑ እልፍ ሲልም ኢትዮጵያን የማፍረስ እንቅስቃሴ እየተደረገ መሆኑን ለየትኛውም አካል ግልፅ ነው ።

**አዲስ ዘመን፡- ‹ኢ-መደበኛ› በተባሉ ኃይሎች ላይ እርምጃ ከመወሰዱ በፊት በሰላማዊ መንገድ መወያየት ለምን አልተቻለም?**

**አቶ እንግዳው፡-** በመሠረቱ ኢ-መደበኛ ኃይሉን ተቆጣጥረናል ስንል የተወሰደው እርምጃ አይደለም። የአጥፊው ድርጊት እየታወቀ ቅድሚያ የተሰጠው የሰላም አማራጭ ነው ። ሰው እውቀት አለው፤ ገንዘብ አለው። መገደል የለበትም ። ሰው በራሱ ለሀገሪቱ ሃብት ነው ። ስለዚህ እጅ እንዲሰጡ የተደረገው በአብዛኛው በመስዋዕትነት ሳይሆን በሰላማዊ መንገድ ነው ። ይህ በጣም ትልቅ ነገር ነው ። የፀጥታ ኃይላችንም የመጀመሪያ ሥራው ከእነዚህ ኃይሎች ጋር መወያየት ነበር ። በድርጊታቸው ተፀፅተው መንግሥትን እና ሕዝብን ይቅርታ ጠይቀው ለተመለሱት የተለያዩ የአቅም ግንባታ ስልጠና ወስደው ወደማኅበረሰቡ ተቀላቅለዋል ።

በኢ-መደበኛ አደረጃጀት ውስጥ ዓላማው ሳይገባቸው እና ዓላማውን አውቀው የገቡበት አሉ ። በሌላ በኩል ደግሞ የኃይል ሚዛን እየተመለከቱ ከመሐል ሆነው የሚዋልሉ ኃይሎች አሉ ። በመሆኑም ለእነዚህ ትክክለኛውን የጠላትን ፍላጎትና እንቅስቃሴ በማስረዳት በሰላማዊ መንገድ ወደ ሕብረተሰቡ እንዲቀላቀሉ እና መደበኛ ሕይወታቸውን እንዲቀጥሉ ተደርጓል ።

ከእነዚህ ውጭ ያሉት ወደ 500 የሚሆኑት ከማረሚያ ቤቶች ያመለጡና ከዚህ በፊት ውሳኔ አርፎባቸው ጠላት በነበረባቸው አካባቢዎች እንዲወጡ የተደረጉ ነበሩ ። ስለዚህ እነዚህን ኃይሎች በሰላማዊ መንገድ ወደ ማረሚያ ቤት እንዲገቡ ተደርጓል ። ሦስተኛው በፍርድ ቤት ውሳኔ አርፎባቸው በማኅበረሰቡ ውስጥ ተደብቀው የሚኖሩ ግን በዚህ ወቅቱን እንደ አጋጣሚ በመጠቀም ከኢ-መደበኛ ኃይሎች ጋር ሆነው ፋኖ ነን ከሚሉት ውስጥ 500 በላይ የሚሆኑትን በቁጥጥር ስር ማዋል ተችሏል። በመሆኑም እነዚህ ኃይሎች ፋኖ ሊሆኑ አይችሉም ። ሰው የገደለ፤ የዘረፈ፤ ፀጥታ ኃይሉን ያሰናከለ መቼም ቢሆን ፋኖ ሊሆን አይችልም ። ነገር ግን ‹‹ፋኖ ››ነን የሚል ሽፋን ይጠቀማሉ ።

**አዲስ ዘመን፡- በክልሉ ተጠርጣሪዎችን ወደ ሕግ ለማቅረብ በሚደረገው ጥረት የሕግ ሂደቱን ያልተከተለና በዘፈቀደ የሚከናወን ነው የሚሉ ወቀሳዎች ይሰማሉ ። በዚህ ላይ ምን አስተያየት አለዎት?**

**አቶ እንግዳው፡-** የመጀመሪያው የሕግ የበላይነት ለማረጋገጥ የሚደረገው እንቅስቃሴ የዜጎችን ሰብዓዊ መብት ባከበረ መልኩ ነው ። ተጠርጣሪዎች የትኛው ማረሚያ ቤት እንዳሉ ይታወቅ ነበር፤ አሁንም የት እንዳሉ ይታወቃል ። የሚወራው ነገር ትክክል አይደለም። የሚያስጮኸው ጠላት ነው ። የሕገ ወጡ ክንፍ የሆነውና የማኅበራዊ መገናኛ ዘዴዎች የሚጠቀመው የሚያጯጩኸው ያ ኃይል ነው ።

መብታቸውን በጣሰ መንገድ አይደለም ። ነገር ግን ለፀጥታ ኃይሉ እጃቸውን በሰላም ለመስጠት ፈቃደኛ ያልሆኑና የኃይል ዕርምጃ የወሰዱት እንዲመቱ ተደርጓል። እያስከበርን ያለነው ሕግ ነው ። ሕግ ለማስከበር በሚደረገው ዘመቻ እስካሁን ከ27 በላይ የፀጥታ አካላት መስዋዕት ሆነዋል ።

ሕግን ለማስከበር መስዋዕት ለሚሆነው ኃይል የሚጮህለት አካል የለም ። ነገር ግን ሕገ ወጥ ሆኖ ሲዘርፍ ለነበረው አካል የሚጮኸው እጅግ ብዙ ኃይል ነው ። ይህ በጣም ያሳዝናል ። የአንዳንድ አካላት ምልከታም ሚዛናዊ አለመሆኑን መረዳት ይገባል ።

በሰላማዊ መንገድ እጅ የሰጡት እየተሰጣቸው ያለው የአቅም ግንባታ እና የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ምን ያክል ክልሉን እና ሕዝቡን አደጋ ውስጥ አስገብተው እንደነበር እየተገነዘቡ ነው ። ከዚህ በፊት የተያዙትም ሆኑ በቀጣይ በሕግ ቁጥጥር ሥር የሚውሉት ሕግን ተላልፈው ግድያ የፈፀሙ፣ ሕዝብን ያፈናቀሉት ላይ የሕግ የበላይነት ማረጋገጡ የማይቀር ጉዳይ ነው ። ስለዚህ ይህን የምርመራ ሂደት መረጃ እና ማስረጃን መሠረት አድርጎ የሕግ የበላይነትን ማረጋገጥ የመንግሥት ኃላፊነት ነው ።

**አዲስ ዘመን፡- በአማራ ክልል የሚንቀሳቀሱ ‹‹ኢ-መደበኛ›› ኃይሎች ከሕዋሓት፣ ከሸኔ እና በሌሎች ክልሎች ከሚንቀሳቀሱ የሰላም ጠል ኃይሎች ጋር ወዳጅነት አላቸው የሚል ግምገማ አላችሁ?**

**አቶ እንግዳው፡-** ምንም ጥያቄ የለውም ። ጠላት የሚጠቀመው ማንን ነው? ጠላት ብድግ ብሎ የአማራ ክልልን ሊደፍር የሚችልበት መሠረት የለውም። በውስጥ ያሉ ማናቸውንም ሕገወጦችን ወይንም ከመንግሥት ጋር መልካም ግንኙነት የሌለው ማነው በሚል ጥናት አድርገው እየሠሩ ነው ። ስለዚህ እነዚህ ኃይሎች ከቅማንት ጽንፈኛ ኃይሎች፤ ከጉሙዝ አማጺያን ጋር እና ከሕወሓት ጋር ትስስር አላቸው። ስለዚህ ችግር ፈጣሪዎች ከየትኛውም ሕገ-ወጥ አካላት ጋር ግንኙነት እንዳላቸው መታወቅ አለበት። የሁሉም ሕገ-ወጥ እንቅስቃሴዎች መዳረሻቸው ክልሉን የማዳከምና ሀገርን የማፍረስ እንቅስቃሴ መሆኑ መታወቅ አለበት ። ቁሳዊ በሆነ ሃብት እየተገዙ የሚገድሉትና የሚጎዱት የራሳቸውን ማኅበረሰብ፤ ያደጉበትን አካባቢ እና የሚኖሩበትን ሀገር የማፍረስ ጥረት ነው ። ጠላትም የሚጠቀመው እነዚህን ኃይሎች ነው ።

**አዲስ ዘመን፡- በአማራ ክልል የሚንቀሳቀሱ ‹‹ኢ-መደበኛ›› ኃይሎች ዕድሉን ቢያገኙ በክልሉ ሊስፋፉ ይችላሉ የሚል ስጋት አለ ?**

**አቶ እንግዳው፡-** የመጀመሪያው ሕዝባዊ መሠረት የላቸውም ። በሕዝብ ግንኙነት ሥራችንም ሕዝብ እና መንግሥት የማይቀበላቸውና አንቅሮ የተፋቸው ናቸው። ስለዚህ በአማራ ክልል ሊያድጉ የሚችሉበት ዕድል የላቸውም ። ምክንያቱም ሕዝባችን፣ አመራሩ እና የፀጥታ መዋቅራችን በጋራ እስከሠሩ ድረስ ወደዚህ የሚያድጉበት ዕድል አይኖርም ። ተራ የሆነ ሕገወጥ ድርጊት ሊፈፅሙ ይችላሉ ። ባህርዳር ላይ ሰሞኑን አመራርና ሕዝብን ለማሸበር ቦንብ ሊጥል የነበረ አካል በቅፅበት በቁጥጥር ስር ውሏል ። ይህ የሚያሳየው ደጀን የሆነ ሕዝብ መኖሩን ነው ።

**አዲስ ዘመን፡- በሕወሓት ወረራ ወቅት በርካታ የጦር መሣሪያ በግለሰቦች እጅ እንደሚገባ ይገመታል ። እንደክልል እነዚህ የታጠቁ ኃይሎችን ሕጋዊ መስመር ለማስያዝ ምን እየተሠራ ነው?**

**አቶ እንግዳው፡-** ሕገ ወጥ የጦር መሳሪያ ዝውውርን ለማስቆም ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ ነው ። በየአካባቢው ሕገወጥ የጦር መሣሪያ እንዳይኖር፤ የያዙትም መሣሪያ ስልጠና ወስደው ወገንን ለማስፈራራት ሳይሆን ከጠላት ራሳቸውን ለመጠበቅ የሚያስችላቸው አሠራር እየተፈጠረ ነው ። በሺዎች የሚቆጠሩ የጦር መሣሪያዎች በፀጥታ መዋቅር መያዝ ተችሏል ። በሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ ለጠላት ሊተላለፍ ሲል በቁጥጥር ስር ውሏል ። በርካታ ሽቀጣ ሸቀጥ፣ ነዳጅ፣ አልባሳት፣ ጫማ እና ተንቀሳቃሽ ስልኮችም ለጠላት ተላልፈው ከመሰጠታቸው በፊት ተይዘዋል ። ይህ የሚያሳየው የክልሉ መንግሥትና ሕዝብ በአንድነት እየሠራ መሆኑን ነው ። ስለዚህ በዚህ ነባራዊ ሁኔታ ከክልሉ የፀጥታ መዋቅርና መንግሥት አቅም በላይ የሚሆን አንድም ነገር እንደማይኖር መታወቅ አለበት ።

የሕግ የበላይነትን ማረጋገጥ የመንግሥት ኃላፊነት ነው ። የዜጎች ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ ጤናማ መሆን አለበት ። ለዚህም የክልሉ መንግስሥት በትጋት ይሰራል። ሕዝባችንንም ደጀን አድርገን ሥራችንን እንሠራለን ። አንድ ክልል ሠላም ስለሆነ ሌላው አካባቢ ሰላም አይሆንም ። በመሆኑም ሕዝባችን ከፀጥታ መዋቅር ጋር በመተባበር ለክልሉ እና ሀገር ሠላም ስጋት የሆኑ ኃይሎችን በጋራ መጋፈጥ ይገባል ። ሕዝባችንም ከፀጥታ ሥጋት ነፃ ሆኖ ወደ ልማት ፊቱን ማዞር አለበት።

**አዲስ ዘመን፡- ስጥያቄያችን ወቅታዊ መረጃና ማብራሪያ ስለሰጡን እናመሰግናለን ።**

**አቶ እንግዳው፡-** እኔም አመሰግናለሁ ።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፤ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

(ጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

# "አባባ" የመባልን የሕዝብ ፍቅር የተጎናጸፉት ንጉሥ

**"ያልታደልሽ እንዴት ከረምሽ"**

ከመንግሥታዊ ሥርዓት መሸጋገሪያ "ጥቋቁር" ታሪኮቻችን መካከል ሁለቱ መገለጫዎች በእጅጉ የጎሉና ተደጋጋሚነት የሚታይባቸው ናቸው ። አንደኛው መገለጫ አሮጌውን ሥርዓት በነፍጥም ሆነ በብልጠት አስወግዶ መንበረ ሥልጣኑን የሚቆጣጠረው አዲሱ መንግሥት "ተሸናፊውን መንበር የሚገለብጠው" እጁን በደም ታጥቦ ሲሆን፤ ሁለተኛው መገለጫ ደግሞ አዲሱና መጤው መንግሥት የቀዳሚውን ሥርዓት የታሪክ ውርስና ቅርስ ተሽቀዳድሞ የሚያጠፋውና የሚያወድመው በጭካኔና በበቀል መሆኑ ነው ።

በሁለቱ መገለጫዎች ማሳያነት ብቻ ከትናንት እስከ ዛሬ ኢትዮጵያን የመሩ መንግሥታትን ታሪክ ብንመረምር እውነታው በሚገባ ፍንትው ብሎ ሊታየን ይችላል። ትናንትን ከዛሬ ያቆራኙትን ሥርዓተ መንግሥታት ችግርና ስህተት ብቻ እየነቀስን ከማዋረድና ታሪካቸውን ከማጠልሸት ይልቅ በጎነታቸውንና ትሩፋታቸውንም ጎን ለጎን አጉልተን ላለማሳየት ማንና መቼ አዚም አድርጎ እንደቀረጸን ለጊዜው ምክንያቱ ይህ ነው የሚባል የጥናት ውጤት ስላላገኘን "ይህንን ድፍን ዕንቁላል" ይሉት ዓይነት ሀገራዊ እንቆቅልሻችንን የምንዘለው እንደተለመደው "በሆድ ይፍጀው" ትዝብት ይሆናል ። ጽናቱን ይስጥሽ ኢትዮጵያዬ!

**"አባባ ጃንሆይ"**

ለዛሬው ጽሐፍ መቀስቀሻ የሆነን የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ዜና መዋዕል በፎቶግራፍ አካቶ የታተመውና በደማቅ ሥነ ሥርዓት ሐምሌ 2 ቀን 2014 ዓ.ም በሂልተን ሆቴል የተመረቀው "አባባ ጃንሆይ" የሚለው ሥዕላዊ መጽሐፍ ነው ። የመጽሐፉ አሰናጅና አርታኢ ወዳጄ ጌታቸው ተድላ አበበ (ዶ/ር) ብርቱ ደራሲና ለሀገር በጎነት የሚተጉ መሆናቸውን ብቻ በመጠቆም ወደ ግለ ወግ ትረካዬ አመራለሁ ።

የንጉሠ ነገሥቱ 130ኛ ዓመት የሚከበረው በዚሁ ሳምንት ሐምሌ 16 ቀን 2014 ዓ.ም መሆኑን በማስታወስ ይህ ጸሐፊ የልጅነቱን ወራት ገጠመኝ ማስታወስ ብቻም ሳይሆን "አባባ ጃንሆይን መልካም ልደት!" በማለትም መልካም ምኞቱን ይገልጣል ። የንጉሡን ታሪክና በጎ አሻራዎች ከትውልድ ትውልድ ሳይደበዝዙ እንዲተላለፉ ለማድረግ "የግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ፋውንዴሽን" እያደረገ ስላለው መልካም ተግባርም ማመስገኑ ተገቢ ይሆናል ። "ከታሪክ መሰዊያ ላይ አመዱን ሳይሆን እሳቱን ጫሩ" የሚለውን አባባል ደጋግመን ብናስብበት ለበርካታ ሀገራዊ በሽታዎቻችን ስክነት በጥቂቱም ቢሆን ሊያግዘን ይችላል ።

ቀ/ኃሥ ከአልጋ ወራሽነታቸው ጀምሮ እስከ ንጉሠ ነገሥት ከፍተኛው የሥልጣን እርከን ድረስ ሀገሪቱን ያገለገሉትና የመሩት ከግማሽ ክፍለ ዘመን በላይ (1909 - 1967 ዓ.ም) ነው ። የአልጋ ወራሽነት ዘመናቸውን ካሰብነውም ከስድስት አሠርታት በላይ ይዘለቃል ። በእነዚህ ረጅም ዓመታት ውስጥ ንጉሡ ህልቆ መሳፍርት በሌላቸው ዘርፎች ሀገሪቱን ወደ ከፍታ ስለማሸጋገራቸው ታሪክ ምስክር ነው ።

ይህ ማለት ግን ንጉሡ ከስህተት ነጻ ናቸው፤ ምንም በደል የሌለባቸው ፍጹም ነበሩ ማለት እንዳልሆነ አንባቢው የሚረዳ ይመስለናል ። የከሳሾቻቸው ጭፍንም ይሁን ምክንያታዊ ፍረጃ እንደተጠበቀ ሆኖ ያለ ማንም አስገዳጅነት አብዛኛው የወቅቱ ትውልድ (ተቃዋሚዎቻቸውን ጨምሮ) ይጠሯቸው የነበረው "አባባ ጃንሆይ" እያሉ እንደነበር እድሜውን ያደለን ዜጎች ሕያው ምስክር ነን ።

ይህ ጸሐፊ የንጉሠ ነገሥቱን የዘመነ ስልጣን ትሩፋቶች በትምህርት፣ በዲፕሎማሲ፣ በኢኮኖሚ፣ በጦር ኃይል አደረጃጀት፣ በሰብዓዊ ተግባራት ወዘተ. እያለ ከመዘርዘር ተቆጥቦ ከንጉሡ ጋር የተገጣጠመበትን አዝናኙን የታዳጊነቱ ትዝታ በወግ መልክ መተረኩን መርጧል ።

**"አባባ ጃንሆይ የእኛ እናት አባት!"**

ምክንያቱን በውል ባንረዳውም አባባ ጃንሆይ ኮልፌ የሚገኘውን ፈጥኖ ደራሽ ግቢና ልዕልት ፀሐይ ሆስፒታልን (ዛሬ ጦር ኃይሎች ሆስፒታል የሚባለውን) አዘውትረው ይጎበኙ ነበር ። ንጉሡ ወደእነዚህ አካባቢዎች በመጡ ቁጥር ዛሬ በአስራ ስምንት ቁጥር አውቶቡስ ማዞሪያነት በሚታወቀው መስቀልያ መንገድ ላይ ቆመው፣ ወይንም ዝቅ በማለት ቤተሰብ መምሪያ በማይታወቅበትና ምንትስ የሚሉት የዛሬው ዘር ማምከኛ ባልተፈለሰፈበት በዚያ ዘመን ያለ ዕቅድ ለተፈለፈለው እኛን መሰል የኮልፌ ውሪ አንድ አንድ ብር ያድሉ ነበር ።

በእኛ በውሪዎቹ ዘንድም ሆነ በትላልቆቹ ሠፈርተኞች ዘንድ የአባባ ጃንሆይ መምጣት የሚታወቀው በጋሽ በቀለ ደምሴ (በቀለ ጢሞ) የዶቅዶቄ ድምጽ ነበር ። ብዙ ሰው ሻምበል በቀለ ጢሞን ይጠራ የነበረው "ጋሼ" የሚል ቅጽል በስሙ ላይ እያከለ እንጂ በሻምበልነቱ ማዕረግ አልነበረም። ሞላ ያለ ሰውነት የነበረው ጋሽ በቄ የግራና የቀኝ ፂሙን አሹሎና ኮስታራ ፊቱን አጨፍግጎ ሲመለከቱት አንዳች የፍርሃት ድባብ ያሰፍናል ። ሁሉም ሰው ጋሽ በቄ ጢሞን አንተ ይለው ስለነበር እኔም አፌን ሞልቼ የተዳፈርኩት ከጀማው አጠራር ላለማፈንገጥ ነው።

ጋሽ በቀለ ጢሞ የሚይዘው የሞተር ቢስክሌት የታርጋ ቁጥር 80 እንደነበር አስታውሳለሁ ። ጋሽ በቄ ጢሞ ንጉሡን ለምን እንደሚያዋክባቸው ባናውቅም እንደ ክረምት አሸን አካባቢውን ያጥለቀለቀው ውሪ የአንድ ብር ዳረጎቱን ተቀብሎ ሳይጠናቀቅ ሞተር ብስኪሌቱን እያስጓራ አባባ ጃንሆይን አክለፍልፎ ይወስድብን ነበር ።

አንድ ዕለት በሠፈራችን ኳስ ሜዳ እየተራገጥን ሳለ እንደ ቤተሰቦቻችን ንብረት የተለማመድናት የጋሽ በቀለ ጢሞ ዶቅዶቄ ከሩቅ እያንባረቀች ስትመጣ ሳይረፏ ጆሯችን ውስጥ ጥልቅ ይላል ። ያ አመዳም የኮልፌ ውሪ ሁላ የቡሆ ዕቃ የመሰለ አፍንጫውን እያበሰ በነፋስ ፍጥነት መክነፍ ይጀምራል ።

ይሄን ግዜ ቅንድበ ግጥሙ አብሮ አደጋችን ከንፍዬ (ንጉሡ የሚታሙበትን ያልተረጋገጠ አሉባልታ ሰምቶ ኖሮ) ከእኛ ከጓደኞቹ ወደ ኋላ ቀረት ብሎ የተጋጠመውን የቅንድቡን ፀጉር ለማስወገድ መላ ብሎ በዘየደው ብልሃት በአካባቢው ባገኘው ስለታም የባልጩት ድንጋይ ቅንድቡን ሲፈገፍግ ክፉኛ ስለቆረጠው ደሙ እየተንዠቀዠቀ ከኋላችን ከች አለ ። ግማሽ ልባችን ከንፍዬ ዘንድ፣ ግማሽ ልባችን አባባ ጃንሆይ ዘንድ እንደተከፈለ ፤

**አባባ ጃንሆይ፣ አባባ ጃንሆይ ፤ የእኛ እናት አባት፣**
**አሳድገውናል፣ አሳድገውናል ፤ በማር በወተት ።**

እያልን በመዘመር፣ ከንፈም ደሙን እያበሰ ከእኛ ጋር ተቀላቅሎ የአንድ ብር ግባችንን ልንመታ ችለናል ። ዕድሜና የሥርዓተ መንግሥታት መለዋወጥ ያላደበዘዘው የከንፌ ጠባሳ ግን ዛሬም ድረስ በቅንድቡ አካባቢ አሻራው ሳይጠፋ ምልክቱ ሆኖ ቀርቷል ። በወቅቱ "ቅንድበ ግጥም ሕፃናትን" በተመለከተ ያልተረጋገጠ የሀሜት ሹክሹክታ ይወራ ስለነበር እኛም ውሪዎቹ መላምቱን እውነት አድርገን ከንፌን መሰል ቅንድበ ግጥም ጓደኞቻችንን ማብሸቃችን እውነት ነበር ። ይህንን አፈ ታሪክ ያስታወስኩት በይባላል መሆኑ ልብ ይባልልኝ ። እንኳን እኔ ከቁምጣ ያልዘለልኩ ውሪ ቀርቶ ማንም ሰው በወቅቱ ስለ ሃሜቱ እርግጠኛ ስላልነበረ ተረት ነው ብሎ ማለፉ ይቀል ይመስለኛል ።

**የንጉሡ ብር "የበረከት ምሥጢርና" ድንክዬዋ ውሻ፤**

ከንጉሥ እጅ አዘውትሮ ብርና የማበረታቻ ቃል መቀበል እንዴት ደስ እንደሚል ከእኔና ከዕድሜ አቻዎቼ የተሻለ የሚመሰክር ያለ አይመስለኝም ። የአባባ ጃንሆይን አንድ ብር ለበረከቱ ሲል በብር ከሃምሳ ሣንቲም የሚመነዝርልንን የባለሱቁን አብደላንና የወላጆቻችንን ልማድ ሳላስታውስ ማለፉ ተገቢ አይመስለኝም ።

ከንጉሡ እጅ የምንቀበለው አንድ ብር ትርፍ ሣንቲሞችን እየጨመሩ የሚመነዘሩልን የንጉሥ እጅ የነካው ብር ልዩ በረከት አለው እየተባለ ስለሚታመን ነበር ። አንዱን ብር በትርፍነት ከለወጡ በኋላም ከሌሎች ብሮች ጋር ደባልቀው የሚያስቀምጡት ለብዙ ግዜያት ነበር ። እናቴም በትርፍነት የገዛችኝን የአባባ ጃንሆይን ብር ከሌላ ገንዘብ ጋር ደባልቃ ሙዳዩዋ ውስጥ ስታስቀምጥ በተደጋጋሚ አስተውያለሁ ።

አባባ ጃንሆይ ለእያንዳንዱ ልጅ ብር የሚያድሉት "በመሬት አንቀጥቅጥ" የንጉሥነት ክብራቸው ተኮሳትረው አልነበረም ። ተራችን ደርሶ ጫማ ስመን ብድግ በማለት እጃችንን ብር ለመቀበል ስንዘረጋ ብዙውን ግዜ ትኩር ብለው በርህራሄ እያስተዋሉን "አንተ ንፍጣም፣ አንተ ረባሽ" በማለት ከቀለዱብን በኋላ "ስታድግ በምን ሙያ መሰማራት ትፈልጋለህ? ስንተኛ ክፍል ነህ? በትምህርትህስ ጎበዝ ነህ?" በማለት ይጠይቁንና "በል ይህንን ብር አልባሌ ቦታ እንዳታጠፋው" ብለው በመምከር ያሰናብቱናል ።

ከአባባ ጃንሆይ እጅ የመጨረሻውን ድፍን ሽልንግ (ሃምሳ ሣንቲም) የተቀበልነው ካልተሳሳትኩ በስተቀር በ1960ዎቹ መጀመሪያ ገደማ ሳይሆን አይቀርም ። የተቀበልንበትን ቦታና ሁኔታ አልዘነጋሁትም እዚያው ዛሬ አስራ ስምንት ቁጥር አውቶቡስ ማዞሪያ እየተበላ በሚጠራው መስቀልያ መንገድ ላይ ቆመው ነበር ።

ንጉሡ ዝርዝር ሣንቲም ሰጥተው ስለማያውቁ በዚያን ዕለት የሰጡን ስጦታ ለአዋቂዎቹም ሆነ ለእኔ ብጤ ዘመነ አቻዎች ትልቅ የመነጋገሪያ ርዕስ መሆኑን አስታውሳለሁ ። አንዳንድ አዋቂ ሰዎችም ባልተጠበቀ ሁኔታ ለመጀመሪያ ግዜ ንጉሡ ሣንቲም መስጠታቸውን እንደ መልካም ምልኪ አልቆጠሩትም ነበር ።

በዚያን ዕለት የማስታውሰው ሌላው ክስተት እንዴትና በምን ሁኔታ እንደሆነ በማናውቀው ምክንያት የንጉሡ ድንክዬ ውሻ ከእግራቸው ሥር ሹልክ ብላ በመውጣት በቅርብ ርቀት ይገኝ በነበረ ጫካ ውስጥ መገኘቷ ጉድ አሰኝቶ ነበር ። አቤት በውሻዋ መጥፋት የደረሰው ትርምስ? ትዕይንቱ ዛሬም ድረስ ከዓይነ ህሊናዬ አልጠፋም ። የክብር ዘበኛ ወታደሮችና የፈጥኖ ደራሽ ፖሊሶች በአካባቢው ፈሰው ሰውን መቆሚያ መቀመጫ አሳጥተው ማንም ሰው ካለበት ቦታ እንዳይንቀሳቀስ በማዘዝ ያደረጉት ፍተሻና አሰሳ አጀብ የሚያሰኝ ነበር ።

ደግነቱ ያቺ ተንኮለኛ ውሻ ጊዜያዊ ትርምስ ብትፈጥርም እጅግም ሳትርቅ ወደ ልዕልት ፀሐይ ሆስፒታል መታጠፊያ ጫካ ውስጥ ስትልከሰከስ ስለተገኘች አሰሳውና ውጠራው በቀላሉ ሊጠናቀቅ ችሏል። ከውሻዋ መጥፋት ጋር ተያይዞ ይሰጥ ስለነበረው መላ ምትና ትርጉም ግን ለአንባቢ ግምት መተውን መርጫለሁ ። "በቤተ መንግሥት ውስጥ ተንደላቆ መኖር አስመርሯት የእኛን ኑሮ ለመኖር ተመኝታ ያደረገችው ነው" በማለት የኮልፌ ልኳንዳ ተራ ተልከስካሽ ውሾች ቀለዱባት እየተባለ ሲፌዝ እንደነበርም ትዝ ይለኛል ።

ንጉሡ በጸሐፊው ቤተሰብ ላይ ያሳደሩት የማይታለፍ ተፅእኖ እነሆ ከዓመታት በኋላም ቢሆን ዛሬም ድረስ ሲወርድ ሲወራረድ በኑሮው ውስጥ መንፀባረቁ አልቀረም ። ታሪኩ እንዲህ ነው ። ነፍሱን በገነት ያኑረውና የጸሐፊው ታላቅ ወንድም ግርማ በለጠ ልጅ እያለ ከአባባ ጃንሆይ እጅ አንድ ብር ሲቀበል ንጉሡ ራሱን እየዳበሱት "አንተ ንፍጣም ይህንን ብር ምን ታደርግበታለህ?" ብለው ይጠይቁታል ። ግርምሽም ትምህርትና ተማሪን ይወዳሉ ማለትን ይሰማ ስለነበር ፈጠን ብሎ አፉ ላይ እንደመጣለት "እስኪሪቢቶና እርሳስ እገዛበታለሁ" ብሎ ይመልስላቸዋል። እርሳቸውም "ቡና ግዢበት ብለህ ለእናትህ ስጣት" ብለው እንደ ዋዛ ይነግሩታል ።

ጠባዬ ሸጋውና ልዩ የመወደድ ፀጋ የተጎናፀፈው ግርማ አንድ ብሩን ከንጉሡ እጅ እንደተቀበለ ሲሮጥ ሄዶ ለእናታችን "አባባ ጃንሆይ ቡና ግዥበት ብለውሻል" በማለት በታማኝነት የንጉሡን ስጦታ ያስረክባታል ። ከዚያን ዕለት ጀምሮ ነው የቡና ሥነ ስርዓት በቤተሰባችን ውስጥ የተከበረና ደማቅ ባህል ለመሆን የበቃው ። እህቶቼም ቢሆኑ ቡና ሲያፈሉ በጥንቃቄና በአክብሮት እንዲሆን ከእናታችን ዘንድ ጥብቅ መመሪያ ስለተሰጣቸው ይህንን ትዕዛዝ ሲተገብሩ ኖረዋል ። የንጉሥ ትዕዛዝ ነዋ! እኔም ከልጅነት እስከ ጉልምስና ዕድሜዬ ለቡና ግብዣ ያለኝ አክብሮት ከፍ ያለ ነው ።

ወርሃዊ የቡና ወጭዬም ቢሆን ዛሬም ድረስ ትንሽ ሳይጋነን የሚቀር አይመስለኝም ። "አመል ይወጣ ከቤት ይከተል ከጎረቤት" እንዲሉ መሃል አራት ኪሎ በሚገኘው ቢሯችን ውስጥ በወር ሁለትና ሦስት ቀናት ባህሉን በጠበቀ ሁኔታ ድፎው እየተዘጋጀ በምሳ ሰዓት ሞቅ ደመቅ ብሎ ቡና ይፈላልን ነበር ። በቤቴ ውስጥም ቢሆን ባለቤቴ የማለዳ ሥራዋን የምትጀምረው የልማዴን ቡና በማፍላት ነው ። ይህ ልማዴ ዛሬም ድረስ አንድም ቀን ተቋርጦ አያውቅም ። ምን ይደረግ እናቴ በውርስ ያስተላለፈችልኝን የንጉሥ ትዕዛዝ መከበር ስላለበት ነዋ!

ይህ ጸሐፊ አራት ኪሎ በሚገኘው የቀድሞ ወጣቶች ወንዶች ክርስቲያናዊ ማኅበር (ወወክማ) የአንደኛ ደረጃ ተማሪ በነበረበት ወቅትም ንጉሡ እየመጡ ሕጻናት ናቸው ብለው ሳይንቁ እኛን ተማሪዎችን "የነገ ተስፋ ናችሁ" እያሉ ያበረታቱን እንደነበር ማስታወሱ ግድ ይላል ። አባባ ጃንሆይ የእኛ እናት አባት እያልን ስንዘምር የኖርነውም ንጉሡ ይህንን መሰሉን በጎ ተጽእኖ በሕይወታችንና በአብዛኛው የዚያ ትውልድ ሕይወት ውስጥ ስላተሙ ነው ። እውነት እውነት እንመስክርና ሕዝቡ ‹ከእርሳቸው በፊት እምዬ› እርሳቸውን "አባባ!" እያለ የተገዛለት ሌላ መሪ በታሪካችን ውስጥ ኖሮ ያውቅ ይሆን? በግሌ እኔ እንጃ! ሰላም ይሁን!

# ከተለመደው አሰራር መውጣት የሚጠበቅበት የንግድ ሥርዓት

**ፍሬሕይወት አወቀ**




የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት «ስለኢትዮጵያ» በሚል ርዕስ በተለያዩ ከተሞች በተለያዩ ሀገራዊ ርዕስ ጉዳዮች ላይ የሚመለከታቸውን አካላት እያወያየ ይገኛል ፡፡ በጅግጅጋ፣ በሀረር፣ በድሬዳዋ፣ በሀዋሳ፣ በአርባምንጭና ጅማ ከተሞች በተካሄዱ መድረኮችም በሰፋፊ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ የመነሻ ጽሁፎች እየቀረቡ በተሳታፊዎች ውይይቶች ተደርገዋል ፡፡ በዚህም ችግሮች ተነስተው መፍትሄዎች ተመላክተዋል፤ ተሞክሮዎችም ተጠቁመዋል ፡፡

የውይይት መድረኮቹ አንድ ሁለት እያሉ ስድስተኛው ላይ ደርሰዋል ፡፡ ስድስተኛው የውይይት መድረክም ሰሞኑን በጅማ ከተማ ተካሂዷል ፡፡ የጅማው መድረክ ርዕሰ ጉዳይ ደግሞ «ብሩህ ሃሳብ፤ ሥራና ክሕሎት ስለ ኢትዮጵያ» የሚል ነበር ፡፡ በመድረኩም ጉዳዩ በቀጥታ የሚመለከታቸው የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎችና የተለያዩ አካላት ተገኝተዋል ፡፡ ከሀገራችን አብይ አጀንዳዎች መካከል አንዱ በሆነው የስራ እድል ፈጠራ ላይ በሚመለከታቸው አካላት የመነሻ ጽሁፎች አቅርበዋል፤ ይህን ተከትሎም፤ በተሳታፊዎች ሰፊ ውይይት ተካሂዷል፡፡

በመድረኩ ከቀረቡበት የመወያያ ጽሁፎች መካከል የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስትር ዴኤታ አቶ አንዳለማው መኮንን የቀረበው ጽሁፍ አንዱ ነው ፡፡ በዛሬው ንግድና ግብይት አምዳችንም ይህን የውይይት መነሻ ጽሁፍና እሱን ተከትሎ ለተነሱ ጥያቄዎችና አስተያየቶች በአቶ አንዳለማው መኮንን የተሰጡ ምላሾችንና ማብራሪያዎችን ይዘን ቀርበናል ፡፡

አቶ እንዳለማው በጽሁፋቸው በአገሪቱ የንግድ ሥርዓት ዙሪያ፤ እየተከናወኑ ስላሉ ተስፋ ሰጪ ሥራዎችና በንግዱ ዘርፍ እየታዩ ስላሉ ተግዳሮቶችና በቀጣይ መወሰድ ስላለባቸውና ስለሚወሰዱ እርምጃዎች ሰፊ ማብራሪያ ሰጥተዋል ፡፡ በተለይ በወጪ እና ገቢ ንግድ መካከል እየታየ ስላለው ሰፊ ልዩነትና በቀጣይ መከናወን ስለሚኖርባቸው ተግባሮች ጠቁመዋል ፡፡

ኢትዮጵያ በዓለም ገበያ ተወዳዳሪ መሆን እንድትችል በማንኛውም ዘርፍ በሚገባ ታስቦ መሰራት ይኖርበታል ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው ፤ በተለይም የአገር ውስጥ ምርቶችን በብዛት፣ በጥራትና በአይነት በማምረት እንዲሁም እሴት በመጨመርና ከተለመደው አሰራር ወጣ በማለት በዓለም የገበያ ሰንሰለት ውስጥ መግባት የግድ መሆኑን በማንሳት ለዛም መዘጋጀት እንደሚያስፈልግ ያብራራሉ ፡፡

ሥርዓት ጠብቆ ለሚሰራው ሰው ንግድ ትልቅ ሥራ እንደሆነና አዋጭ እንደሆነም ጭምር አስታውቀው፣ አንድ አገር የተፈራና የተከበረ እንዲሆን ጠንካራ መከላከያ፣ ጠንካራ መከላከያ ደግሞ ጠንካራ ኢኮኖሚን እንደሚፈልጉ አብራርተዋል ፡፡ ጠንካራ ኢኮኖሚም እንዲሁ ዜጎች በሰላም ወጥተው ገብተው ሠርተው ግብር ገብረው የሚኖሩበትን የተደላደለ ሥርዓት ይፈልጋል፤ የተደላደለ የንግድ ስርዓትን ለመፍጠርም ጠንካራ መንግሥት ይፈልጋል፤ ጠንካራ መንግሥትም እንዲሁ ጠንካራ ፖሊሲን ይፈልጋል ሲሉ ሚኒስትር ዴኤታው ይገልጻሉ ፡፡

ስለንግድ አሰራሩ ተግዳሮቶች ሲያብራሩም፤ ከንግድ አንጻር እንደ አገር ጠንካራ የንግድ ፖሊሲ አለመኖሩ አንዱ ችግር መሆኑን ጠቅሰዋል ፡፡ የንግድ ህጉ ላለፉት 60 ዓመታት ሶስት የተለያየ ባህሪ ያላቸውን መንግሥታት አስተናግዷል ሲሉ አስታውቀዋል ፡፡ ቴክኖሎጂ ባደገ ቁጥር ብዙ የተለወጡ ነገሮች ቢኖሩም ውስጡን መለወጥ ግን አልተቻለም ያሉት አቶ አንዳለማው፣ ዜጎች በአነስተኛ፣ በመካከለኛና በከፍተኛ ደረጃ ንግድን በቀላሉ ጀምረው በቀላሉ የማይወጡበትና በሩቁ የሚፈራ ሆኖ መቆየቱን ነው ያብራሩት ፡፡

እንደ ሚኒስትር ዴኤታው ገለጻ፤ የትኛውም ሥራ ቢዝነስ ነው፤ ንግድ ነው ፡፡ ስለዚህ ንግድ ማንኛውም ሰው በቀላሉ ገብቶበት በቀላሉ ስርዓት ይዞ ሊወጣበት የሚችል አሰራርን ይፈልጋል ፡፡ ለዚህም የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር በአዲሱ ሪፎርም ጠንካራ ፖሊሲና ጠንካራ ህግ የሚያስፈልግ መሆኑን በማመን ስርዓቱን በመፈተሽ በርካታ ተግባራትን እያከናወነ ይገኛል ፡፡

የንግድ ፖሊሲን በተመለከተ ንግድ የሚመራበት ፖሊሲ ኢትዮጵያ ኖሯት እንደማያውቅ ጠቅሰው፣ አዲስ የንግድ ፓሊሲ ተረቅቆ በአሁኑ ወቅት የመጨረሻው ረቂቅ ተዘጋጅቷል ሲሉ ይጠቁማሉ ፡፡ ይህም እንደ አገር በንግድ ስርዓት ውስጥ ያሉ ቁልፍ ችግሮች ምንድናቸው የሚሉ ጥያቄዎችን መመለስ የሚያስችል መሆኑንም ነው ያመለከቱት ፡፡ ፖሊሲው የተለዩትን ቁልፍ ችግሮች ሊፈታ የሚችል መሆኑንም ጠቁመው፣ ይህን ጠንካራ የንግድ ፖሊሲ ተግባራዊ ማድረግ ከተቻለ በንግድ ስርዓቱ ውስጥ የሚታየውን ምስቅልቅልና ወጣ ገባ አሰራር መፍታት ይቻላል ብለዋል ፡፡

የሀገሪቱን የወጪና ገቢ የንግድ ሚዛን ክፍተትን በተመለከተም ሲያብራሩ እንደ ዜጋ እጅግ በጣም የሚያሳስብ መሆኑን ነው የጠቆሙት ፡፡ 18 ቢሊዮን የሚደርስ የአሜሪካ ዶላር ለገቢ ንግድ እንደሚወጣ ጠቅሰው፣ በአንጻሩ በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ባለፈው በጀት ዓመት ከወጪ ንግድ 3 ነጥብ ስድስት ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ማስገባት መቻሉን ይገልጻሉ ፡፡ 15 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር የንግድ ልዩነት እየታየ መሆኑን ጠቅሰው፣ ይህ ምን ማለት ነው ሲሉም ይጠይቃሉ ፡፡ እዚህ ላይ አርቆ ማሰብና መስራት የሚችል የሰው ኃይል ያስፈልገናል ይላሉ ፡፡

እንደ ሚኒስትር ዴኤታው ማብራሪያ፤ አገሪቷ አሁን ባለችበት ውስብስብ ችግር ውስጥ ሆና በተያዘው በጀት ዓመት በወጪ ንግድ/ ኤክስፓርት/ የሚገኘውን ገቢ አራት ነጥብ አንድ ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ማድረስ ተችሏል ፡፡ ስለዚህ ጠንክሮ መሥራት ከተቻለ እና ጠንካራ ተቋማት ከተገነቡ ከዚህም በላይ ውጤት ማስመዝገብ ይቻላል ፡፡ የተለመደውን ዓይነት ምርት ይዞ ወደ ገበያ በመውጣት አሁን እየታየ ያለውን የንግድ ሚዛን ጉድለት መሙላት አይቻልም ፡፡ ለእዚህም የኤክስፓርት ገቢውን የሚያሳድግ የኤክስፖርት ስትራቴጂው እየተዘጋጀ ነው ፡፡ በውስጡ የተለያዩ ጉዳዮች የተካተቱበት የስትራቴጂው ረቂቅ ላለፉት አስር ወራት ሲዘጋጅ ቆይቶ አሁን የመጨረሻው ሰነድ ላይ ደርሷል ፡፡

አሁን ያለው ሁለት አይነት ምርት ሲሆን አንደኛው ከግብርና ቀጥታ ተመርቶ ወደ ውጭ ገበያ የሚቀርብና አገሪቷ ጥገኛ ሆና የኖረችበት የወጪ ንግድ ነው ፡፡ ሁለተኛው ደግሞ በማምረቻ ተቋማት በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ እሴት ተጨምሮበት የሚወጣ ምርት ነው ፡፡ እሴት የሚጨመርበትን ይህን ምርት አሁን ካለው በበለጠ በአይነት ማበራከት ያስፈልጋል ፡፡ ስለዚህ የተዘጋጀው የንግድ ሥርዓት ፖሊሲና ስትራቴጂ የተለያዩ ምርቶችን እሴት ጨምሮ ወደ ውጭ ገበያ መላክን አንዱና ወሳኝ ጉዳዩ ያደረገ ነው ፡፡

ሁለተኛው የገበያ መዳረሻዎችን ማስፋት ነው አሁን ያሉት ነባር አገሮች እንዳሉ ሆነው፣ የገበያ መዳረሻ አገራትን ማበራከት ያስፈልጋል ፡፡ ባለፈው አመት በጦርነት ወቅት አሜሪካ ኢትዮጵያን ከአግዋ የገበያ ዕድል እንድትሰረዝ ማድረጓ ይታወሳል ፡፡ ይህ ምን ማለት እንደሆነ ይታወቃል ፡፡ አግዋ ደሃ አገራት የማምረት አቅማቸው ደካማ ስለሆነ ጥራት በሚፈለገው መንገድና መጠን ተደራሽ ማድረግ ስለማይቻሉ ከታሪፍ ነጻ ማቅረብ ቢችሉ የተሻለ ያመርቱ ይሆናል በሚል የተዘረጋ የንግድ ስርዓት ነው ፡፡

የማምረት አቅማችንን ማሳደግ ከተቻለና ተቀባይ አገራት በሚፈልጉት የጥራት ደረጃ ጥራቱን አሟልቶ ማቅረብ ከተቻለ አግዋን የመሰለ የገበያ ዕድል መፈለግ አይጠበቅም ፡፡ የትኛውም ገበያ ውስጥ ዘልቆ መግባትና ተደራሽ መሆን ይቻላል ፡፡

«የትኛውም ገበያ የተለየ እይታ፣ ክህሎትና አሁን ካለው በተሻለና እጅግ በጣም ያማረ ሥራ ይፈለጋል ፡፡ አሁን ያለው ውድድርም ይሄው ነው ፡፡ ውድድሩ ብዙ የሚያስፈራ አይደለም ፡፡ ነገር ግን መጪው ጊዜ ግን ያስፈራል» ሲሉ ሚኒስትር ዴኤታው ይገልጻሉ፤ የተለያዩ አገራትን ዝግጅት እያደረጉ ያለው ዝግጅት እና በእኛ አገር እየተደረገ ያለው ዝግጁነት እንደሚለያዩ ጠቅሰው፣ የኢትዮጵያ ዝግጅት በቂ አንዳልሆነ ይገልጻሉ ፡፡

እንደ አቶ እንዳለማው ማብራሪያ፤ ዓለም አቀፍ ጽንሰ ሃሳብን መሰረት ባደረገ መልኩ ኢትዮጵያ የት እንዳለችና የት መድረስ እንዳለባት ማየት ተችሏል ፡፡ ለዚህም ከተለመደው አሰራር ወጣ በማለት በተለየ እይታ ብሩህ የሆነ እሳቤን ይዞ መሄድ የሚችል ትውልድ ያስፈልጋል ፡፡

ይህ ትውልድ ጎጥን የተሻገረ፣ መንደርን ያለፈ፣ ወንዝ ተራራን የተሻገረ ሙሉ አገራዊ እይታ ያለውና አህጉራዊ እሳቤን የተላበሰ መሆን እንዳለበት አስገንዝበው፤ በዚህ መልኩ የሚገነባው ትውልድም ዓለም አቀፍ የምርት ሰንሰለት ውስጥ መግባት ይችላል፤ ዓለም አቀፍ የምርት ሰንሰለት ውስጥ መግባት ሲቻል ደግሞ ያለንን ሃብትና ኢኮኖሚ በሚገባ ማሳደግና የንግድ ሰንሰለት ውስጥ መግባት ይቻላል ብለዋል ፡፡

ሀገሪቱ ያለፉት በርካታ ዓመታት ሶስት አብዮቶችን ሳትጠቀምባቸው ማለፏን ያስታወሱት አቶ እንዳለማው፤ በአሁኑ ወቅት ያለንበትንና አራተኛውን የኢንዱስትሪ አብዮት በሚገባ ልንጠቀምበት ይገባል ብለዋል ፡፡ አሁን ያለንበት የኢንዱስትሪ አብዮት ዓለምአቀፋዊ መሆኑን ጠቅሰው፣ ገበያው ለሁሉም አንድ በመሆኑ በዓለም ገበያ ሁላችንም አንድ ነን ይላሉ ፡፡ በምርትና ምርታማነት እንዲሁም በጥራት ተወዳዳሪ መሆን እንደሚገባ አስገነዝበው፣ በአራተኛው የኢንዱስትሪ አብዮት ውስጥ ዘልቀን ለመግባት የተጀመሩ ስራዎችን አጠናክሮ መቀጠል እንደሚያስፈልግ አስታውቀዋል ፡፡

እሳቸው እንዳሉት፤ በቅርቡ ኢትዮጵያ የአፍሪካ የንግድ ቀጠና ስምምነትን የፈረመች ሲሆን፣ ከኤርትራ ውጭ ከ54 አፍሪካ አገራት መካከል ኢትዮጵያ አንዷ በመሆን ስምምነት አድርጋለች ፡፡ በዚህ ውስጥም ሶስት ነጥብ አምስት ትሪሊዮን የአሜሪካ ዶላር ትልቅ ገበያ አለ ማለት ነው ፡፡ ስለዚህ የዚህ ገበያ ተቋዳሽ መሆን የሚቻለውም እንደ አገር የሚገነባው ሲስተምና የሚገነቡት ተቋማት ከዚሁ ጋር የተቃኙ መሆን ይኖርባቸዋል ፡፡

በአሁኑ ወቅትም ኢትዮጵያ የዓለም የንግድ ድርጅት / WTO/ አባል ለመሆን በሂደት ላይ ትገኛለች ፡፡ ይህ ሂደት ሲጠናቀቅ ኢትዮጵያ አባል ትሆናለች ፡፡ አባል ስትሆን ደግሞ የንግዱ ማህበረሰብና አምራቹ እንዴት ተጠቃሚ መሆን እንደሚችሉ ማሰብና መስራት ያስፈልጋል ፡፡ ለእዚህም በክህሎትም ሆነ በአመለካከት ብሩህ የሆነ እሳቤ ይዞ ለመገኘት መዘጋጀት ያስፈልጋል ፡፡

የአለም ንግድ ድርጅት በአለም አቀፍ ደረጃ ትልቁ ገበያ እንደመሆኑ ትልቅ እድልና ፈተናን ይዞ የሚመጣ ነው ያሉት አቶ እንዳለማው፣ ስለሆነም ዕድሉን ለመጠቀም ከዛሬ አንስቶ መስራት ያስፈልጋል ብለዋል ፡፡

እንደ ሚኒስትር ዴኤታው ገለጻ፤ ዓለም አቀፍ የንግድ ድርጅቱ 165 አገራትን በአባልነት ይዟል፤ 22 አገራት ደግሞ አባል ለመሆን በሂደት ላይ ይገኛሉ፤ 11 አገራት ደግሞ ምንም ውስጥ የሉበትም፤ ኢትዮጵያ ነገ አባል መሆን በምትችልበት ሂደት ላይ ትገኛለች ፡፡

አቶ እንዳለማው በንግድ ዙሪያ ያቀረቡትን የውይይት መነሻ ሀሳብ መሰረት በማድረግ እንዲሁም በአጠቃላይ በሀገሪቱ የንግድ አንቅስቃሴ ላይ ከተሳታፊዎች ጥያቄዎችና አስተያየቶች ቀርበዋል፤ እሳቸው በሰጡት ምላሽና ማብራሪያም አብዛኞቹ አስተያየቶችና ማብራሪያዎች ገንቢና በቀጣይ ሊሰራባቸው የሚገቡ የቤት ሥራዎች ናቸው ብለዋል ፡፡ በንግዱ ዘርፍ የሚስተዋሉ ችግሮችን በዝርዝር በማየት የመፍትሔ አቅጣጫ ማስቀመጥ እንደሚያስፈልግም ጠቁመዋል ፡፡

የዓለም የንግድ ድርጅት 98 በመቶ ንግድ የሚካሄድበት እንደመሆኑ ከዛ ውጭ መሆን አይቻልም፤ የዓለም የንግድ ድርጅት ውስጥ መግባት የግድ ነው ብለዋል ፡፡ ለእዚህም በቂ ዝግጅት እየተደረገ እንደሆነም ገልጸው፣ ብቃት ያላቸው ተቋማትን ማዘጋጀት አንዱ መሆኑን ተናግረዋል፤ እዚህ ውስጥ የትምህርት፣ የማምረቻና የምርምር ተቋማት ትልቁን ድርሻ ይወስዳሉ ፡፡ በተጨማሪም ማህበረሰቡ ድርሻ ያለው በመሆኑ በእዚህም ላይ አስቀድሞ መስራት ያለባቸውን ሥራዎች መስራት ያስፈልጋል ብለዋል ፡፡

ከውጪ ወደ አገር ውስጥ የሚገቡትን ምርቶች የሚተኩ ምርቶችን በአገር ውስጥ በማምረት ማስቀረት እንደሚቻል ጠቅሰው፣ የተለመደውን ከግብርና በቀጥታ ምርትን ወደ ውጭ ገበያ መላክን በማስቆም እሴት ጨምሮ መላክ እንደሚገባ አስገንዝበዋል ፡፡ ቡናን በአብነት ጠቅሰውም ቡናን በቀጥታ በጥሬው ስንልክ ኖረናል ያሉት አቶ እንዳለማው፣ ወደፊትም ጥሬውን ቡና ስንልክ አንኖርም ፡፡ ስለዚህ እሴት የጨመረ ቡናን መላክ አለብን፤ ለዚህም ቴክኖሎጂው አለ ሲሉ አብራርተዋል ፡፡ ይህን ቴክኖሎጂ በመጠቀም በምንሰራው ሥራ የሥራ ዕድል ከመፍጠር ባለፈ ኢኮኖሚው ላይ የምንፈጥረው በጎ ተጽዕኖ ጎላ ይሆናል ብለዋል ፡፡ ይህን ማድረግ ሲቻል እየታየ ያለውን የገበያ ጉድለት በአጭር ጊዜ ማሟላት እንደሚቻልም በመጠቆም በንግዱ ዘርፉ ወደፊት ያለውን ተስፋ አመላክተዋል ፡፡

# ሕሊና ሕግን ይገዛል

**ዋለልኝ አየለ**

ይህ የአንድ የፊልምና ድራማ ደራሲ ገጠመኝ ነው። ጽሑፉ ‹‹ለክብርት ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ›› በሚል በማህበራዊ ገጾች ሲዘዋወር አይቼ፣ ጽሑፉን ያነበብኩት ዕለት እኔም ተመሳሳይ ገጠመኝ ማስተዋሌ ነው ትኩረት እንድሰጠው ያደረገኝ ። የታዘቢውን ገጠመኝ ላስቀድም።

‹‹.... ዛሬ ከባድ ዝናብ እየዘነበ ዝናቡን ሽሽት አንድ መንደር ውስጥ ያለ ስጋ ቤት ተጠልዬ ነበረ። የስጋ ቤቱ አስተናጋጆች በመላው አዲስ አበባ እየተለመደ የመጣውን ‹‹ከፓንት ትንሽ የረዘመ›› ቀሚስ ለብሰዋል። ብርዱ እንኳን በዚህ አለባበስ ይቅርና ጋቢ ለለበሰም ይከብዳል።

በዚህ መሀል አንዷ አስተናጋጅ ከስር ታይት አድርጋ ስትመጣ ከባለቤቱ ጋር ተጣሉ። ባለቤቱ ታይቷን እንድታወልቅ ሲያዛት እሷም ማህፀኗን እንደሚያማትና ዝናቡ እስኪያልፍ ድረስ ታይቱን እንድትለብስ እያለቀሰች ብትለምነውም በጄ ሊላት አልፈቀደም። ታይቱን እንድታወልቅ ካልሆነ ስራውን እንድትለቅ ነገራት።

ሰውየውን በሰዓቱ አነጋግሬ ከነታይቷ እንድትሰራ ካልሆነ እንደምከሰው ነግሬው ባስቆመውም ይህ ግን በአሁኑ ሰዓት የመላ ከተማው ገፅታ እየሆነ በመምጣቱ በኔ ብቻ ሊፈታ የሚችል ጉዳይ ስላልሆነ በቀጥታ ለእርስዎ ደብዳቤዬን ፃፍኩ...›› በማለት ጉዳዩን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትኩረት እንዲሰጠው ተማጽኗል።

በተመሳሳይ የዚያኑ ዕለት ማታ ከአንድ ጓደኛዬ ጋር ጉርድ ሾላ አካባቢ ከሚገኝ አንድ አነስተኛ ሆቴል ገባን፤ ሥጋ ቤትም ያለው ነው ። በዕለቱ ዝናብ ሙሉ ቀን ሲዘንብ ውሎ በዚያን ሰዓትም እየዘነበ ነበር ። እንደተለመደው የሥጋ ቤቱ አስተናጋጆች ከጭናቸው ሥር የተጣበቀች አጫጭር ቀሚስ ለብሰዋል ።

የተቀመጥነው ወደ በሩ በኩል ጠጋ ብሎ ነበር። ከጣሪያ ላይ የሚወርደው ፍሳሽ በበሩ በኩል ወደ ውስጥ እየገባ ነው ። ያቺኑ ጭኗ ሥር የተጣበቀች ቀሚስ የለበሰች አንደኛዋ አስተናጋጅ ወደ ውስጥ እየገባ ያለውን ውሃ በመጥረጊያ ወደ ውጭ ትረጫለች ። ከላይ ያለው ዝናብ እንዳለ ሆኖ ከሥር ወደ ውጭ የምትረጨው ውሃ ነጠብጣቦች በቀጥታ ሰውነቷ ላይ ነው የሚያርፉት ።

ምግብ ቤት ውስጥ እንደዚያ አይነት አጭር ቀሚስ የሚለብሱ አስተናጋጆች ትኩረት ሰጥቼ ያየሁት ያቺን ልጅ ብቻ ነው ። የሆቴሉ ተስተናጋጆችም ሆኑ አላፊ አግዳሚው ሁሉ ከእግር ጥፍራቸው እስከ ራስ ፀጉራቸው ድረስ ተከናንበዋል ። እንደዚያም ሆኖ ያልተቻለውን ብርድ ግን እነዚህ ልጆች ሙሉ ራቁት ሊሆን ምንም ባልቀረው አለባበስ የዝናብና ብርድ ማረፊያ ሆነዋል ።

ሥጋ ቤቶች የራሳቸው የአለባበስ ሕግና ደንብ እንደሚኖራቸው ግልጽ ነው ። ብዙ የሥራ ቦታዎች የራሳቸው የአለባበስ ሕግ አላቸው ። ምክንያቱ ለምን እንደሆነ ባይገባኝም የሥጋ ቤቶች ደንብ ደግሞ የሴት ልጅን ገላ የሚያራቁት ሆነ ።

ወደውና ፈቅደው የሚያደርጉት ብዙ ናቸው፤ ያ ግን በፍላጎት ነው ። የሚደረገውም በእንዲህ አይነት ብርድ ሳይሆን ለዝግጅት ነው ። በአዘቦት የሚያደርጉትም የራሳቸው መኪና ያላቸው ናቸው፤ የተሻለ የኑሮ ደረጃ ላይ ያሉ ናቸው ። ብርድ ላይ ቆመው የሚውሉ አይደሉም ።

እንግዲህ የሥጋ ቤቶችም ሆነ ሌሎች ሆቴሎች የአለባበስ ሕግ ነውና ለምን እንዲህ አደረጉ ማለት አንችል ይሆናል ። ምክንያቱም ‹‹ሕጋችን ነው›› ነው የሚሉት ።

ዳሩ ግን አንዳንዴ ሕሊና ከሕግ በታች ይሆናል ። ወደሰውየው ገጠመኝ እንመለስና፤ ለምሳሌ ልጅቷ የማህፀን ህመም አለባት ። በዚያ ብርድ ላይ ህመም ሲጨመርበት ልጅቷ ለዘላቂ በሽታ ተዳረገች ማለት ነው ። ጤናዬ ይበልጥብኛል ብላ ትታው እንዳትሄድ የዕለት እንጀራዋ ነው ። ሥራ ቶሎ አታገኝም፤ ሥራ አላገኘችም ማለት ደግሞ የዕለት ጉርሷን እና የቤት ኪራይ የምትከፍለው አታገኝም ማለት ነው ። እንዲህ ዙሪያው ገደል ሆኖባት ነው ያለቀሰችው ።

ባለገጠመኙ ባለቤቱን ባይቆጣውና ‹‹እከስሃለሁ›› ባይለው ኖሮ ልጅቷ ተባራ ነበር፤ ላለመባረር ብላ እያመማት ብትሰራ ኖሮ ደግሞ የማህፀኗ ህመም ተባብሶ የአልጋ ቁራኛ ትሆን ነበር ማለት ነው ።

የእኔ ትዝብት፤ አንዳንድ ጊዜ ሕሊና ሕግን ቢገዛ ምን ችግር አለው? ያቺ ልጅ ዝናቡ እስከሚለቅ እንኳን ከሥር ‹‹ታይት›› የሚባለውን ብታደርግ ሆቴሉ ምን ኪሳራ ይደርስበታል? እሷ እንደዚያ በመልበሷ የሚመለስ ደንበኛ ይኖር ይሆን?

የሆነውስ ሆነና ግን ‹‹የሴት መብት ተሟጋች ነን›› የሚሉ ሴቶችስ የእንዲህ አይነት ሴቶችን በደል ያስተውሉት ይሆን?

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ቤተ መጻሕፍት ውስጥ አንዲት ሴት አጭር ቀሚስ ለብሰሽ አትገቢም ተብላ በሴት መብት ተሟጋቾች ዘንድ ተነስቶ የነበረውን ከፍተኛ ቅሬታ አስታውሳለሁ ። በቴሌቭዥን ሁሉ መወያያና መከራከሪያ ሆኖ ነበር ።

ታዲያ አጭር ቀሚስ መልበስ መብት እንደሆነው ሁሉ በብርድ ወቅት ብርድን ሊከላከል የሚችል ልብስ መልበስስ ምናለ መብት ቢሆን? ሥጋ ቤቶች ሙሉ ልብስ የሚከለክሉ ከሆነ ቤተ መጽሐፉ ደግሞ አጭር ቀሚስ ሊከለክል ይችላል ። ስለዚህ ለአጭር ቀሚስ ተከላካዮች የተደረገው የመብት መሟገት ልብስ መልበስ የሚከለከሉትም የመብት ተሟጋች ያስፈልጋቸዋል ። ለዚያውም ለሕመም እየተዳረጉ ።

ሥጋ ቤት ምግብ ቤት ነው ። ጭፈራ ቤት ወይም መዝናኛ አይደለም ። ምግብ ቤት ውስጥ የሚገባው ለመብላት እንጂ ለመዝናናት አይደለም ። ስለዚህ የምግብ ቤት እንደዚያ አይነት አለባበስ ለምን ግዴታ ሆነ? እዚያ የሚገባው ሰው የምግቡ ጥራት ነው መመዘኛው ወይስ የአስተናጋጆቹ ጭን መታየት?

ገጠመኞችን ያነሳናቸው እንደ ማሳያ ነው ። በትዝብት ደረጃ ሕጋቸውን ይቀይሩ አንልም ። ዳሩ ግን በየትኛውም ሥራ ቦታ ቢሆን የሰዎችን ችግር መረዳት ባለሀብትን አያከስርም፤ የህሊና እርካታ ነው የሚሰጥ ። የሰዎችን ችግር መረዳት ሰዋዊነት ነው ።

እንኳን እነዚህን ተራ እና ቀላል ነገሮች ሕሊና ካለ ሕግንም ይበልጣል ። ሕግ የሚያስፈልገው በሕሊና መተማመን አልኖር ሲል ነው ። ሰዎች ወደ ክስ እና የፍርድ ቤት ውጣ ውረድ የሚሄዱት አለመግባባትና አለመተማመን ሲፈጠር ነው ። ሕሊና ከቀደመ እና ለሕሊናችን ተገዢ ብንሆን መተማመን ይኖራል፣ መተሳሰብና መተዛዘን ይኖራል ። ስለዚህ ሰዎች ሕግ አያስፈልገንም ነበር ማለት ነው ።

ሕግ አያስፈልግም እያልኩ አይደለም፤ ወይም ሕግ መከበር የለበትም እያልኩ አይደለም ። እያልኩ ያለሁት ሕግ የሚያስፈልገን ከአግባብ ውጭ የሆነ ስናደርግ ነውና እዚያ ድረስ መሄድ የለብንም ነው ። መተሳሰብና መተማመን ካለ ነገርየው በባለጉዳዮች ብቻ ያልቃል። ለምሳሌ አሰሪና ሰራተኛ ከተማመኑና ከተሳሰቡ ክስ እና ክርክር አያስፈልግም ። ስለዚህ በፈቃዳችን ለሕሊና ተገዢ እንሁን፤ አለበለዚያ በግዴታ ለሕግ ተገዢ እንሆናለን!

# ዓለም አቀፍ

## አስከፊው የአውሮፓ ሙቀት እየተስፋፋ ነው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

በምዕራብ አውሮፓ የተከሰተው ኃይለኛ የሙቀት ማዕበል ወደ ሰሜን እየተስፋፋ ሲሆን በዛሬውም ዕለት አስከፊ ደረጃ ሊደርስ እንደሚችል ማስጠንቀቂያዎች እየተሰጡ ነው።

ፈረንሣይ እና ዩናይትድ ኪንግደም በከፍተኛው የሙቀት ምክንያት ማስጠንቀቂያዎች የሰጡ ሲሆን ሰኞ ዕለት በሰሜናዊ ስፔን 43ዲግሪ ሴንቲግሬድ ሙቀት መጠን መዝግቧል።በፈረንሣይ፣ ፖርቱጋል፣ ስፔን እና ግሪክ የተቀሰቀሰው ሰደድ እሳት በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ቤታቸውን ለቀው እንዲወጡ አስገድዷቸዋል።

ዩናይትድ ኪንግደም ከፍተኛው ሞቃታማ ቀን ታስተናግዳለች ተብሎ የሚጠበቅ ሲሆን በአንዳንድ የፈረንሳይ ክፍሎች “አስከፊ ሙቀት” እንደሚገጥማቸው ባለሙያዎች ተናግረዋል።በርካታ የፈረንሳይ ክፍሎች ከዚህ ቀደም አይተው የማያውቁትን ሙቀት አስመዝግበዋል። በምዕራባዊቷ ናንተስ ከተማ 42ዲግሪ ሴንቲ ግሬድ መመዝገቡን ብሄራዊው የሜትሮሎጂ ቢሮ አስታውቋል።

ባለፉት ጥቂት ቀናት በተከሰተው ሰደድ እሳት ከ30 ሺህ በላይ ሰዎች ከቤታቸው ተፈናቅለው ወደ መጠለያ ጣቢያዎች እንዲገቡ ተገደዋል።በጎብኚዎች ተመራጭ የሆነችው የደቡብ-ምዕራቧ ዢሮንድ ክፉኛ ተጎድታለች። የእሳት አደጋ መከላከል ባለሙያዎች ካለፈው ማክሰኞ ጀምሮ ወደ 17 ሺህ ሄክታር የሚጠጋ መሬት ያወደመውን ቃጠሎ ለመቆጣጠር እየሠሩ ነው።



የዢሮንድ ክልል ፕሬዝዳንት ዣን ሉክ ግሌይዝ “ጭንቅላቴ ውስጥ የሚመጣው ሀሳብ ጭራቅ እንደሆነ ነው” ሲሉ ስለእሳቱ ተናግረዋል።”እንደ ኦክቶፐስ ያለ ጭራቅ ነው። ከፊት እና ከኋላ በሁለቱም በኩል እየተስፋፋ ነው። በሙቀት፣ በነፋስ እና በአየር ውስጥ የውሃ እጥረት ምክንያት ጭራቁን ለመዋጋት በጣም ከባድ ሆኖብናል” ብለዋል።

ሰኞ ዕለት 40 ዲግሪ ሴንቲግሬድ አካባቢ የደረሰው የሙቀት መጠን ማክሰኞ እንደሚቀንስ ተነግሯል። ደረቃማ እና ተለዋዋጭ ነፋሶች እስካሉ ድረስ ግን ይህ ፈጣን እፎይታ ላያመጣ ይችላል ስትል የቢቢሲዋ ሉሲ ዊሊያምሰን በዢሮንድ ዘግባለች።

በዩናይትድ ኪንግደም ታሪክ ሰኞ ዕለት በጣም ሞቃታማ ከሆኑ ቀናት ውስጥ አንዱ ነበር። በምስራቅ እንግሊዝ በሱፎልክ ከፍተኛው 38.1 ዲግሪ ሴንቲግሬድ ሆኖ ተመዝግቧል። ትንበያዎች እንደሚያሳዩት ማክሰኞ ደግሞ ከ 40 ዲግሪ ሴንቲግሬድ እንደሚሻገር ይገመታል። ይህ ከሆነም በሃገሪቱ የተመዘገበው ከፍተኛው የሙቀት መጠን ይሆናል።

በዚህ ምክንያት ጉዞዎች ተስተጓጉለዋል። የባቡር ጉዞዎች የተሰረዙ ሲሆን የለንደን ሉተን አውሮፕላን ማረፊያ በረራዎች የአውሮፕላን ማኮብኮቢያው በከባድ ሙቀት በመመታቱ የጉዞ መስተጓጎል ተፈጥሮ ነበር።ኔዘርላንድስ የዓመቱን ከፍተኛ ሞቃታማ ቀን ሰኞ ዕለት አስመዝግባለች። በደቡብ ምዕራብ ዌስትዶርፕ ከተማ የሙቀት መጠኑ 33.6 ዲግሪ ሴንቲግሬድ ደርሷል።

በኔዘርላንድስ ደቡባዊ እና መካከለኛው ክፍሎች የሙቀት መጠኑ ወደ 39C ከፍ እንደሚል በመተንበዩ ማክሰኞ የበለጠ ሞቃት እንደሚሆን ይጠበቃል።የአየር ሙቀት መጠኑ ወደ ሰሜን እያመራ መሆኑን ባለሙያዎች ገልጸዋል። ቤልጂየም እና ጀርመን በሚቀጥሉት ቀናት 40 ዲግሪ ሴንቲግሬድ የሚደርስ የሙቀት መጠን እንደሚያስተናግዱ ይጠበቃል።

በስፔን እና ፖርቱጋል ባለፉት ቀናት ከ1,000 በላይ ሰዎች ከሙቀት ጋር በተያያዘ ለህልፈት ተዳርገዋል።በፖርቹጋል ያለው የሙቀት መጠን ሐሙስ ዕለት 47 ዲግሪ ሴንቲግሬድ ደርሶ ነበር። ይህም ለሐምሌ ወር ክብረ ወሰን ሆኖ ተመዝግቧል። አብዛኛው የሃገሪቱ ክፍል በብሔራዊ የአየር ትንበያ ቢሮ (አይፒኤምኤ) በከፍተኛ የእሳት አደጋ ስጋት ክልል ውስጥ ተካቷል።

የሀገር ውስጥ መገናኛ ብዙሃን የሰሜናዊቷ ሙርካ ማዘጋጃ ቤት 300 ሰዎች በእሳት አደጋ ምክንያት ከአካባቢያቸው አስወጥቷል። ባለስልጣናት በአውሮፓውያኑ 2017 በተከሰተ ሰደድ እሳት 66 ሰዎች ህይወታቸው ያለፈበት ጊዜ እንዳይደገም ስጋት ገብቷቸዋል።

በስፔን ቢያንስ 20 እሳቶች ከቁጥጥር ውጪ እየነደዱ ነው። የፖርቹጋል ድንበር አቅራቢያ ሲጓዝ በነበረ ባቡር የተሳፈረ መንገደኛ ከባቡሩ በሁለቱም አቅጣጫ በነበረ እሳት ምክንያት ጉዞው መስተጓጎሉን የሚያሳይ ቪዲዮ ቀርጾ አሰራጭቷል።የሰው ልጅ በሚፈጥረው የአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት የሙቀት ሞገዶች በጣም ተደጋጋሚ፣ የበለጠ ኃይለኛ እና ረዘም ያለ ጊዜ የሚቆዩ ሆነዋል።

የኢንዱስትሪ ዘመን ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ ዓለምበ1.1 ዲግሪ ሴንቲ ግሬድ ገደማ ሞቃለች። መንግስታት ከፍተኛ የሆነ የልቀት መጠንን ካልቀነሱ በስተቀር የሙቀት መጠኑ እየጨመረ እንደሚሄድ ቢቢሲ ዘግቧል።

ማህበራዊ

# ባለውለታዎቻችን

## በጥምር ጥበብ ሀገሩን ያስጠራ ባለውለታ

አስናቀ ፀጋዬ

በኢትዮጵያ የስነ ጥበብ ታሪክ ስማቸው ከሀገር አልፎ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከናኙ እንቁ ኢትዮጵያውያን ጥበበኞች ውስጥ አንዱ ነው ። የስዕል ሥራዎቹ ጥልቅና ረቂቅ በመሆናቸው የራሳቸው ጥበባዊ ትንታኔ ይፈልጋሉ። በኢትዮጵያ ዘመናዊ የሥነ ጥበብ ህዋ ላይ በተለይ ‹‹አብስትራክት›› የተሰኘውን ዘመናዊ የሥዕል አሠራር ስልት በስፋት ከማስተዋወቅ በላይ የሀገሪቱን እና የሕዝቧን ሕይወት ባመዛኙ አፅም በአፅም በሆኑ ሥዕሎቹ በመግለፅ የጠቢብና የዜግነት ግዴታውን በመስዋዕትነት ጭምር ተውጥቷል ።

እንደ ዘመናዊ ሥዕሎቹ ሁሉ፣ በኢትዮጵያ የሥነ ግጥም ባህል ውስጥም አዲስ ዘር የዘራና የኢትዮጵያ ዘመናዊ ግጥም ቆርቋሪ ነው ። ግጥሞቹና ቅኔዎቹም አዲስና እንግዳ በመሆናቸው ጥቂት ከማይባሉ ወገኖች ተቃውሞ ደርሶባቸዋል ። የዛኑ ያህል ደግሞ ከብዙኃኑ አድናቆትን አትርፈዋል ። ግጥሞቹ በተለያዩ ሥነ ሰዋዊ ባህሪ ላይ አውጠንጥነው የተፃፉ በመሆናቸው በሳልና ጥልቅ መልዕክት የሚያስተላልፉ እንደሆነም ተመስክሮላቸዋል ።

የስዕል ሥራዎቹን በአፍሪካ፣ አውሮፓ፣ ሰሜን አሜሪካ፣ ደቡብ አሜሪካና እስያ በሚገኙ የተለያዩ ሀገራት በማሳየት ሰፊ እውቅና አገኝቷል ። እነዚህኑ የስዕል ሥራዎቹን ለሌሎች በማካፈልም በርካታ ሰዓሊያንን ማፍራት ችሏል ። በዚህም ከሀገር ውስጥና ከውጪ በርካታ እውቅናና ሽልማቶችን አግኝቷል- ሰዓሊ፣ ገጣሚና ባለቅኔ ገብረክርስቶስ ደስታ ።

ሰዓሊ፣ ገጣሚና ባለቅኔ ገብረክርስቶስ ደስታ የተወለደው ጥቅምት 5 ቀን 1924 ዓ.ም ከአባቱ ከአለቃ ደስታ ነገዎ እና ከእናቱ ወይዘሮ አፀደማሪያም ወንድምአገኝ በሐረር ከተማ ነው ። አባቱ አለቃ ደስታና አያቱ ደብተራ ነገዎ መሠረታቸው ሰሜን ሸዋ ውስጥ በአንኮበር አካባቢ ሲሆን ሁለቱም የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ነበሩ ። አለቃ ደስታ ወደ ሐረር የሄዱትም ልዑል ራስ መኮንን ወልደሚካኤልን ተከትለው ነው ።

እናቱ ወይዘሮ አፀደማርያም ደግሞ ከአራስ ቤት ጀምሮ ባደረባቸው ሕመም ልጃቸው ገብረክርስቶስን ጡት ሳያጠግቡት መንፈቅ እንኳን ሳይሞላው ነበር በሞት የተለዩት ። ሆኖም ገብረክርስቶስ የታላላቅ እህቶቹና የወንድሞቹን እንክብካቤ ሳይጎልበት፤ የአባቱም ፍቅርና ጉያ ሳይርቀው ማደግ ችሏል ።

የገብረክርስቶስ ደስታ ሕፃንነት በእናታቸው ጡት እጦት ብቻ አልነበረም የተፈተነው ። ገና በተወለደ በአራት ዓመቱ የሚወዳት ሀገሩ ኢትዮጵያ በፋሺስት ጣሊያን መወረሯ ሳያንስ በኋላ ላይ በወራሪው እጅ ስር ወድቃለች ።

ገብረ ክርስቶስ ደስታም ፊደል የቆጠረው በዚህ አስቸጋሪ ወቅት ነበር ። በቅድሚያ ጣሊያኖች ከፍተውት በነበረ አንድ ትምህርት ቤት ውስጥ ገብቶ ትምህርቱን ጀምሮ የነበረ ቢሆንም በትክክል የመጀመሪያ ትምህርቱን የተከታተለው ግን ነፃነት ከተመለሰ በኋላ በ1934 ዓ.ም ሐረር በሚገኘው ራስ መኮንን አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነበር ።

የልጅነቱን ግዜ በተመለከተ ‹‹የሰዓሊ ገብረክርስቶስ ደስታ ታሪክና አንዳንድ ቅኔዎቹ›› በሚል ርዕስ የዲግሪ ማሟያ ጥናታቸውን ላደረጉት ለአቶ ብርሀነ መስቀል ደጀኔ ቃለመጠይቅ በሰጡበት ግዜ የልጅነት ጓደኛው ደራሲ ሰይፉ መታፈሪያ ፍሬው እንዲህ ብለው ነበር፡-

‹‹ ገብረክርስቶስ ያኔ በክፍል ደረጃ ይበልጠኝ ነበር። ኳስ በጣም ይወዳል ። በጣም የሚሮጥ፣ ቀልጣፋ ሳይደክም የሚጫወት ነበር ። ጠረጴዛ ቴኒስም እንጫወት ነበር ። አቋሙም ስፖርተኛ ነው ። ጧት ወይም በእረፍት ሰዓት ቁጭ ብለን ፀሐይ ስንሞቅ ቁጭ ብሎ ጉልበቱ ላይ አስቀምጦ ይስላቸው የነበሩ ስዕሎች አስገራሚ ነበሩ ። ያኔ ያለምን ጥርጥር የስነ ክህን ሰው መሆኑን እረዳ ነበር ። በስነ ክህን ስሜት የተነደፈ ልጅ ነበር›› ሲል ገልፆታል ።

ከዚህ ባለፈ ገብረ ክርስቶስ ደስታ በልጅነቱ ከወንድምና ከእህቱ ይልቅ የአባቱን ስዕሎችና ሐረጎች ጽሕፈት ቤታቸው እየገባ ሰርቆም ቢሆን ማየት ይወድ እንደነበርና አንዳንዴም ቀለሞች ከቅጠልና ከአበባ እንዴት እንደሚቀመሙ ያይ እንደነበር የአቶ ብርሀነ መስቀል ደጀኔ የዲግሪ ማሟያ ጥናት ያመለክታል ።

ሰዓሊ ገብረክርስቶስ ደስታ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቱን በሐረር ካጠናቀቀ በኋላ ወደ አዲስ አበባ



ሰዓሊና ገጣሚ ገብረክርስቶሽ ደስታ፤

በመምጣት በኮተቤ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ት/ቤት ገብቶ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን ተከታትሏል ። ለነፃነቱ ስስ የነበረው ሰዓሊ ገብረክርስቶስ ከመምህሩ ጋር በመጣላቱ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ትምህርት ቤትን ለቆ ጄኔራል ዊንጌት ትምህርት ቤት በመግባት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን አጠናቋል ።

የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን ካጠናቀቀ በኋላ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ ሳይንስ ፋክልቲ ገባ ። በግዜው ግን ስዕልን እንደሙያ ለማጥናት የሚገፋፋ ሁኔታ አልነበረም ። እርሱ ከፍተኛ የስዕል ዝንባሌና ፍላጎት የነበረው ቢሆንም አስቀድሞ በሀገሪቱ የተደራጀ የስዕል ትምህርት ቤትም አልተገነባም ። ከሀገሪቱ የወደፊት ግስጋሴና ዘመናዊ እድገት አንፃር የኢኮኖሚ መሠረቷ ግብርና በመሆኑ ሰዓሊ ገብረ ክርስቶስ ዩኒቨርሲቲ ገብቶ ለማጥናት የተገፋፋው እርሻ ነበር ። ቤተሰቡም በዚሁ አቅጣጫ እንዲገፋበት መወትወት ያዙ ። እርሱም እርሻ ለማጥናት ወሰነ ።

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ለመጀመሪያ ግዜ በሀገሪቱ የተቋቋመበት ወቅት ነበርና ሰዓሊ ገብረክርስቶስ ደስታ በ1943 ዓ.ም በሳይንስ ፋክልቲ ገብቶ ግብርናን ማጥናት ጀመረ ። ትምህርቱን ግን አልወደደውም ። መንፈሱም በሚፈልገውና በማይፈልገው ነገር ክፉኛ ተወጠረ ። በሕይወቱ ለመጀመሪያ ግዜ ከራሱ ጋር መራራ ግጭት ውስጥ ገባ ። በሁለተኛ ዓመት አጋማሽ ላይ የኮሌጅ ትምህርቱን አቋርጦ ወጣ ።

ቀጣዮቹ ጊዜያት ገብረክርስቶስ ደስታ ከራሱ ውስጣዊና ውጫዊ ሕይወት ጋር ግጭት የገባባቸው ዓመታት ነበሩ ። በነዚህ አታካችና መራር አራትና አምስት ዓመታት ውስጥ ራሱን ፍለጋ ያልገባበት ስፍራ የለም ። ያልወጣበት፣ ያልወረደበት፣ ያልሞከረው ያልጣለው የለም ።

የኮሌጅ ትምህርቱን አቋርጦ እንደወጣ በመጀመሪያ በአውራጎዳና ባለስልጣን የአፈር ምርመራ ባለሙያ ሆኖ ተቀጠረ ። ሆኖም በዚህ አልረካም ። ወዲያው ሥራውን ጥሎ ወጣ ። ትንሽ ግዜ እቤት አሳለፈና ሲንክላር የነዳጅ ድርጅት አጋዴን ቀጠረው ። ዓመቱን ሳይደፍን ሥራውን አቋርጦ ወደ አዲስ አበባ ተመለሰ ። እንደገና በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሂሳብ ሠራተኛ ስታትስቲሺያን ሆኖ ተቀጠረ ። ይህንንም ብዙ ሳይሠራበት ተወው ።

በስብስቴ ነጋሲ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተቀጥሮ በመምህርነትም አገልግሎ ነበር ። በመጨረሻም ራሱን ፍለጋ ላይ የነበረው ሰዓሊ ገብረክርስቶስ ደስታ ሥራ የሚባል ነገር ትቶ በስዕል ሥራው ላይ ብቻ ተጠምዶ ያለእረፍት መሥራት ጀመረ ። በሕይወቱም በዝንባሌውም እጅግ ፍሬያማ ውጤት አገኘበት ። በወቅቱ የአሜሪካ የማስታወቂያ ድርጅት በነበረው ቤተመጽሐፍት ዘመናዊ የአሳሳል ዘዴውን የያዙና አዳዲስ የአሠራር ስልቶችን የሚያስተዋውቁ ስዕሎቹን ኤግዚቢሽን አሳየ ።

በተወለደ መንፈቅ ሳይሞላው እናቱን ያጣው ሰዓሊ ገብረ ክርስቶስ ኤግዚቢሽኖቹን አሳይቶ ዓመት ባልሞላ ግዜ ውስጥ በአካል፣ በመንፈስና በእውቀት የወለዱትን አለቃ ደስታ ነገዎን አጣ ።

ሰዓሊና ገጣሚ ገብረክርስቶስ ደስታ ከአባቱ ኃዘን በኋላ ጥቂት ቆይቶ ለኋለኛው እርምጃ ቀና በሆነው ፖይንት ፎር ይባል በነበረው የአሜሪካ የትምህርትና የባህል ድርጅት በሕፃናት የመማሪያ መጽሐፍትና እትሞች ዝግጅት ክፍል በሰዓሊነት ተቀጠረ ። በዚህም ለሁለት ዓመታት ያህል ሠራ ። በ1949 ዓ.ም ደግሞ በዓለም አቀፍ የስዕል ትርኢት ላይ ለመሳተፍ ሕንድ ኒውደልሂ አቀና ። ለመጀመሪያ ግዜም በባህር ማዶ የስነ ጥበብ አደባባይ ዘልቆ ፈነደቀ ።

ሰዓሊ ገብረክርስቶስ ደስታ ከሕንድ ከተመለሰ በኋላ የሚያበሳጨውና ተስፋ የሚያስቆርጠው አንዳንድ ሁኔታዎች ገጠሙት ። የኋላ ኋላ እየሰፋ የመጣው ለምፅ በቆዳው ላይ ምልክቶች ያሳዩ ጀመር ። በሀገር ውስጥ በኋላም ከሀገር ውጪ ወጥቶ ለመታከም ቢሞክርም ማዳን ግን አልተቻለም ። በመጨረሻ ግን ወደ ውጪ ሀገር ሄዶ ለመማር የነበረው ፍላጎት፣ ልፋትና ምኞት ተሳክቶለት የኮሎኝ የጥበብ አካዳሚ የነፃ ትምህርት እድል ሰጠውና በ1950 ዓ.ም ምዕራብ ጀርመን ገባ ።

ከዚህ በኋላ በጀርመን የቴክኖሎጂ እድገት ዘመናዊ ጥበብ የደረሰበትን የመንፈስ ርቀትና ውስብስብነት ይቦጠቡጠው ጀመር ። በ1953 ዓ.ም በቤተሆቨን አዳራሽ ከሌሎች የጀርመን ሰዓሊዎች ጋር ኤግዚቢሽን ከማሳየቱም ሌላ በ1954 ዓ.ም ኮሎኝ ከተማ በሚገኝ በጋለሪ ኩፐርስ አዳራሽ የኢትዮጵያ አምባሳደር በተገኙበት ከፍተኛ አድናቆት ያተረፈለትን ኤግዚቢሽን በግሉ አሳይቷል ።

ይህ የስዕል ትርኢት በጀርመን ዘመናዊ የአሳሳል ቴክኒክን የተካነና ለእንዲህ አይነቱም የስዕል ኤግዚቢሽን የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊም አፍሪካዊም ሰዓሊ ለመሆን አብቅቶታል ። ከዚህ በኋላም በየቦታው እየተጋበዘ በግልም በቡድንም የስዕል ትርኢት ማሳየት ችሏል ። አውሮፓንም እንደቱሪስትም እንደጠቢብም ዞሯታል ።

ሰዓሊ ገብረ ክርስቶስ ደስታ በዚሁ የስዕል ሥራው የጥንቷን የፍልስፍናና የጥበብ አምባ ግሪክን ረግጧል ። ቤልጂየም፣ ስፔን፣ ፈረንሳይንና ጣሊያንንም ጎብኝቷል ። በመጨረሻም በጀርመን ሀገር ሲከታተል የነበረውን የስዕል ትምህርት አጠናቆና በተለያዩ የአውሮፓ ሀገራት የስዕል ሥራዎቹን አሳይቶ ወደ ሀገሩ ተመልሷል ።

ወደሀገሩ ከተመለሰም በኋላ ስለወደፊት ዓላማው ተጠይቆ ጋዜጣዊ መግለጫ ሲሰጥ፡- ‹‹አስተማሪ ለመሆን ነው የምመኘው ። ሰዓሊዎች ስዕል ብቻ መሥራት አይበቃቸውም ። የስዕልን ውበትና ሚስጥር ደግሞ መማር ይገባቸዋል ። ለተማሪዎች ስለጠቅላላ የስዕል አይነትና በተለይም ስለዘመናዊ ስዕል የሚገልፅ ጠቃሚ መጽሐፍ ለማዘጋጀትም ሃሳብ አለኝ›› ብሎ ነበር ።

ከዛም ሰዓሊ ገብረክርስቶስ ደስታ በትምህርትና ሥነጥበብ ሚኒስቴር ስር ይገኝ በነበረው የስነጥበብ ትምህርት ቤት በሚፈልገው የስነ ጥበብ መምህርነት ሙያ ተቀጠረ ። እንደተመኘውም በስዕል መምህርነት የአስራ ሁለት ዓመት አገልግሎቱ አያሌ የጥበቡን ፍሬዎች አፍርቷል ።

በዚሁ ግዜ በምክትል ርዕሰ መምህርነትም አገልግሏል። በመምህርቱም በ1960 ዓ.ም በትምህርትና ስነ ጥበብ ሚኒስቴር የዓመቱ ምርጥ መምህር ተብሎ ተሸልሟል ። በቀጣዩ ዓመት የአዲስ አበባ ትምህርት ቤቶች ጽሕፈት ቤትም ምርጥ የዓመቱ መምህር በሚል ተመሳሳይ ምስጋናና ሽልማት ሰጥቶታል ።

አብረውት ያስተምሩ የነበሩት የሙያው አጋሩ አቶ ታደሰ ግዛው ስለ ገብረክርስቶስ ደስታ ለብርሃነ መስቀል ደጀኔ የጥናት ወረቀት በሰጡት ቃለመጠይቅ፡ -‹‹ገብረክርስቶስ ደስታ እጅግ ክብራዊ ሰው ነበር ። በጥበቡ የተካነ፣ በመንፈሱም በገንዘቡም እጅግ ለጋስ የነበረ፣ ህብራዊ ሰው ነበር›› ሲሉ ገልፀውታል ።

ሰዓሊ ገብረ ክርስቶስ ደስታ ጀርመን ሀገር ሳለ ባልንጀራው የነበሩት ሊቁ ዶክተር ኋለ ገብረየኋንስ ‹‹ ገብረክርስቶስ ደስታ አብዛኛውን ግዜ ቸር ነው ። እስኪለምኑትም አይጠብቅም ። ይሰጣል ይቸራል ። የሚቀበለውን፤ የሚጠይቀውንም ይወዳል ። በሰጠ መጠን ክብርና ከፍተኛነት ይሰማዋል ። በዚህ ምክንያት ሁልግዜ ለመስጠት ይመኛል ። የማጣት፤ ያልቅብኛል የሚል ፍርሃት አይደርስበትም ። እንዲህ ያለ የመንፈስ ባለፀጋ አይገኝም›› ብለዋል ።

ሰዓሊና ገጣሚ ገብረክርስቶስ ደስታ ራሱን በማስተማር ሙያ ላይ አሠማርቶ፤ለእሱና ለግጥሙም ግዜ ሰጥቶ ያለእረፍትና ድካም በመርሳት ከጀርመን ሀገር በተመለሰ በዓመቱ በ1955 ዓ.ም በሚያስተምርበት የአዲስ አበባ ስነ ጥበብ ትምህርት ቤት የሰባ ሁለት ስዕሎቹን ኤግዚቢሽን ከፍቷል ። ይህ ኤግዚቢሽን የወቅቱን የእለት፣ የሳምንትና የወሩን የአማርኛና የእንግሊዘኛ ጋዜጦችና መጽሔቶች የግለሰቦችና የሃያሲያንን ልዩ ልዩ የአድናቆት አስተያየቶችን አትርፎለታል ።

ከዚህ በኋላም ሰዓሊ ገብረክርስቶስ ደስታ የስዕል ሥራውን በሀገር ውስጥ ብቻ ሳይሆን በውጭ ሀገር በተለይ በምዕራብ ጀርመን፣ በሕንድ፣ በቼኮዝሎቫኪያ፣ በዩጎዝላቪያ፣ በግሪክ፣በስፔን፣ በጣሊያ፣ በሶቪየት ኅብረት፣ በሴኔጋል፣ በጋና፣ በቤልጂየም፣ በካናዳ፣ በአሜሪካ፣ በብራዚል፣ በኬኒያ፣ ናይጄሪያና ደቡብ ኮሪያ ተዘዋውሮ አሳይቷል ። በተለያዩ ዓለም አቀፍ ጋዜጦችና መጽሔቶች ላይም እፁብ ድንቅ ተብሏል ።

በዚሁ ሥራውም በግዜው በንጉሡ ነገሥቱ ስም ይጠራ በነበረው የሽልማት ድርጅት በሶስተኛው ዓመት ላይ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የሽልማት ድርጅት በሀገሪቱ ገና ሁለተኛ ሽልማት የነበረውን የ1958 ዓ.ም የሥነ ጥበብ ተሸላሚ ለመሆንም በቅቷል ።

ከ1967 እስከ 1968 በእድገት በኅብረት የዕውቀትና የሥራ ዘመቻ በስነ ጥበባት መምሪያው በአስተባባሪነት ሠርቷል ። ከ1967 አስከ 1970 ዓ.ም ደግሞ በአዲስ አበባ የቲያትርና ባህል አዳራሽ በሙያው አገልግሏል ። ነገር ግን በግዜው የነበረው የሀገሪቱ ፖለቲካ ለሰዓሊ ገብረክርስቶስ ደስታ ምቹ አልሆነለትም ።

በመሆኑም የሚወዳትን ሀገሩን ሳይወድ በግዱ ጥሎ ለመሰደድ ወሰነ ። በመስከረም ወር 1971 ዓ.ም የግል የስዕል ትርኢቱን በማሳየት ሰበብ ኬኒያ ናይሮቢ ሄዶ እዛ በነበረበት ግዜ የተማረበት የጀርመን ሀገር መንግሥት ባደረገለት ጥሪ ወደጀርመን ተጓዘ ። በመጨረሻም አሜሪካን ሀገር ዘልቆው በስደት እየኖረ ሳለ በ1973 ዓ.ም መጋቢት 21 ቀን በአሜሪካ አክላሃማ ግዛት ውስጥ በተወለደ በአርባ ዘጠኝ ዓመቱ በድንገት ታሞ አረፈ ።

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
ዘመን
በሪሳ
ወጋሕታ
BAKKALCHO
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጻችንንና ፌስቡክ ገጻችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

# አዲስ ዘመን ረቡዕ ስፖርት

ይህ ቦታ
ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

## የማለዳ ብስራት የሆኑ ሁለት የብር ሜዳሊያዎች

ብርሃን ፈይሳ

በአትሌቶች ዘንድ ትልቅ ከበሬታና ቦታ ከሚሰጣቸው ውድድሮች መካከል የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና አንዱ ነው። ጠንካራ ፉክክር በሚደረግበት በዚህ ውድድር ሌሎችን ረትቶ ለራስና ለሃገር ውጤት ማስመዝገብ ደግሞ ከሜዳሊያም በላይ የሆነ ከበሬታን ያስገኛል። በዚህ የተካኑት ኢትዮጵያዊያን አትሌቶችም የሃገራቸውን ስም በድል ሲያስጠሩ ባንዲራዎንም ከሌሎች በላይ ሲያውለበልቡ ዘመናትን ተሻግረዋል።

ከተጀመረ ዛሬ ስድስተኛ ቀኑን ባስቆጠረው 18ኛው የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮናም የኢትዮጵያውያን የተለመደ ድል በተለያዩ ርቀቶች ቀጥሏል። ኢትዮጵያ እስካሁን በሰበሰበቻቸው ሜዳሊያዎች ብዛት አዘጋጇን ሃገር አሜሪካንን ተከትላ ሁለተኛ ደረጃ ላይ ያስቀመጧት ሁለት የብር ሜዳሊያዎችም ትናንት የማለዳ ብስራት ሆነዋል። የወንዶች 3ሺ ሜትር መሰናክል እና 1ሺ500 ሜትር የሴቶች ውድድር ሜዳሊያዎቹ የተገኙባቸው ርቀቶች ናቸው።

አስቀድሞ በተካሄደው የ3ሺ ሜትር መሰናክል ቅድሚያ ግምት እንደተሰጠው ሁሉ የአሸናፊነት ፉክክሩ በሰሜን እና ምስራቅ አፍሪካዊያን አትሌቶች መካከል አይሎ ነበር። በዚህ ውድድር በርቀቱ ለረጅም ዓመታት የበላይነቱን ይዘው የቆዩት ኬንያዊያን አትሌቶችም ተፎካካሪ እንደሚሆኑ ቢጠበቅም የአሸናፊነት ግምቱ ግን የኦሊምፒክ ቻምፒዮኑ ሞሮኳዊው ሶፊያን ኤል ባካሊ እና በተፎካካሪው የኦሊምፒክ የብር ሜዳሊያ ባለቤት ለሜቻ ግርማ መካከል እንደሚቀር ይጠበቅ ነበር። ጌትነት ዋለ እና ኃይለማርያም አማረም በኢትዮጵያ በኩል የውድድሩ ፈተናዎችና የሜዳሊያ ሯጮች እንደሚሆኑም ተገምቶ ነበር።





ጉዳፍ ፀጋዩ እና ለሜቻ ግርማ ሁለት የብር ሜዳሊያዎችን በማጥለቅ ኢትዮጵያን አኩርተዋል፣

ብርቱ ፉክክር በታየበት በዚህ ውድድርም ተጠባቂው ባካሊ ርቀቱ 200 ሜትር ሲቀረው አፈትልኮ በመውጣት አሳማኝ በሆነ ብቃት ሲያሸንፍ፤ ኢትዮጵያዊው አትሌት ለሜቻ ደግሞ የብር ሜዳሊያውን አጥልቋል። በዶሃ የዓለም ቻምፒዮና፣ በቶኪዮ ኦሊምፒክ እንዲሁም በቤልግሬዱ የቤት ውስጥ የዓለም ቻምፒዮና የብር ሜዳሊያዎችን የሰበሰበው ለሜቻ (ሌላኛው ሲልቨር ማን) በኦሪገንም ሁለተኛ በመሆን የብር ሜዳሊያ ለሃገሩ አበርክቷል። ከውድድሩ አስቀድሞ በነበረው የዝግጅት ጊዜ የወርቅ ሜዳሊያውን ለማጥለቅ በቁጭት ወደ ስፍራው እንደሚጓዝ አሳውቆ የነበረው ለሜቻ፤ ከውድድሩ በኋላም ሌላ ቁጭት ላይ መሆኑን አንጸባርቋል።

ከሩጫው በኋላ ከዓለም አትሌቲክስ ድረገጽ ጋር በነበረው ቆይታም ‹‹በጣም ዝግ ያለሩጫ ስለነበር የአሯሯጥ ስልቴን ለመቀየር ብሞክርም እንደፈለኩት እንዳልሮጥ ገድቦኛል። ይኸውም ወርቁን የግሌ እንዳይሆን አድርጓል። በቀጣይ ግን የወርቅ ሜዳሊያው የኔ ነው፤ ዝግጅቱም ከአሁን ይጀምራል›› ማለቱን አስነብቧል።

በንፋሳማ የአየር ሁኔታ በተካሄደው ውድድር ከፍተኛ ፉክክር ሲያደርግ የታየው ሌላኛው ኢትዮጵያዊ ጌትነት ዋለም ብርቱ ተፎካካሪነቱን አስመስክሯል። ጌትነት ከሞሮኳዊው አትሌት አሸናፊነቱን ሊቀማ የሚችልበትን አቅም እስከመጨረሻው ዙር አሳይቷል። ይሁንና ርቀቱ ሊጠናቀቅ ጥቂት ሜትሮች መሰናክሉን ሲዘል በሰራው ስህተት ወደ ኋላ በመቅረቱ አራተኛ ደረጃን ይዞ ዲፕሎማ ተሸላሚነት ሊያጠናቅቅ ችሏል። ኬንያዊው አትሌት ኮንሴስለስ ሊፕሩቶ ደግሞ ሶስተኛ በመሆን የነሃስ ሜዳሊያው ለሃገሩ አስገኝቷል።

በተከታይነት የተካሄደው ሌላኛው የፍጻሜ ውድድር የሴቶች 1ሺ500ሜትር ውድድር ሲሆን፤ በዚህም የብር ሜዳሊያው የኢትዮጵያ ሆኗል። ከመነሻው ጥቂት አትሌቶች ከፊት ቀድመው በመውጣት ባከረሩት በዚህ ውድድር በዓለም ቻምፒዮና ታሪክ እጅግ ስኬታማዋ አትሌት ኬንያዊቷ ፌዝ ኪፕዬጎን ሌላኛውን ስኬቷን አስመዝግባለች። በቤልግሬድ የቤት ውስጥ ቻምፒዮና በርቀቱ የወርቅ ሜዳሊያ ባለቤት የነበረችው ኢትዮጵያዊቷ አትሌት ጉዳፍ ጸጋይ ደግሞ ለሃገሯ ሶስተኛውን የብር ሜዳሊያ ልታስቆጥር ችላለች። አትሌቷ ከኬንያዊቷ ጋር ብርቱ ፉክክር እስከመጨረሻው ስታደርግ ብትቆይም እንዳሰበችው የወርቅ ሜዳሊያውን ግን የግሏ ለማድረግ አልታደለችም።

የዩጂን እና የዶሃ የነሃስና የብር ሜዳሊያ ባለቤቷ ጉዳፍ በዚህ የውድድር መድረክም ሶስተኛውን ሜዳሊያዋን አግኝታለች። ከውድድሩ መጠናቀቅ በኋላም ‹‹ከዚህ ውድድር የተሻለ ውጤት እጠብቅ ነበር፤ ይሁንና ተፎካካሪዬ የተሻለ ልምድ ያላትና እድለኛም ነበረች። የብር ሜዳሊያ በማግኘቴ ደስተኛ ነኝ›› ስትል አስተያየቷን ሰጥታለች። አትሌቷ በ5ሺ ሜትር ውድድርም ተካፋይ መሆኗ ይታወቃል።

---

POPULATION MEDIA CENTER
Acting for Change

## ከፖፑሌሽን ሚዲያ ሴንተር ጋር በመተባበር በየወሩ የሚታተም

## “እማራለሁ ካልኩ እማራለሁ...!”

“ቻይ ሉቃስ እባላለሁ” አለችኝ።

‘እውነትም ቻይ’ አልኩኝ በልቤ። እንደው ምኑን ነው የቻለችው ይሆን?

ቀጥሎ የተመለከተው በእውነተኛ ታሪክ ላይ የተመሰረተ በደቡብ ኦሞ ዞን በዳሰነች ወረዳ በአንድ የገጠር ቀበሌ ውስጥ የደረሰ ገጠመኝ ነው።

**ቻይ፡-** “በአስራ አንድ ዓመቴ፣ ከአራተኛ ክፍል ወደ አምስተኛ እንደተዘዋወርኩ ነበር እንደአብዛኞቹ እኩዮቼ ሁሉ እኔም የምወደውን ትምህርት እንዳቋርጥ የተነገረኝ። አንደኛ የምወጣ ጎበዝ ተማሪ ስለነበርኩ ከአስተማሪዎቼ ጋር ጥሩ ቀረቤታ ነበረኝ። እናም ለአንደኛው አስተማሪዬ ቤት ውስጥ እየተፈጠረ ያለውን ነገር ነገርኩት። ምክንያቱን አልጠየቀኝም፤ ያውቀዋልና። በእኛ በዳሰነቾች ማኅበረሰብ ሴት ልጅ ጡቷ መጠጠር ሲጀምር ዘጠኝም ሆነ አስር ዓመት ቢሆናትም መጀመሪያ ትገረዝና ከዚያ ለባል ትሰጣለች”።

**መምህር፡-** “አንድ ነገር ልምከርሽ አንቺ ጎበዝ ተማሪ ነሽ። ትምህርትሽን መቀጠል አለብሽ። መገረዝም ገና በሕጻንነትሽ ያለ ዕድሜሽ ማግባትም የለብሽም። እነዚህ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ናቸው። ስለዚህ እነዚህን ዓይነት ጎጂ ድርጊቶችን ለመከላከል ወደሚሠራው የሴቶች ወጣቶችና ሕጻናት ቢሮ ሂጂ። እዚያ ይከላከሉልሻል” አለኝ።

**ቻይ፡-** “ቤተሰቦቼ እኔን ማስጨነቃቸውን ቀጠሉ። ቦርዴና አረቄ የገዛላቸው፣ እኔን ለጋብቻ ከሰጡት ከብት እንደሚሰጣቸው ቃል የገባላቸው ሰው በጣም ያረጀ፣አይኖቹ ማየት የማይችሉ፣ ሦስት ሚስቶች አግብቶ ከእኔ የሚበላልጡ ትልልቅ ልጆች ያሉት ሽማግሌ ሰው ነው።

“እማራለሁ እንጂ አላገባም!” አልኩኝ ደጋግሜ።

“ሰደቡኝ፣ ደበደቡኝ። እሱም አልበቃቸው፤ ውሃ ውስጥ እየከተቱ አሰቃዩኝ። ከእኔም አልፈው ተርፈው ሊረዳኝ የሞከረውን አስተማሪንም ደበደቡት። እኔ ግን አሁንም እንቢ አልኩኝ። ከዚያ በግድ ወስደው የወንድሜ ሚስት ጋር አስቀመጡኝ”።

“ጊዜ አላጠፋሁም። በሌሊት ከዚያ ቤት ጠፍቼ ጫካ እያደርኩ ሦስት ቀን ሙሉ ተጉዤ ሴቶችና ሕጻናት ቢሮ ደረስኩ። እነሱም ሆስቴል ማደሪያ አመቻቹልኝና ትምህርቴን ቀጠልኩ”።

**ጸሐፊው፡-** ከሕጻን ቻይ ጋር እየተነጋገርን የ14 ዓመት ዕድሜና የ18 ዓመት ዕድሜ ያላቸው ወንዶች ደርብ እና ሰብስቤ አጠገባችን ሆነው እየሰሙን አንዳንዴም በአንዳንድ የሷ ንግግሮች ላይ ጣልቃ እየገቡ አስተያየት ይሰጡ ነበርና፤ የ18 ዓመቱ ሰብስቤ፡ - “ሴቶች ካልተገረዙ ወይ እናት፣ ወይ አባት፣ወይ ወንድም፣ ወይም ደግሞ የቅርብ ዘመድ ይሞታል ተብሎ ነው የሚታሰበው በእኛ ባህል” አለኝ።

**ጸሐፊው፡-** “እናንተ ታምኑበታላችሁ ግን በዚህ ነገር?” ጠየኳቸው።

ሰብስቤ፡- “ይሆናል። ይደርሳል” አለ።

ደርብ፡- “እኔ ግን አይመስለኝም። ምክንያቱም ያላስገረዙ ቤተሰቦች ዘንድ መግባት እንኳን የፈጣሪ ቅጣትን ያመጣል ይላሉ። መጥፎ ነገር ይደርሳል ይላሉ። እኔ ግን እንደዚህ ያሉ ማለትም ሴቶች ልጆቻቸውን ያላስገረዙ ሰዎች ቤት ገብቼ በልቻለሁ። ምንም አልሆንኩም” አለ የ14 ዓመቱ ደርብ።

**ሰብሰቤ፡-** “አንተ ስለተማርክ፤ ስላወቅህ ነዋ!” አለ አቋርጦት። ቀጠለና

“በእኔ በኩል ሴት ልጅ ባትገረዝ ጥሩ ነው ነው የምለው። ግን በእኛ ባህል ሴት ልጅ ካልተገረዘች ቤተሰቧ ሁሉ ይሞታሉ”።

**ጸሐፊው፡-** “ይኸው እሷ አልተገረዘችም። ቤተሰቦቿ ምን ሆኑ?” አልኩኝ ወደቻይ ሉቃስ እየጠቆምኩኝ።

**ሰብሰቤ፡-** “ካደገችና ሳትገረዝ አግብታ ከወለደች ነዋ”

**ቻይ፡-** “እኔ ልጆቻቸውን ያላስገረዙ ሰዎች አውቃለሁ። ልጆቹ ትልልቅ ሆነዋል።ግን ቤተሰቦቻቸው አልሞቱም” አለች።

**ጸሐፊው፡-** “አንተ አሁን 14 ዓመትህ ነው። በስንት ዓመትህ ትዳር ለመያዝ ታስባለህ?”

**ደርብ፡-** “በፈለኩኝ ጊዜ ነው የማገባው። ገና እቆያለሁ”።

**ጸሐፊው፡-** “ስታገባ ግን የተገረዘች ነው የምታገባው?”

**ደርብ፡-** “አይደለም፤ ያልተገረዘች ነው የማገባው”።

**ጸሐፊው፡-** “ቤተሰቦችህ እሺ ይሉሃል እንዴ?”

**ደርብ፡-** “አይሉም። ግን አሁን እኔ ከዚያ ጭንቅ ነገር ወጥቻለሁ።ተምሬ እውቀት አግኝቻለሁ። ሃሳቤ ሁሉ ወደዚህ ነው፤ ወደኋላ አልመለስም”።

**ጸሐፊው፡-** “በስንት ዓመቷ ነው እዚህ እናንተ ጋር ሴት ልጅ የምታገባው?”

**ደርብ፡-** “እነሱ ተገረዘች ከተባለ ወዲያው መዳር ነው። አንዲት ልጅ ጡቷ ትንሽ ጠንከር ማለት ከጀመረ ወዲያው ይገርዟትና እንድታገባ ያደርጓታል። አርብቶዎች እንደዚህ ናቸው”።

**ጸሐፊው፡-** “ያገባች እህት አለችህ?”

**ደርብ፡-** “አዎ”

**ጸሐፊው፡-** “በስንት ዓመቷ አገባች?”

**ደርብ፡-** “በአስር ዓመቷ፣ እቺን ስታክል” አለ እጁን ቁመት ለመስፈር ወደታች አድርጎ፤ “አሁን ሁለት ልጆች ወልዳለች”።

**ጸሐፊው፡-** “ታናሽህስ?”

**ደርብ፡-** “እሷ ገና በጣም ሕጻን ነች”።

**ጸሐፊው፡-** “በቅርብ የምታገባ ይመስልሃል?”

**ደርብ፡-** “አይ ጡቷ እስኪጠነክር ትቆያለች”።

**ጸሐፊው፡-** “አንተ ግን ስታስበው በስንት ዓመቷ ብታገባ ጥሩ ነው?”

**ደርብ፡-** “እስከምታድግ ድረስ፣እስከምትፈልግ ድረስ ቆይታ ብታገባ መብቷ ቢሆን ጥሩ ነው። አሁን ግን አርብቶ አደሮች እንደዚህ አያደርጉም። በአረቄ፣ በምናምን ነው ልጆቻቸውን የሚሰጡት”።

**ጸሐፊው፡-** “ለልጅቷ ወላጆች ነው የሚሰጡት?”

**ሰብስቤ፡-** “አዎ ጉቦ ነው” አለ የ18 ዓመቱ ሰብሰቤ ጣልቃ ገብቶ።

**ጸሐፊው፡-** “አንተ እህት አለህ?”

**ሰብስቤ፡-** “አዎ፤ አግብታለች። ግን በ 17 ዓመቷ ነው”።

**ጸሐፊው፡-** “እንዴት በአስር ዓመቷ ከማግባት አመለጠች?”

**ሰብስቤ፡-** “አባታችን ስለሞተ እኔና ወንድሜ ጠብቀናት ነው”።

**ጸሐፊው፡-** እየተቀባበሉ አወጉኝ። በአጉል ልማዳዊ ማስፈራሪያ ሴት ሕጻናት እንደሚገረዙ፣ ወዲያው እንደሚያገቡ፣ አረቄ፣ ቦርዴና ከብት ለማግኘት ሲባል ገና በሕጻንነታቸው እንደሚዳሩ፣ ገና በልጅነታቸው አከታትለው መውለድ እንደሚጀምሩ፤ የግርዛት፣ የልጆች ጋብቻና የሌሎችም ተደራራቢ ጎጂ ድርጊቶች ሰለባ እንደሚሆኑ።

ቻይ ሉቃስ ግን ግርዛቱም ሆነ የሕጻንነት ጋብቻው ጉዳት እንደሆነ ተገንዝባለች። ተድራ ቤተሰቦቿን በምታስገኝላቸው ከብትና ጥቃቅን ጥቅም መሳይ ነገር ሳይሆን አድጋ፣ ተምራ፣ ትልቅ ደረጃ ደርሳ በምታገኘው ገንዘብ እንደምትጦራቸው ትናገራለች።

አሁን ላይ ግን...

“አልገረዝም ካልኩኝ አልገረዝም!” “አላገባም ካልኩኝ አላገባም!”

“እማራለሁ ካልኩም እማራለሁ!” በማለት በእልህ ውሳኔዋን ተናግራለች።

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ